LIBRAIRIE ORIENTALE ET AMÉRICAINE

HENRI CORDIER
*Professeur à l'École des Langues Orientales.*

**Bibliotheca sinica. Dictionnaire bibliographique des ouvrages relatifs à l'Empire chinois.**

Deuxième édition, revue, corrigée et considérablement augmentée.

Division de l'ouvrage : I. La Chine proprement dite. — II. Les Étrangers en Chine. — III. Relations des Étrangers avec les Chinois. — IV. Les Chinois chez les peuples étrangers. — V. Les Pays tributaires de la Chine.

L'ouvrage paraîtra en six fascicules grand in-8° brochés, formant trois tomes, à raison de deux fascicules par an.

Fascicule III . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . Net 25 »

*Il a été tiré quelques exemplaires sur papier de Hollande :*

Prix du fascicule, sur Hollande . . . . . . . . . . Net 40 »

«La grande bibliographie des ouvrages relatifs à la Chine, entreprise par M. Henri Cordier, sera un très précieux recueil, et la vigueur avec laquelle elle se poursuit est le gage d'un prochain achèvement. Certainement, aucun dépouillement aussi complet de cette vaste matière bibliographique n'aura été fait... La bibliographie bien faite est de l'histoire, souvent plus vraie, plus complète que l'histoire proprement dite, si souvent rédigée par à peu près.»

Ernest Renan
*Journal Asiatique, XVI, 1879, p. 58.*
*Rapport annuel, 1878-79.*

«M. H. Cordier stands unrivalled among bibliographers for the exactness, completness and lucid classification of his work, which is a monument of industry.»

E. J. Eitel
*China Review, XXI, p. 59.*

«M. Cordier is a specialist, but one who brings to his task high literary qualifications... Our author's diligence and acumen are apparent on every page.»

A. Wylie
*London and China Express, June 20, 1879.*

«Tous les savants, et particulièrement les sinologues, reconnaissent le mérite que M. Cordier s'est acquis par ses travaux sur la bibliographie chinoise. La Bibliotheca Sinica est un « Standard-work»...

G. Schlegel
*Toung Pao, IV, 1893, p. 452.*

HENRI CORDIER
*Professeur à l'École des Langues Orientales.*

**Aperçu sur l'Histoire de l'Asie en général et de la Chine en particulier.** Conférence faite en anglais, à Saint-Louis, au Congrès des Arts et des Sciences, à l'occasion de l'Exposition internationale. Brochure in-8° . . . . . . . 3 frcs.

**C. MONDON-VIDAILHET**

*CONSEILLER D'ÉTAT DE L'EMPIRE D'ÉTHIOPIE, CHARGÉ DU COURS D'ABYSSIN A L'ÉCOLE DES LANGUES ORIENTALES*

# CHRONIQUE
## DE
# THÉODOROS II
## ROI DES ROIS D'ÉTHIOPIE
## (1853-1868)

D'APRÈS UN MANUSCRIT ORIGINAL

TEXTE ABYSSIN (AMHARIQUE)

LIBRAIRIE ORIENTALE & AMÉRICAINE
E. GUILMOTO, Éditeur
6, Rue de Mézières, PARIS

C. MONDON-VIDAILHET

*CONSEILLER D'ÉTAT DE L'EMPIRE D'ÉTHIOPIE, CHARGÉ DU COURS D'ABYSSIN A L'ÉCOLE DES LANGUES ORIENTALES*

# CHRONIQUE DE THÉODOROS II

## ROI DES ROIS D'ÉTHIOPIE

## (1853–1868)

D'APRÈS UN MANUSCRIT ORIGINAL

TEXTE ABYSSIN (AMHARIQUE)

LIBRAIRIE ORIENTALE & AMÉRICAINE

E. GUILMOTO, Éditeur

6, Rue de Mézières, PARIS

VIENNE. — TYP. ADOLPHE HOLZHAUSEN,
IMPRIMEUR DE LA COUR I. & R. ET DE L'UNIVERSITÉ.

# INTRODUCTION.

Je n'ai point à rappeler les évènements qui ont, dans ces dernières années, attiré l'attention de l'Europe sur l'Abyssinie. Depuis l'expédition qu'y firent les Portugais, au XVIe siècle, jusqu'au milieu du XIXe siècle, on peut dire que l'Ethiopie était redevenue le mystérieux empire du Prêtre-Jean. Elle a repris aujourd'hui, grâce à un souverain libéral et éclairé, contact avec les peuples européens avec lesquels les Abyssins, malgré leur teint bronzé, ont tant de points de ressemblance qu'on peut les considérer comme en faisant partie. Le résultat de l'intérêt qui s'est porté sur ce pays a été la publication de nombreux ouvrages historiques et littéraires, d'une valeur très diverse, mais qui ont été accueillis avec faveur. La littérature de ce peuple y a gagné d'être mieux connue; malheureusement, si la langue liturgique (gheez) a été l'objet de nombreuses publications, la langue populaire, l'amharique, — qui peut, à bon droit, être appelée la langue abyssine, — a été assez négligée. Cela tient certainement au petit nombre de documents écrits en cette langue que contiennent nos bibliothèques, car

l'amharique possède une certaine littérature et il est depuis bien des siècles la langue officielle, diplomatique et commerciale de l'empire d'Ethiopie, dont l'Abyssinie est la région dominante.

Nous devons cependant signaler les récents travaux de M. Ignace Guidi, qui a publié d'intéressants documents originaux dans cette langue, et de M. Enno Littmann, qui a publié précisément une chronique du roi Théodoros, d'après un manuscrit amharique de la Bibliothèque royale de Berlin.[1] Cette chronique, attribuée avec raison, je crois, au dabtarâ Zanab, ne comprend malheureusement que la première partie du règne du fameux despote abyssin et s'arrête aux rébellions d'Ato Sayfou dans le Choâ et de Négoussié dans le Tigré.

J'eus la bonne fortune, pendant mon séjour en Ethiopie, de pouvoir me procurer une chronique différente du même Théodoros, grâce à l'amabilité de l'alaqâ Gabra Sellassié, secrétaire des commandements de l'empereur Menilek, qui voulut bien échanger son manuscrit contre une copie que j'en fis faire. Le manuscrit offre cette particularité d'être écrit sur parchemin mêlé de papier arabe. Bien que cette chronique contienne moins de détails sur la période comprise dans la chronique de Berlin publiée par M. Littmann, elle a sur celle-ci l'avantage d'être complète, c'est-à-dire de donner la vie de Théodoros toute entière, jusques et y compris sa mort tragique à Maqdalâ.

Le manuscrit de Berlin contenant la chronique du dabtarâ Zanab — et non Zanêb, comme l'ont écrit à tort Prätorius et M. Littmann, — a dû être copié par un

[1] MS. orient. quart. 478.



scribe certainement plus préoccupé d'embellir son livre au point de vue calligraphique que de donner à la ponctuation une forme rationnelle. Cela se voit trop souvent en Ethiopie. La ponctuation du manuscrit de Berlin est absolument déplorable et M. Littmann a eu, à mon avis, le grand tort de la conserver. Je ne crois pas que la probité scientifique ait rien à voir avec le soin méticuleux qu'on peut apporter à conserver les fautes de copistes inconscients, excellents calligraphes parfois, presque toujours dépourvus du moindre sens critique. On pourrait admettre à la rigueur ce respect exagéré si l'on se trouvait en présence du manuscrit original d'un auteur; mais, malheureusement pour l'élégance du langage et la suite de la pensée, les auteurs éthiopiens écrivent bien rarement eux-mêmes; ils dictent.

Le manuscrit que nous publions est convenablement ponctué; j'ai eu fort peu à y retoucher et je puis dire que je n'ai fait que réparer quelques omissions. J'ai mis aussi en relief d'assez nombreux passages en vers, qui ne sont point détachés dans le manuscrit, les copistes se contentant souvent d'une certaine ponctuation pour les indiquer. Je l'ai fait surtout parce que la poésie abyssine contient presque toujours des jeux de mots qui exigent des explications particulières.

Je possède dans ma collection un second manuscrit de la chronique, celui-ci sur parchemin; mais j'ai la certitude qu'il n'est qu'une copie du premier qui, étant donné sa provenance, pourrait bien être le manuscrit original. Je n'ai relevé que quelques-unes des variantes qui existent entre les deux manuscrits; je n'ai jugé utile de le faire que pour indiquer de temps à autre l'usage des différents caractères ayant aujourd'hui la même va-

leur phonétique, mais je n'y ai point manqué lorsque les deux manuscrits présentaient des formes ou des mots différents. Le second manuscrit, ayant été copié par un Godjamite, se ressent de l'origine du copiste, les lettrés du Godjam employant certains caractères de préférence à d'autres, sans que la prononciation en soit changée pour cela, sauf lorsqu'il s'agit du *dz'aday* ou du *tzappa*, mis au lieu du *t'ayt*. J'ai indiqué ces changements par des astérisques, qui se rapportent tous au second manuscrit.

Lorsque l'alaqâ Gabra Sellassié me remit la chronique, il me dit de bonne foi que l'auteur en était dabtarâ Zanab, celui auquel est attribuée la chronique de Berlin. En lisant le manuscrit il me fut facile de constater son erreur. Il y existe, en effet, un passage où il est dit : « Celui qui a écrit cette chronique est du pays du Méhouy Qwallâ Warraw (?) dans le Choâ; son nom est Walda Mâryâm . . . » Ce passage indique suffisamment que l'auteur du livre fut l'alaqâ Walda Mâryâm, du Choâ, dont j'ai entendu parler maintes fois et qui occupa un rang distingué parmi les lettrés abyssins. Il avait passé une partie de sa jeunesse dans l'entourage immédiat de l'aboune Salâmâ, le métropolite dont le rôle, parfois mystérieux, fut souvent important pendant le règne de Théodoros. Le style des deux manuscrits est assez différent. Les deux ouvrages sont bien écrits dans l'amharique le plus correct parlé de notre temps; mais il est à remarquer que le dabtarâ Zanab use de transpositions de membres de phrase d'une façon qui lui est particulière et qu'on trouve peu en amharique, bien qu'elles ne soient pas sans élégance. Les deux chroniqueurs étaient cependant originaires de la même pro-



vince, le Choâ. Cela se voit surtout dans la chronique que nous publions. Toutes les sympathies de l'auteur vont à Menilek et son livre éclaire d'un certain jour les particularités qui précédèrent le retour au Choâ du futur souverain de l'Ethiopie, longtemps en otage à la cour de Théodoros.

Les deux chroniques, — celle du manuscrit de Berlin et celle que nous publions, — ont un caractère bien différent. On trouve dans chacune d'elles des renseignements qu'on ne trouve pas dans l'autre, si bien que les deux écrits se complètent dans une large mesure et offrent une intéressante histoire anecdotique de Théodoros. Quelques-unes de ces anecdotes ont été publiées, arrangées le plus souvent, par Guillaume Lejean [1] et d'autres voyageurs. On sent cependant que les deux chroniqueurs racontent des choses vues : dabtarâ Zanab avait été secrétaire des commandements de Théodoros et alaqâ Walda Mâryâm occupa une situation distinguée à la cour du Choâ. Tous deux étaient donc particulièrement autorisés à raconter les évènements auxquels ils avaient assisté. Malgré les terribles massacres qui ensanglantèrent les dernières années du règne de Théodoros, on sent qu'ils ont partagé dans une large mesure l'admiration du peuple abyssin pour l'étrange souverain parvenu dont les cruautés n'ont pu faire oublier le brillant début et dont le nom redouté reste encore populaire en Ethiopie.

Paris, 3 novembre 1904.

C. MONDON-VIDAILHET.

---

[1] *Théodore II et le nouvel empire d'Ethiopie.*

የደግማዊ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ንጉሠ ፡
ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ባንድ ፡
አብነት ፡ የሚገኝ ፡ ታሪክ ፡
ይህ ፡ ነው ። ይህን ፡ ታሪክ ፡ የ
ጻፈው ፡ ስሙ ፡ አለቃ ፡ ወልደ ፡
ማርያም ፡ አገሩ ፡ ሸዋ ፡ ም
ሁይ ፡ ቈላ ። ይህንም ፡ መ
ጻፍ ፡ ያሳተመው ፡ አቶ ፡ ሞን
ዶን ፡ ዊዳሌ ፡ በ ፲፰፻፺፪ ዓመተ ፡
ምሕረት ፡ በፓሪስ ፡ ከተማ ።

ይገኛል ፡ በፓሪስ ፡ በሙሴ ፡ ጊልሞቶ ፡
ቤት ፡ ፮ ሩድመዜር ፡ በሚባል ፡ መንገድ ።

ንጽሕፍ ፡ መጽሐፈ ፡ ታሪክ ፡ ዘቴዎድሮስ ፡ ንጉሠ ፡ ኢትዮጵያ ። እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ከፈጠረው ፡ ፯ሺ ፫፻፵፰ ዓመት ፡ ሲሆን ፡ በዘመነ ፡ ማቴዎስ ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ ሲባሉ ፡ ሽፍታ ፡ ሁነው ፡ ወጡ ፡ የመንግሥት ፡ ስምዎን ፡ ኋላ ፡ እናመጣዋለን ። የዚህስ[1] ፡ ምክንያት ፡ ነገር ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ በቋራ ፡ የደጃች ፡ ክንፉ ፡ የወንድም ፡ ልጅ ፡ ሁነው ፡ አደጉ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ደጃች ፡ ክንፉ ፡ ለማኅበረ ፡ ሥላሴ ፡ መነኰሳት ፡ ከልጆቼ ፡ አልጋዬ ፡ እንዳይሄድ ፡ እዘኑልኝ ፡ አትርሱኝ ፡ ብለው ፡ ፪ ሰዎች ፡ ላኩ ፡ እነዚያም ፡ መነኰሳት ፡ ከልጆችህ ፡ አልጋህን ፡ የሚይዝ ፡ የለም ፡ ገዢው ፡ የወንድምህ ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ ነውና ፡ አደራ ፡ ብለህ ፡ ንገረው ፡ ብለው ፡ ላኩባቸው ፡፡ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ ከትምህርት[2] ፡ ቤት ፡ ገብተው ፡ ዳዊት ፡ ደግመው ፡ ወታደርነት ፡ ከደጃች ፡ ጐሹ ፡ ሄዱ ። ከዚያም ፡ ኑረው ፡ ተመልሰው ፡ ከራስ ፡ አሊ ፡ ቤት ፡ ገቡ ፡ ሰዎችም ፡ ከዚህ ፡ ኑር ፡ ምሽት ፡ አግብተህ ፡ ቢሏቸው ፡ የራስ ፡ አሊን ፡ ልጅ ፡ አገባ ፡ እንደሆን ፡ አሉ ። እነዚያም ፡ ሰዎች ፡ የራስ ፡ አሊን ፡ ልጅ ፡ ላንድ ፡ ወታደር ፡ ይስጡ ፡ ብሎ ፡ ማን ፡ ይደፍራል ፡ ሲሉ ፡ ነገሩን ፡ አቀለሉት ። ፪ ሰዎች ፡ ወደጆች ፡ የሆኑ ፡ ግን ፡ እግዚአብ

---

[1] በዚኅ ፡ [2] ትምርት ፡

ሔር ፡ ያዘዘው ፡ አይቀርም ፡ ብለው ፡ ለራስ ፡ አሊ ፡ ገብተው ፡ ቢነግሩ ፡ የኔን ፡ ልጅ ፡ አንድ ፡ ወታደር ፡ እንዴት ፡ ደፈረ ፡ ብለው ፡ ተቆጡ ። እናትዎ ፡ ወይዘሮ ፡ መነን ፡ ግን ፡ ክርስቶስ ፡ ባለው ፡ ይሁን ፡ እንስጠው ፡ በሀብቱ ፡ ያሳድራት ፡ ብለው ፡ ሰጡዋቸው ፨ ። ወይዘሮ ፡ ተዋበችን ፡ አግብተው ፡ አማች ፡ ሁነው ፡ ሲኖሩ ፡ መድኃኒት ፡ ቀምሰው ፡ እራቴን ፡ ብለው ፡ ቢልኩ ፡ ወርች ፡ ሥጋ ፡ መጣልዎ ። ልጅ ፡ ካሳም ፡ ወርች ፡ ሥጋስ ፡ አልበላም ፡ ገምቦኛም ፡ አይዶለሁ ፡ ብለው ፡ መለሱት ። ወይዘሮ ፡ ተዋበችም ፡ ሚስትዎ ፡ አገር ፡ ያለህምን ፡ ታጠቅ ፡ እንሂድ ፡ ቢሉ ፡ ምነው ፡ የለኝ ፡ ብለው ፡ ይዘዋቸው ፡ ቋራ ፡ ወረዱ ፡ አባ ፡ ታጠቅ ፡ ተባሉ ። ከዚያም ፡ ሲኖሩ ፡ ልጅ ፡ ካሳም ፡ ሰው ፡ ያስከትሉ ፡ ዠመር ፡ ወሬም ፡ ተሰማ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ወይዘሮ ፡ መነን ፡ አለፉ ፡ ተቀምጠው ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ ቋራ ፡ ሸፈተ ፡ አሏቸው ። ጦር ፡ ሰብስበው ፡ ቢወርዱ ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ ጭንዎን ፡ ወግተው ፡ ወይዘሮ ፡ መነንን ፡ ያዙ ። ይህን ፡ ጊዜ ፡ ራስ ፡ አሊ ፡ ብሩ ፡ ጐሹን ፡ ለመያዝ ፡ ብቸና ፡ ተቀምጠው ፡ ነበሩ ፡ የናትዎን ፡ መወጋት ፡ የደጃች ፡ ካሳን ፡ መውጣት ፡ ቢሰሙ ፡ ደጃች ፡ ጐሹን ፡ ጦር ፡ አድርገው ፡ ሰደዱ ። ጉር ፡ አምባ ፡ ላይ ፡ ገጠሙዋቸው ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ደጃች ፡ ጐሹ ፡ ሞቱ ፡ ሌሎችም ፡ ከደጃች ፡ ጐሹ ፡ ጋራ ፡ አለቁ ፡ የቆሰለው ፡ የተማረከውም ፡ ብዙ ፡ ነው ። ለደጃች ፡ ጐሹም ፡ የጐጃም ፡ አልቃሽ ፤

ጐሹ ፡ እንደ ፡ አርዮ ፡ አሊ ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡
የጥንት ፡ አይደለሞይ ፡ ተልከ ፡ መሞት ፡

አለች ። በዚህም ፡ ስልፍ ፡ የደጃች ፡ ካሳ ፡ ሰውና ፡ የደጃች ፡ ጐሹ ፡ ሰው ፡ በነፍጥ ፡ ተመትተው ፡ ወድቀው ፡ ሳሉ ፡ የደ



ጃች ፡ ካሳ ፡ አንድኛው ፡ በቀል ፡ ይባላል ። አንተ ፡ የማነህ ፡ ቢለው ፡ የደጃች ፡ ጐሹ ፡ እንግዲያው ፡ የማነን ፡ እፈልጋለሁ ፡ ብሎ ፡ እየተጐተተ ፡ ቀርቦ ፡ በድንጋያ ፡ አፍንጫውን ፡ መትቶ ፡ ገደለው ። ይህም ፡ ነገር ፡ ድንቅ ፡ ተብሎ ፡ ከግዳይ ፡ ቍጥር ፡ በለጠ ። ደግሞም ፡ ደደጃች ፡ ካሳ ፡ አዝማሪ ፡ ጣፋጭ ፡ ከደጃች ፡ ጐሹ ፡ ሲኖር ፡ የጠሩ ፡ ለት ፡ ተያዘ ። አፉም ፡ ክፉ ፡ ተናግርዋል ፤

አያችሁት ፡ ብያ ፡ የኛን ፡ እብድ ፡
፳ ጋሞች ፡ ይዞ ፡ ጉራምባ ፡ ሲወርድ ፡
ወዶ ፡ ወዶ ፡ በሴቶቹ ፡ በነጕንጭት ፡ ለምዶ ፤

አለ ። ከደጃች ፡ ጐሹ ፡ ቤት ፡ ሁኖ ፡ ይህነን ፡ ገጠመ ፡ ተይዞ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ባደባባይ ፡ አቁመው ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡ እንዴት ፡ ብለህ ፡ ሰደብኸኝ ፡ ቢሉት ፡ እጅግ ፡ ተጨነቀ ፡ እንዴህም ፡ አለ ፤

እወይ ፡ ያምላክ ፡ ቁጣ ፡ እወይ ፡ የግዜር ፡ ቁጣ ፡
አፍ ፡ ወዳጁን ፡ ያማል ፡ ሥራ ፡ ሲያጣ ፡

አለ ፡ እንዲህም ፡ ቢል ፡ ሞት ፡ አልቀረለትም ፡ በሸመል ፡ ገደሉት ፡ ይህ ፡ የተደረገ ፡ በኅዳር ፡ በ ፲፱ ቀን ፡ ነው ፨ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ አሊ ፡ በሁዳዴ ፡ ጦም ፡ ጐጃም ፡ ሁነው ፡ ፬ ደጃች ፡ አዝማች[1] ፡ ያዘው ፡ በለው ፡ አቤ ፡ የላስታውን ፡ ብሩ ፡ አሊጋዝ ፡ ደጃች ፡ ውቤም ፡ ከስሜን ፡ ፯ አምበል ፡ ጨምረው ፡ ሰደዱ ። ደጃች ፡ ካሳም ፡ እኒህን ፡ ሁሉ ፡ ተቀብለው ፡ ፭ ቱንም ፡ ፈጁዋቸው[2] ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የራስ ፡ አሊን ፡ ከተማ ፡ ደብረ ፡ ታቦርን ፡ ፮ ተኛ ፡ አቃጠሉ ፡

---

[1] ደጃዝማች ፡ [2] ፈጁዋል ፡

በመዠመሪያ[1] ፡ ታርቀው ፡ ከራስ ፡ አሊ ፡ ወይዘሮ ፡ መነን ፡ ማኅደረ ፡ ማርያም ፡ ገብተው ፡ ከፍርቃ ፡ በር ፡ በታች ፡ ሰጥ ቸዋቸው ፡ ደጅ ፡ አዝመች ፡ ተብለው ፡ ነበር ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ራስ ፡ አሊ ፡ ጐጃም ፡ ገሠገሡ ፡ በቀረቡም ፡ ጊዜ ፡ የራስ ፡ አሊ ፡ ሰው ፡ ይህ ፡ ቆለኛ ፡ በርበሬ ፡ ኰትኳች ፡ የኛ ፡ ተዋጊ ፡ ሊሆን ፡ መጣ ፡ አለ ። አንዱም ፡ ላንዱ ፡ ወታደር ፡ አንድ ፡ ለ፲ ር ፡ ይደርሰን ፡ ቢለው ፡ ተው ፡ እንዲህስ ፡ አትበል ፡ እግ ዚአብሔር ፡ የሚያደርገውን ፡ ማን ፡ ያውቃል ፡ አለው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ራስ ፡ አሊ ፡ አይሻል ፡ በሚባል ፡ ሜዳ ፡ ጦር ምን ፡ ሰርተው ፡ ተቀምጠው ፡ ሳሉ ፡ ደጃች ፡ ካሳም ፡ ድር ፡ ደሩን ፡ ይዘሩ ፡ ዠመሩ ፡ ሰውም ፡ የፍርሀት ፡ መስሎት ፡ ተመ ልሶ ፡ ሊሄድ ፡ ነው ፡ ይል ፡ ዠመረ ፡ ኋላ[2] ፡ ግን ፡ ገጠሙ ፡ በጧት ፡ የራስ ፡ አሊ ፡ ሰው ፡ ድል ፡ አደረገ ፡ የተማረከው ፡ ብዙ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃይሉን ፡ ለደ ጃች ፡ ካሳ ፡ ሰጥቶ ፡ የራስ ፡ አሊ ፡ መንግሥት ፡ አልቋልና ፡ ቢገጥሙ ፡ የራስ ፡ አሊ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ቅጠል ፡ ረገፈ ። የሰ ውም ፡ ሬሳ[3] ፡ ቢነባበር ፡ በአይሻል ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ከአውድማ ፡ የገባ ፡ ነዶ ፡ መሰለ ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ አጅግ ፡ ዝናም ፡ በረዶ ፡ ወረደ ። የተወጋ ፡ በነፍጥም ፡ የተመታ ፡ የሚያነሳው ፡ እያጣ ፡ በብርድ ፡ አለቀ ። እራስ ፡ አሊም ፡ ደምበጫ ፡ ደውለው ፡ ገቡ ፡ ከዚያም ፡ ሸሽተው ፡ ማኅደረ ፡ ማርያም ፡ ሌሊት ፡ ገቡ ። ከዚ ያም ፡ ዋድላ ፡ ወጥተው ፡ የነጃ ፡ ገቡ ፡ ደጃች ፡ ካሳም ፡ ቢከ ተሉ ፡ ወደ ፡ የጁ ፡ ወርደው ፡ ራያ ፡ ገብተው ፡ ተቀመጡ ፡ መን ግሥት ፡ መልቀቅዎ ፡ በሰኔ ፡ በ፳ወ፫ ቀን ፡ ነው ፡ ባመቱ ፡ ብሩ ፡

---

1 መጀማሯ ፡     2 ኋላም ፡     3 እሬሳ ፡



ጐሹ ፡ ተያዙ ። ከዚህ ፡ በኋለ ፡ እስከ ፡ ጊዜ ፡ ሞት ፡ አልተገና ኙም ። ይህን ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ በጌምድር ፡ ተመለሱ ፨ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከፍጥረተ ፡ ዓለም ፡ በ፯ ሺ ከ፫፻፵፯ ዓመት ፡ በዘመነ ፡ ሉቃስ ፡ ወታደር ፡ ስሜን ፡ ስሜን ፡ እነግርሀ ለሁ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ገሠገሱ[1] ። ደጃች ፡ ው ቤም ፡ የትግሬን ፡ ፵፬ነጋሪት ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ ስሜን ፡ ቧሂት ፡ ላይ ፡ ደረሱ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ቀኑ ፡ በመጋቢት ፡ በ፫ ቀን ፡ ዓርብ ፡ ማታ ፡ ሁኖ ፡ አለና ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡ አያሳድረኝ ፡ ይህን ፡ ቍርጥማታም ፡ አላሳድረው ፡ ብለው ፡ ፊት ፡ አውራሪውን[2] ፡ ገጠሙት ፡ ይኸው[3] ፡ ድል ፡ አደረገ ። በኋላ ፡ ግን ፡ የደጃች ፡ ካሳ ፡ ጦር ፡ ተመልሶ ፡ ገጠመ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለደጃች ፡ ካሳ ፡ ረድቶ ፡ አለና ፡ ሁሉም ፡ ድል ፡ ሆነ ፡ ደጃች ፡ ውቤም ፡ ተያዙ ። አቡነ ፡ ሰላማ ፡ ጳጳሱም ፡ እነአለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ በ፪ ልደት ፡ ሃይማኖት ፡ ከሸዋ ፡ ተሰደው ፡ የነበሩ ፡ ደረስጌ ፡ ከደብር ፡ ተገኙ ። የደጃች ፡ ውቤ ፡ በለሟል ፡ መኰ ንኑም ፡ እየሸሸ ፡ የገባው ፡ ብዙ ፡ ነው ። ደጃች ፡ ካሳም ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተማፀነውን ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ እግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ምሬዋለሁ ፡ ብለው ፡ አዋጅ ፡ ነገሩለት ፡ አደረ ። በማግስቱ ፡ የደጃች ፡ ውቤ ፡ ልጅ ፡ ጓንጕል ፡ አሰልፎ ፡ ነጋሪት ፡ እያስመታ ፡ ቢደርስ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ እንደታያዙ ፡ ሁሉም ፡ ድል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሰማ ፡ መካሪዎችም ፡ እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ እንመለስ ፡ እንጂ ፡ ወዴት ፡ እንሄዳለን ፡ ቢሉት ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ የተሸከምሁትን ፡ አረር ፡ ከዚህ[4] ፡ ሳላራግፈው ፡ አልመለስም ፡ ብሎ ፡ ገፍቶ ፡ መጣ ፡ ወደ ፡ ደጃች ፡ ካሳ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ገጠመ ፡ ድል ፡ ሆነና ፡

---

1 ገሠገሡ ፡     2 ፊታወራሪውን ፡     3 ይሀው     4 ከዜኅ ፡

ሸሽቶ፡ከአምባው፡ጠዘን፡ገብቶ፡ተቀመጠ። ደጃች፡ካሳም፡
ይህነን፡ ቢሰሙ፡ ደጃች፡ ውቤን፡ አስረው፡ በቁጣ፡ ቃል፡
ግንዘቤን፡የሚገባኝን[1]፡ሁሉ፡ አሁን፡ ለቅመህ፡ አምጣ፡
ቢሉ፡ደጃች፡ውቤ፡ደረሰኄ፡እግዝትነ፡ማርያምን፡እጅግ፡
ይወዱ፡ ነበርና፡ ገንዘብዎን፡ ወርቅና፡ ብር፡ በርሷ፡ ቤተ፡
ክርስቲያን፡ስራ[2]፡ጌጥ፡አስደርገውት፡ከባሕር፡ወዲህ፡እን
ድርሷ፡ድንቅ፡ተብሎ፡የሚነገር፡ስራ፡የለም፡በዚህ፡ጊዜ፡
እንዴህ፡አሉ፡ይህን፡ሁሉ፡ ግንዘቤን፡ለእግዝእትነ፡ማር
ያም፡መስጠቴ፡የምድርና፡የሰማይ፡መከራ፡እንዳታሳየኝ፡
ነበር፡አሁን፡እንዴት፡ላድርግ፡ክርሷ፡ይቀበሉ፡እንጂ[3]፡
አሉ። ይህነን፡ማለታቸው፡የድልቡን፡ግንዘብ፡ሁሉ፡ከአ
ምባው፡ከጠዘን፡ለመስጠት፡ታስረው፡በልጅዎ፡በጓንጉል፡
ፊት፡በቆሙ፡ጊዜ፡ልጅ፡ጓንጉል፡ያባቱን፡መታሰር፡ስለ
ግንዘብ፡ቢያይ፡ያባቱ፡መታሰር፡አሳዝኖት፡ከአምባው፡
የተቀመጠ፡ገንዘብ፡ተራዛሚው፡ነፍጥ፡ብቻ፡፳፱ ተቆጠረ፡
አረቂ፡ መርፌም፡ ፪ ጋን፡ ተገኘ፡ ይባላል፡ ይህን፡ ሁሉ፡
ከሰጡ፡በኋላ፡ነው። ከዚህ፡በኋላ፡ለትግሬ፡ደጃች፡አር
አያን፡ ጠባቂ፡ ሰጥተው፡ ባለህ፡ እርጋ፡ ብለው፡ አዋጅ፡
ነገሩ ፨ ። ከዚህ፡በኋላ፡ጳጳስ፡አቡነ፡ሰላማ፡
ከዚያው፡ተገኝተዋልና፡ሥርዓተ፡መንግሥት፡አድርሰው፡
ቀብዓ፡መንግሥት፡እንደ፡ሳሙኤል፡ቀብተው፡አነገሡዎ።
ስሜን፡ስሜን፡እነግርኃለሁ፡እንዳሉ፡ ስሜን፡ ቴዎድሮስ፡
በሉ፡አሉ። ከዚህ፡በኋላ፡ሰው፡ሁሉ፡ደጃች፡ካሳ፡ማለ
ትን፡እየተወ፡ንጉሥ፡ቴዎድሮስ፡ይል፡ዠመረ ፨ ።

[1] የገባኝም፡ [2] ሥራ፡ [3] manque



እንዲህ፡ አድርገው፡ ክረምቱን፡ አምባ፡ ጫራ፡ ከረሙ።
በዓመቱ[1]፡ወደ፡ሸዋ፡ሲመጡ፡ገረገራ፡ሰፍረው፡ትግሬ፡
ግብር፡ይዞ፡መጣ። በዚህ፡ጊዜ፡ከሳሽ፡በደጃች፡አርአያ፡
ቢነሳ፡ደጃች፡ካሳን፡የሰብአ፡ጋዲስን፡ለትግሬ፡ሹመው፡
ወደ፡ወሎ፡መጡ፡ወርቂት፡የምትባል፡እስላም፡ቤተ፡ክር
ስቲያን፡ስታቃጥል፡ገረገራ፡ተቃጥሎ፡ነበርና፡በዚህ፡ተና
ደው፡ቸኩለው፡ነበርና፡ወረህ፡ይመኑ፡ሲደርሱ፡በመዠ
መሪያ፡አሊ፡አደራ፡የሚባል፡ገብቶ፡ያባቱን፡አገር፡ተ
ሹሞ፡ሄደ። ከዚህም፡በኋላ፡በግዜር፡ድልድይ፡ተሻግ
ረው፡ወደ፡ወሎ፡ሲገቡ፡፯ ቤት፡ወሎ፡ሁሉ፡ግብሩን፡
እያየዘ፡ገባ፡አይዞህ፡ብለው፡ዓዋጅ[2]፡ነግረው፡ሳሉ፡
የወርቂት፡ሹም፡መቅደላ፡እንደተቀመጠ፡ቢሰሙ፡ገሥ
ግሰው፡ተመልሰው፡መቅደላን፡ሰብረው፡ዕቃውን፡ተቀ
ብለው፡ተመለሱ፡ጊምባ፡ላይ፡ሰፍረው፡፯ ቤት፡ወሎ፡
ተሰብስቦ፡አፄ፡ተክላ፡ጊዮርጊስ፡ቢመጡ፡መለስነ፡እራስ፡
አሊም፡እንዲህ፡ተመላሱ፡ዛሬ፡ይህ፡መጥቶ፡አገራቸ
ንን፡እንዴት፡ያልፋል፡ብሎ፡መከረ። መክሮም፡አል
ቀረ፡ውሎ፡ፈረሱ፡ብዙ፡ነውና፡በፈረስ፡ብዛት፡እናስ
ቀረዋለን፡መስሎት፡፬ ቀን፡ከበበ፡ለጐዞም፡አስቸገረ፡
ሰውም፡ከብትም፡እየነጠቀ። በዚህ፡ጊዜ፡ንጉሥ፡ቴዎ
ድሮስ፡ጊምባ፡ሰፍረው፡በመኻከሉ፡ሜዳ፡ሲጓዙ፡ግራ፡
ቀኙ፡ተራራ፡ነውና፡እንደ፡ወትሮ፡ልማዱ፡በፈረስ፡
እየሆነ፡መጣ። ይህን፡ጊዜ፡አፄ፡ቴዎድሮስ፡ፈረሰኛ፡
በየግምባሩ፡ቢለቁበት፡ካንድ፡ወገን፡፳ ካንድ፡ወገን፡

[1] አመቱ፡ [2] አዋጅ፡

፴ ሰው ፡ ተይዞ ፡ ቢመጣ ፡ የቀጣት ፡ መዠመሪያ[1] ፡ ፪ ት ፡ ፪ ት ፡ እጁን ፡ እየቈረጡ ፡ በየአንገቱ ፡ እያንጠለጠሉ ፡ ሰደዱት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ያየ ፡ ሁሉ ፡ እስላም ፡ አላህ ፡ ምን ፡ ጉድ ፡ አወረድህብን ፡ እያለ ፡ ደግመኛ ፡ ከፊትዎ ፡ አልደረሰም ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የወሎ ፡ እህል ፡ ሲበሉት ፡ ጨርቋ ፡ እሸትም ፡ ነበርና ፡ ሆድ ፡ እያመመ ፡ እጅግ ፡ ሰው ፡ ሞተ[2] ። ነገር ፡ ግን ፡ በክረስቶስ ፡ ፈቃድ ፡ በጥቅምት ፡ በ፯ ቀን ፡ ሸዋ ፡ ሲገቡ ፡ የግሼው ፡ ሹም ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡ ግራ ፡ ቀኙ ፡ ይባላል ፡ ከበሩ ፡ ላይ ፡ ጽኑ ፡ ውጊያ ፡ እየተመሰገነ ፡ ተዋጋ ፡ በኋላ ፡ ተያዘ ፡ ወንድሙ ፡ ግን ፡ ሞተ ፡ እነአቤቶ ፡ ሰሙ ፡ ንጉሥ ፡ ከግድም ፡ መጥተው ፡ ረድተው ፡ ነበሩ ፨ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ መንዝ ፡ ሲደርስ ፡ ጳጳስ ፡ ሰላማ ፡ በክህነት ፡ ንጉሥ ፡ በመንግሥት ፡ ሁነው ፡ ቢያያቸው ፡ የምሥራቁ ፡ የግድም ፡ የኤፍራታ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ እያለው ፡ አመነ ። ወዲያውም ፡ ዓዋጅ ፡ ነገሩለት ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ በየአባትህ ፡ ግባ ፡ ሰጥቼኻለሁ[3] ፡ አባት ፡ የሌለህ ፡ እኔን ፡ ደጅ ፡ ጥና ፡ አባትህ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ አሉ ፡ በዚህ ፡ ዓዋጅ ፡ የሸዋን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አሰኙት ። ነገር ፡ ግን ፡ ቴዎድሮስ ፡ ሸዋን ፡ በጦርነት ፡ ስለምን ፡ ደፈሩት ፡ ቢሉ ፡ ራጉኤል ፡ መልአክ ፡ ለአፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ የነገረዎ ፡ ራእይ[4] ፡ ቢደርስ ፡ ይመስላል ። ራእዩስ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ወፍቁረ ፡ ዑርኤል ፡ መልአክ ፡ ዘይትወለድ ፡ እምቤተ[5] ፡ ያ ፡ ንጉሥ ፡ ይኳንንዋ ፡ ለምድረ ፡ ሸዋ ፡ ፲ ወ ፺፱ እስከ ፡ ትውልድ ፡ ፯ ቱ ፡ ይላል ። ይህንንም ፡ ቄጥሮ ፡ ያዩዋል ፡ የነ

---

[1] መጀመሪ ፡ [2] አለቀ ፡ [3] ሰጥቺሀለሁ ፡ [4] ራዕይ ፡
[5] cinq mots gheez.



ጋሚ ፡ ፯ የአብዬ ፡ ፲፩ የሰብስቴ ፡ ስብስትያኖስ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ፷፭ አምኃ ፡ ኢየሱስ ፡ ፴፫ አስፋ ፡ ወሰን ፡ ፴፫ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ፩ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ፴፩ ኃይለ ፡ መለኮት ፡ ፰ ዓመት ፡ ጨምሮ ፡ ፲፻፺፱ ይሆናልና ፡ ስለዚህ ፡ መሰለ ። አፄ ፡ ቴዎድሮስም ፡ በሃይመኖት ፡ ምክንያት ፡ ጳጳስ ፡ ይዘው ፡ መጡ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድም ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ በጳጳሱ ፡ የፈረደለዎን ፡ ነገር ፡ ከዚህ ፡ ጥቂት ፡ እንናግራለን ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የመጡ ፡ ጳጳሳት ፡ ፲፯ ናቸው ፡ እስከ ፡ አቡነ ፡ ሰላማ ፡ እነዚህ ፡ ኍሉ ፡ የእስክንድርያ ፡ ሃይማኖት ፡ ፪ ልደት ፡ በተዋህዶ ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ እያሉ ፡ ከማርቆስ ፡ ወንበር ፡ ጀምረው ፡ መጡ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይጨምሩበትም ፡ ነበሩ ። የሸዋ ፡ ካህናት ፡ ግን ፡ ክርስቶስን ፡ በጸጋ ፡ ይወለዳል ፡ እያሉ ፡ የጸጋ ፡ ልጅ ፡ ሲሉት ፡ በሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘመን ፡ ክርክር ፡ ተዠምሮ ፡ ነገሩ ፡ ሳያልቅ ፡ ተነስተው ፡ ጐንደር ፡ ወረዱ ። አቡንም ፡ ጐንደር ፡ ገብርኤልን ፡ ከተከሉበት ፡ ቦታ ፡ ከቤትዎ ፡ ነበሩ ፡ እነዚያም ፡ ካህናት ፡ ከእቴጌ ፡ መነን ፡ ገብተው ፡ ነገራቸውን ፡ አጽንተው ፡ ወታደርም ፡ አስረድተው ፡ እየሰደቡ ፡ ወደ ፡ ጳጳሱ ፡ ቀረቡ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ውጊያ ፡ ተዠመረ ፡ እድሞውንም ፡ ባንካሴ ፡ በዶማ ፡ እየቈፈሩ ፡ አፈረሱ ፡ ጉልበትም ፡ በተሰጣቸው ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ደስታ ፡ አደረጉ ፡ ንሴብሖም[1] ፡ ተባለ ፡ እቴጌ ፡ መነንም ፡ በሸዎች ፡ ምክር ፡ ጳጳስ ፡ ባርያ ፡ ነው ፡ በወርቅ ፡ ተገዝቶ ፡ መጥቷልና ፡ ደግሞ ፡ ባርያ ፡ ጌታው ፡ እመቤቱ ፡ የወደዱትን ፡ ያዘዙት ፡ ይሰራል ፡ እንጂ[2] ፡ የርሱ ፡ ፈቃድ ፡ አይ

---

[1] gheez. [2] እንጅ ፡

ሆንም ፡ ሲሉ ፡ ሰምተው ፡ አቡነ ፡ ሰላማ ፡ እኔ ፡ ባርያ ፡ ሁ፫ ፡ ወርቅ ፡ የምትዩው ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ነው ፡ በሺ ፡ ብር ፡ ተገዛሁ ፡ አንቺስ ፡ ባገሬ ፡ ፲ ብር ፡ አታወጭም ፡ ብለው ፡ መለሱ ፧ ። እንዲህም ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ ከጐንደር ፡ ወጥተው ፡ ወደትግሬ ፡ የሃይማኖት ፡ ልጆችዎን ፡ አስከትለው ፡ እያዘኑ ፡ ሂደው ፡ ደብረ ፡ ዳሞ ፡ ገብተው ፡ ሲኖሩ ፡ አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ከደጃች ፡ ውቤ ፡ ሊዋጉ ፡ ስሜን ፡ ላይ ፡ ቢመጡ ፡ ጳጳስ ፡ የክርቲያን ፡ አባት ፡ ነውና ፡ አስታርቃለሁ ፡ ብለው ፡ መጡ ፡ ክርስቶስም ፡ ያዘዘው ፡ ሆነ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ተይዘው ፡ ቴዎድሮስን ፡ አንግሠው ፡ ክህነት ፡ ይሰጡ ፡ ዠመር ። ከዚህ ፡ ወዲህ ፡ ንጉሡ ፡ እንደ ፡ ሥርዓት ፡ ቍርበው ፡ ሠራዊትዎንም ፡ ያልቈረብህ ፡ እጠላኃለሁ ፡ ብለው ፡ ዓዋጅ ፡ ቢነግሩ ፡ ከሠራዊትም ፡ ከመኳንንትም ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ እግዚአብሔር ፡ የመረጣቸው ፡ እየተንኙ ፡ ቈረቡ ፡ የመንግሥትም ፡ ሥርዓት ፡ ወሬ ፡ በየሀገሩ ፡ ተነገረ ። አቡነ ፡ ሰላማም ፡ ይህን ፡ መንፈሳዊ ፡ ስራ ፡ ቢያዩ ፡ ንጉሡን ፡ እጅግ ፡ አክብረው ፡ ወደዱ ። ከዚህ ፡ ፍቅር ፡ የተነሣ ፡ የሃይማኖት ፡ ልጅ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰጠኝ ፡ ነህና ፡ ሸዋ ፡ እንሂድ ፡ ሃይማኖት ፡ እናቅና ፡ ብለው ፡ ስለዚህ ፡ ከንጉሡ ፡ ጋራ ፡ ተሰማምተው ፡ መጡ ። እግዚአብሔርም ፡ ፈታሒ ፡ በጽድቅ ፡ ኰናኒ ፡ በርትዕ[1] ፡ ነውና ፡ ጠላትዎን ፡ ሁሉ ፡ በእጅዎ ፡ ጣለው ፧ ። እንግዴህ ፡ ከጥንት ፡ ነገር ፡ እንመለስ ። ቴዎድሮስ ፡ በጥቅምት ፡ በ ፲፬ ቀን ፡ ጅብ ፡ ዋሻ ፡ ሲደርሱ ፡ አቶ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡ የጠራው ፡ ሲዋጉ ፡ ሞቱ ። ንጉሥ ፡ ኃይለ ፡ መለኮት ፡ ግን ፡

[1] cinq mots gheez.



ድብረ ፡ ብርሃን ፡ ነበሩ ፡ በተጕለት ፡ ቈላ ፡ ወደ ፡ ሰላ ፡ ድንጋይ ፡ ሄዱ ። ቴዎድሮስ ፡ ተመልሰው ፡ ቢገሠግሱ ፡ አልተገናኙም ፡ ተመልሰው ፡ መጡ ፡ በዚህ ፡ ወር ፡ በ ፲፯ ቀን ፡ ዓርብ ፡ የንጉሥ ፡ የኃይለ ፡ መለኮት ፡ ቅጥር ፡ አንኮበር ፡ በመኳንንት ፡ ምክር ፡ ተቃጠለ ፡ ቴዎድሮስም ፡ ወደ ፡ ኃይለ ፡ መለኮት ፡ ገሠገሱ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ቍንዲ ፡ ላይ ፡ ጳጳሱ ፡ ከንጉ ፡ ቀርተው ፡ ነበሩና ፡ የአንኮበር ፡ ካህናት ፡ ሁሉ ፡ ታቦታት ፡ ይዘው ፡ ወጥተው ፡ አቡንን ፡ እጅ ፡ ነስተው ፡ ተመለሱ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኃይለ ፡ መለኮት ፡ ታመው ፡ ነበርና ፡ የተከተለዎ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የመዋጋትን ፡ ነገር ፡ አላሰበም ፡ ከነገሡ ፡ በ ፷ ዓመት ፡ በኅዳር ፡ በ ፴ ቀን ፡ ዓርብ ፡ ሌሊት ፡ አረፉ ፡ በማግሥቱ ፡ አቡነ ፡ ሐፃን ፡ ሞዓ ፡ ደብር ፡ ደብረ ፡ በገዕ ፡ ተቀበሩ ፧ ። በዚህ ፡ ጊዜም ፡ የኃይለ ፡ መለኮት ፡ ልጅ ፡ ምን ፡ ይልክ[1] ፡ ሕፃን ፡ ነበሩና ፡ ወገኖችዎን ፡ ይዘው ፡ ገበሬ ፡ ሸንኅ ፡ ወጥተው ፡ ሰፈሩ ። ቴዎድሮስም ፡ እየተከተሉ ፡ መጡ ፡ ልጅ ፡ ምን ፡ ይልክም ፡ ከክርስቶስ ፡ ረድኤት ፡ ጋራ ፡ ከሰምን ፡ ተሻግረው ፡ ባባትዎ ፡ ሀገር ፡ እንደ ፡ ሌላ ፡ አረርቲ ፡ ሰፈሩ ፡ ከቴዎድሮስም ፡ ጋራ ፡ የቁር ፡ ሁነው ፡ በጭቃ ፡ ቍልቍለት ፡ ሲወርዱ ፡ በመነጽር ፡ ተያዩ ። ቴዎድሮስም ፡ ታቹን ፡ በቈላው ፡ ይቀድመኛል ፡ ሲሉ ፡ መከሩና ፡ ጦር ፡ ከፍለው ፡ እነራስ ፡ እንግዳን ፡ ወደ ፡ በረከት ፡ ሰደዱ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጭቃ ፡ በሚሉት ፡ ሀገር ፡ ወርደው ፡ ወደ ፡ ምንጃር ፡ ተሻገሩ ። ልጅ ፡ ምን ፡ ይልክም ፡ ከአረርቲ ፡ ተነስተው ፡ በምንጃር ፡ ቈላ ፡ ቈላውን ፡ ሂደው ፡ ከሰምን ፡ ተሻግረው ፡

[1] ምኒልክ ፡ orthographe plus usitée et officielle.

ወደ ፡ በረከት ፡ ሲወጡ ፡ ወሬ ፡ ተሰማ ። ይህን ፡ ጊዜ ፡ እነራስ ፡ እንግዳ ፡ ወርደው ፡ በኅዳር ፡ በ፲ ቀን ፡ ሰኞ ፡ ተዋጉ ፡ ቍጥር ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ ከራስ ፡ እንግዳ ፡ ወገን ፡ አለቀ ፡ ከወዲህም ፡ የታወቁ ፡ እነ ፡ አቶ ፡ ሸሸጉ ፡ አባ ፡ ወልደ ፡ መድኅን ፡ እየተዋጉ ፡ ሞቱ ። አቶ ፡ ብዛብኅ ፡ ግን ፡ ተወግቶ ፡ ድል ፡ ሲሆን ፡ ተያዘ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እነ ፡ አቶ ፡ ሀብቱ ፡ እነ ፡ አቶ ፡ ገብሩ ፡ ልጅ ፡ ምኒልክን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ተመለሱ ፡ ቦካን ፡ ሰፍረው ፡ ነበሩ ። አፄ ፡ ቴዎድሮስም ፡ ምን ፡ ይልክን ፡ እንደ ፡ ልጅ ፡ ወደው ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ አክብረው ፡ ከተቀበሉ ፡ በኋላ ፡ ሜዳውን ፡ በገርማማ ፡ መጥተው ፡ ሸኖ ፡ እስከ ፡ ኅልባ ፡ ሰፈሩ ፡ ከነራስ ፡ እንግዳም ፡ ተገናኙ ፡ ቴዎድሮስም ፡ በነራስ ፡ እንግዳ ፡ ጦርነት ፡ እየጠየቁ ፡ ደስ ፡ ብሎዎ ፡ ነበር ፡ የበጌ ፡ ምድር ፡ ጦር ፡ ብርቱ ፡ ይባላልና ፦ ። ያን ፡ ጊዜም ፡ በበረከት ፡ ድል ፡ ፯ እስላሞች ፡ ዕቃቸውን ፡ እንደ ፡ ተሸከሙ ፡ በድል ፡ ተቈርጠው ፡ ከወንዝ ፡ ተሸሽገው ፡ አንዱ ፡ ከራስ ፡ እንግዳ ፡ ወገን ፡ እንደነዚህ ፡ እስለሞች ፡ በድል ፡ ተቈርጦ ፡ ከሰዎቹ ፡ ተለይቶ ፡ ብቻውን ፡ ሲሄድ ፡ አገኛቸው ። ቢመለከታቸውም ፡ እንዳች ፡ የማያነሱ ፡ በጎች ፡ መሰሉት ፡ እርሱም ፡ ከዚህ ፡ ከያዛችሁት ፡ ፩፩ ሱሪ ፡ ስጡኝ ፡ ቢላቸው ፡ ፯ ቱም ፡ ሰጡት ። ደግሞ ፡ አያቸው ፡ ዝም ፡ ቢሉት ፡ ፩፩ ኩታ ፡ ድገሙኝ ፡ አለ ፡ ሰጡት ። ፫ ተኛም ፡ አያቸው ፡ ፈርተውታልና ፡ ዝም ፡ አሉ ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ እኒህስ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰጠኝ ፡ ግቦ ፡ ከብቶቼ ፡ ናቸው ፡ አለና ፡ እንደ ፡ ተሸከማችሁ ፡ ተነሱ [1] ፡ ቢላቸው ፡ ሁሉም ፡ ተነሱ ፡ እርሱም ፡

[1] ተነሡ ፡



አስቀድሞ ፡ እንደ ፡ ከብት ፡ እየነዳ ፡ ከሰፈሩ ፡ አደረሳቸው ፦ ። ከዚህ ፡ ወዲህ ፡ ደብረ ፡ ሊበኖስ ፡ ወርደው ፡ ሲመለሱ ፡ ጠባሴ ፡ ኮሶ ፡ ሰፈሩ ፡ ከዚህም ፡ ተነስተው ፡ ሞጣጢት ፡ ሰፈሩ ። የአንኮበርም ፡ ካህናት ፡ ሁሉ ፡ ተቦታቱን ፡ እንደ ፡ ፊተኛው ፡ ይዘው ፡ መጥተው ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ሲቀርቡ ፡ እስመ ፡ ጽጽቅ ፡ ቃሉ ፡ ለቴዎድሮስ ፡ ወኵሉ ፡ ገብሩ ፡ በሃይማኖት [1] ፡ እያሉ ፡ በወረብ ፡ እጅ ፡ ነስተው ፡ ተመለሱ ። ይህ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ የአንኮበርን ፡ ከተማ ፡ ሊያዩ ፡ መጡ ፡ በላይኛው ፡ መሻገሪ ፡ ንገመድ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሰፈር ፡ በጐረቤላ ፡ በጨፋ ፡ ሜዳውን ፡ መልቶ ፡ ነበረ ፡ ጳጳሱም ፡ አቡነ ፡ ሰላማ ፡ ከቅጽሩ ፡ ውስት ፡ ሙቅ ፡ ምድር ፡ ንጉሡ ፡ ከተቃጠለው ፡ ላይ ፡ ሰገነት ፡ ከነበረው ፡ ተቀመጡ ። የከተማውን ፡ ሥርዓት ፡ እይተው ፡ አልዘረፉትም ፡ ጥቂት ፡ ቀንም ፡ ሰነበቱ ፦ ። እንዲህም ፡ ሳሉ ፡ ፪ ሰዎች ፡ ተነስተው ፡ በሌሊት ፡ እየዞሩ ፡ ይህ ፡ ንጉሥ ፡ የሚሄድበት ፡ አይታወቅ [2] ፡ ከዕባብ ፡ ሀገር ፡ ይወስድኃል ፡ ወታደር ፡ የተከተልኸው ፡ ሁሉ ፡ በአቡነ ፡ ሰላማ ፡ ቃል ፡ ገዝተናል ፡ እያሉ ፡ ሲዞሩ ፡ ተያዙ ። እነዚያም ፡ የታወቁ ፡ ሰዎች ፡ ከሰፈራቸው ፡ አብረው ፡ የመከሩ ፡ ፵፭ ሰዎች ፡ ተያዙ ። ንጉሡም ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ተናደው ፡ ወጥተው ፡ ቶራ ፡ መስክ ፡ ሰፈሩ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እሊህን ፡ የተያዙ ፡ ሰዎች ፡ አምጥተው ፡ ከአደባባይ ፡ ግንድ ፡ አስተክለው ፡ ፳ ቱን ፡ ሰው ፡ ባንዱ ፡ ፲ ሩን ፡ ባንዱ ፡ እያሰሩ ፡ በነፍጥ ፡ በጐራዴ ፡ ደብድቡ ፡ ሲሉ ፡ አቡነ ፡ ሰላማ ፡ እንዲህ ፡ አሉ ፡ እሊህ ፡ ሰዎች ፡ ክህነት ፡ ቅስና ፡ ሳይኖራቸው ፡ ገዝተ

[1] gheez. [2] አይታውቅም ፡

ናል ፡ አሉ ፡ ለኔ ፡ ስጠኸና ፡ በመንፈሳዊ ፡ ቅጣት ፡ ልቅጣ
ቸው ፡ አንተም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሰጠህ ፡ ትገዛለህ ፡
ቢሉ ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ እጅግ ፡ ተናደዋልና ፡ አይሆን
ልኝም ፡ አልተውም ፡ አሉ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወታደር ፡ እየ
ተሰለፈ ፡ ቁሞ ፡ ነበርና ፡ እነዚያን ፡ ሁሉ ፡ ደብድቦ ፡ ጨ
ረሰ ፥

። ይህንም ፡ ያየ ፡ የሸዋ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እ
ጅግ ፡ ፈራ ፡ ተንቀጠቀጠ ፡ የንጉሥ ፡ ዓመፀኛ ፡ ቢሞት ፡ ስለ ፡
ምን ፡ ቢሉ ፡ ከነጋሜ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ንጉሥ ፡ ኃይለ ፡ መ
ለኮት ፡ ፰ ትውልድ ፡ የበደላቸው ፡ ያስሩታል ፡ ይወርሱታል ፡
ዓመፀኛ ፡ ነፍሰ ፡ ገዳይም ፡ ቢገኝ ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ አስ
ፈርደው ፡ ይገድሉታል ፡ እንጂ ፡ እንደነዚህ ፡ የሆነ ፡ ሞት ፡
ታይቶ ፡ አያውቅምና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ። ይህን ፡ አድርገው ፡
ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ወርደው ፡ ሲሰነበቱ ፡ ከበሬሳ ፡ ወንዝ ፡ ከባ
ሕሩ ፡ ዋናተኛ ፡ እየገባ ፡ ብዙ ፡ ነፍጥ ፡ መርውጥም ፡ አወጡ ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በየካቲት ፡ በ ፲፱ ቀን ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡
አስኘተው ፡ የሣህለ ፡ ሥላሴን ፡ ልጅ ፡ ኃይለ ፡ ሚካኤልን ፡ ሹ
መው ፡ ላቶ ፡ አንዳርጋቸው ፡ አበጋዝነት ፡ ሰጥተው ፡ ጠባሴ ፡
ኮሶ ፡ ወርደው ፡ ሰፈሩ ፡ ከሸዋም ፡ ሰዎች ፡ እነ ፡ አቤቶ ፡ ና
ደው ፡ የታመኑ ፡ የተመረጡ ፡ ምን ፡ ይልክን ፡ ለመከተል ፡
አልተለዩም ፥

። በዚህም ፡ ላይ ፡ ዓዋጅ ፡ ነገሩ ፡ እን
ዴት ፡ ቢሉ ፡ በመዠመሪያ ፡ ሸዋ ፡ ሲገቡ ፡ አባት ፡ ያለህ ፡ ያ
ባትህን ፡ ሰጥቼኃለሁ ፡ ያባት ፡ የሌለህ ፡ እኔን ፡ ደጅ ፡ ጥና ፡
አባትህ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ እያሉ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ አሰኝተ
ውት ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ አገሬን ፡ አባቴን ፡ የማይል ፡
የለምና ፡ የንጉሥ ፡ ዓዋጅ ፡ ነው ፡ እያለ ፡ በየሹመቱ ፡ በየመ
ሬቱ ፡ እገባለሁ ፡ እያለ ፡ ሲጠላ ፡ እየተዋጋ ፡ ሰው ፡ ያልቅ ፡



ዠመረ ። ይህን ፡ ሰምተው ፡ የሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ሥርዓት ፡ ይ
ርጋ ፡ እንደ ፡ ልማዱ[1] ፡ ይሁን ፡ ብለው ፡ ዓዋጅ ፡ መለሱ ።
ነገር ፡ ግን ፡ ሸዋ ፡ ነፍስ ፡ ገዳዩ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ያው ፡ ገዳዩ ፡ ይ
ሙት ፡ እንጂ ፡ ሌላው ፡ ዘመዱ ፡ ካልመከረ ፡ ከጠቡም ፡ ላይ ፡
ካልነበረ ፡ በቀር ፡ አባቱ ፡ ነው ፡ ወንድሙ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡
አይሙት ፡ ብለው ፡ ሥርዓት ፡ አደረጉ ፥

።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከጠባሴ ፡ ኮሶ ፡ ተነስተው[2] ፡ ሳላይሽ ፡ ሰ
ፈሩ ፡ ከዚህ ፡ ተነስተው[2] ፡ በዋዩ ፡ ወርደው ፡ ጅሩ ፡ አ
ፋፍ ፡ ወርደው ፡ ሰፈሩ ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ በመርሀ ፡ ቤቴ[3] ፡
ይሔዳሉ ፡ ሲባል ፡ ተመልሰው ፡ በገላን ፡ ሲጓዙ ፡ ጋላውን ፡
እየዘረፉ ፡ በደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ደጋ ፡ አልፈው ፡ በውላ ፡
ውሞ ፡ ወርደው ፡ ጀርሶ ፡ ከቈላው ፡ ሰፈሩ ፡ ሠራዊትም ፡
በውሀ ፡ ቸግሮት ፡ አደረ ። በማግሥቱ[4] ፡ የዓባይ ፡ ውሀ ፡
እየታየ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከንፍ ፡ ተመኘ ፡ ቶሎ ፡ ለመድረስ ፡
ቀኑም ፡ ረቡዕ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ መንገዱ ፡ ዱር ፡ ጠ
ባብ ፡ ነበርና ፡ በብዙ ፡ ጭንቅ ፡ ሲደርሱ ፡ በውሀ ፡ ጥም ፡
ሰው ፡ ይሞት ፡ ዠመረ ። ይልቁንም ፡ ውሀውን ፡ ባገኘ ፡
ጊዜ ፡ እንደ ፡ ከብት ፡ እየገባ ፡ ሲጠጣ ፡ እየወጣ ፡ ከዳር ፡
ሲሞት ፡ ቢያዩ ፡ አስከለከሉት ፡ ንጉሡ ። አባ ፡ ወልደ ፡ ሥ
ላሴም ፡ ታስረው ፡ የሄዱት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ቀሩ ፡ ጋላም ፡ ገደላ
ቸው ፡ ተባለ ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የወሀውን ፡ መሻገሪያ ፡ ላይና ፡
ታች ፡ ፪ መልካ ፡ ተገኘና ፡ ባንገት ፡ በወገብ ፡ እየሆነ ፡ ሰውም ፡
አህያም ፡ እየነጠቀ ፡ እየወሰደ ፡ ተሻገረ ። ንጉሡ ፡ ግን ፡ ተሻ

---

[1] ልማድ ፡ [2] ተነሥተው ፡ [3] በመርሐ ፡ ቢቴ ፡
[4] በማግስቱ ፡

ግረው ፡ የወዲሁን ፡ እስኪሻገር ፡ ከኋላም ፡ ጋላ ፡ እንዳይሰ
ርቅ ፡ መነጽር ፡ ይዘው ፡ እያዩ ፡ ይጠብቁት[1] ፡ ነበር ። በዚህም ፡
ላይ ፡ መሸቷልና ፡ ከወሀው ፡ ዳር ፡ አድረው ፡ በመግሥቱ ፡ ዓ
ቀበቱን ፡ ወጥተው ፡ የገወራ ፡ ሰፈሩ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የጐጃም ፡
ከህናት ፡ ከየደብሩ ፡ መጥተው ፡ ጽልመተ ፡ ታበርህ ፡ ዘአስ
ተዓፀቡ ፡ ታቀልል ፡ መኑ ፡ ከማከ ፡ ሰላማ ፡ አልቦ ፡ ዘይሰአ
ነከ[2] ፡ እያሉ ፡ በከበሮ ፡ በጸናጽል ፡ ሲያመሰግኑ ፡ ከጳጳሱ ፡ ቡ
ራኬ ፡ ተቀብለው ፡ ተመለሱ ፨ ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡
ሸዋ ፡ አንኮበር ፡ ላይ ፡ ሲገዝቱ ፡ ተይዘው ፡ የነበሩ ፡ ወታደ
ሮች ፡ ሀገራቸው ፡ ጐጃም ፡ ነውና ፡ ዘመዳቸው ፡ እንዲያይ ፡
፪ ቱን ፡ ሰቀሏቸው ፡ እጅ ፡ እግራቸውን ፡ እየቈረጡ ፨ ።
ይህን ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ በናዝሬት ፡ ወጥተው ፡ ፬ መከራ
ክር ፡ ሰፈሩ ፡ በዙሪያውም ፡ ያሉ ፡ ሀገሮች ፡ እነእርባብ[3] ፡ ተ
ዘረፉ ። የዚህም ፡ ዘመኑ ፡ ዮሐንስ ፡ ነው ፡ ወርኁም ፡ መጋ
ቢት ፡ የሁዳዴ ፡ ጾም ፡ ነበርና ፡ ከዚያው ፡ ተቀመጡ ፡ በሕ
ማማት ፡ ሰኞ ፡ ተነሱ ። ሲነሱም ፡ ቢት ፡ ውደድ ፡ ውቤ ፡ ኋላ ፡
ራስ ፡ የተባሉትን ፡ ራስ ፡ እንግዳን ፡ ለጐጃም ፡ ሹመው ፡ ዓ
ዋጅ ፡ ነገሩ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ፊት ፡ ወራሪ ፡ ቸኰል ፡ ተይዘ ፡
እነራስ ፡ እንግዳ ፡ የምስራች ፡ ላኩ ። ንጉሡ ፡ ሰምተው ፡
ባሶ ፡ ገቢያ ፡ ስቀሉት ፡ ብለው ፡ ተሰቀለ ፨ ። ከዚ
ህም ፡ ተጕዘው ፡ አመዳሚት ፡ ላይ ፡ ፋሲካን ፡ ውለው ፡ አ
በላ ፡ ንጉሥ ፡ ከሚባለው ፡ ቢሰፍሩ ፡ ድንቅ ፡ ተደነቀ ። ስለ
ምን ፡ ቢሉ ፡ ጅብ ፡ ስንኳን ፡ ከጉሬው ፡ ሂደውለት ፡ እየፈ
ለገ ፡ ሂዶ ፡ ያገኘውን ፡ ይበላል ። አበላ ፡ ማለት ፡ ንጉሥ ፡

---

[1] ይጠብቁ ፡ [2] neuf mots gheez. [3] እነዕርባብ ፡



የቡዳ ፡ ሁሉ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ቡዳ ፡ ገደለው ፡
ሲገል ፡ ያው ፡ የበላው ፡ በዕፁ ፡ እያስነሳ ፡ እየወሰደ ፡ ግብር ፡
ይሰጠዋል ፡ እርሱም ፡ ተቀብሎ ፡ እንደ ፡ ግድግዳ ፡ ገድግዶ ፡
እንደ ፡ ማገር ፡ ማግሮ ፡ አቁሞት ፡ ይኖራል ፡ ይባላል ። ይ
ህስ ፡ በምን ፡ ታወቀ ፡ ቢሉ ፡ ፩ ድኃ ፡ የቡዳ ፡ ወዳጅ ፡ አለው ፡
የንብረት ፡ ማደሪያ ፡ ቢቸግረው ፡ እንዴት ፡ ልሁን ፡ ምክር ፡
መጽውተኝ ፡ ቢለው ፡ ምሥጢሩን ፡ ሁሉ ፡ ነገረውና ፡ ና ፡
ልውሰድህ ፡ ከአበላ ፡ ከንጉሣችን ፡ ለርሱም ፡ ሎሌ ፡ እንደኔ ፡
ትሆናለህ ፡ ብሎ ፡ ወሰደው ። በገባም ፡ ጊዜ ፡ በብርሌ ፡ በብ
ርጭቆ ፡ መድኃኒቱን ፡ እየቀዳ ፡ ተራውን ፡ አስቀምጦ ፡ አገ
ኘው ። ከዚያም ፡ አንዱን ፡ ጠጣው ፡ አለው ፡ በጠጣው ፡
ጊዜ ፡ የመንገድ ፡ ደንጊያ ፡ ሆነ ፡ በመንገድም ፡ ተቀምጦ ፡
እንቅፋት ፡ ሁኖ ፡ መንገደኛ ፡ ቢመጣ ፡ መድኃኒቱን ፡ እያደ
ረገ ፡ ከወጥመዱ ፡ ሳይገባለት ፡ ቀረ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ አንዱ ፡
ከሚስቱ ፡ ተጣልቶ ፡ ምሳውን ፡ ሳይበላ ፡ በነገሩ ፡ እየተናደደ ፡
መጣ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ እግሩን ፡ ቢመታው ፡ ጣቱ ፡ ለብቻው ፡
ሁኖ ፡ ጥፍሩ ፡ ተለይቶ ፡ ወደቀ ፡ እርሱም ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡
ልብ ፡ አደረገና ፡ እንቅፋት ፡ ቡዳ ፡ ነው ፡ ተመልክቶ ፡ ተመ
ልክቶ ፡ አንደጊዜ ፡ ብቻ ፡ ቢመቱት ፡ መፍትሔው ፡ ነው ፡
ሲሉ ፡ ሰምቷል ፡ ተመልሶ ፡ ቢመታው ፡ በደንጊያ ፡ ጥርሱ ፡
ሁሉ ፡ ረገፈ ። ያም ፡ ሰው ፡ እንግዴህ ፡ የቡዳ ፡ ንብረት ፡ ምን ፡
ሊሆነኝ ፡ እያለ ፡ ለሰው ፡ ሲናገር ፡ ይህነን ፡ ምሥጢሩን ፡ አ
ይቶ ፡ ተናግሮታልና ፡ ይህነን ፡ ሲያውቁ ፡ በታሪክ ፡ ቴዎድ
ሮስ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ቢሰፍሩ ፡ ተደነቀ ። ሰውም ፡ ከሠራዊ
ትዎ ፡ ቡዳ ፡ ነካው ፡ አልተባለም ፨ ። ከዚህ ፡
ተነስተው ፡ ደብረ ፡ መዊዕ ፡ ሰፍረው ፡ ውለው ፡ አደሩ ።

ከዚህ፡በኋላ፡ተሰማ፡ጐሹ፡የሚባል፡ሽፍታ፡ከጮቄው፡
ላይ፡መኖሩን፡ሰምተው፡ቢገሠገሡ፡አልተገኘም፡ተመ
ልሰው፡ወርደው፡ባሕር፡ዳር፡ሰፈሩ። ከዚህም፡ሲሰነ
ብቱ፡ነፍጠኛ፡የሚባል፡በሽታ፡በጧት፡እየጀመረ፡እ
ስከ፡ረፋድ፡እየታመመ፡ብዙ፡ሰው፡አለቀ፡እጅግም፡
ጭንቅ፡ሆነ፡እግዚአብሔር፡በሰው፡መዓቱን፡ልኳልና፡
ከዚህም፡ጭንቅ፡የተነሣ፡ንጉሡ፡ተነስተው፡ዓባይን፡
እግር፡በር፡በሚባለው፡ተሻገሩ። ሲጓዙም፡የታመመው፡
ከፈረስ፡ከበቅሎ፡እየወደቀ፡ይቀር፡ነበረ። በጌምድር፡
ሲገቡ፡ግን፡ነፍጠኛው፡በሽታ፡በክርስቶስ፡ቸርነት፡ለ
ቋቸው፡ጐንደር፡ሲገቡ፡ሥራዊቱ፡በተሰሪ፡ከረመ⁘ ።
በመስከረም፡ለመስቀል፡ደብረ፡ታቦር፡ወጥተው፡ወታደ
ርም፡ከየቤቱ፡ተሰበሰበ። በዚህ፡ጊዜ፡የግብጽ፡ሊቀ፡
ጳጳስ፡አቡነ፡ቄርሎስ፡መጥተው፡ገቡ። የመጡበት፡ም
ክንያት፡ለጵፈት፡እንዳይበዛ፡ቀርቷል⁘ ።ከዚህ፡
በኋላ፡ወደ፡ወረህ፡ይመኑ፡ጅፋ፡ወጥተው፡ጋላ፡ያፈረ
ሰውን፡አድሰው፡ታቦት፡መድኃኒ፡ዓለምን፡መቅደላ፡
እግዝእትነ፡ማርያምን፡አስገብተው፡ካህናት፡ሰርተው፡
መቅደላን፡እጅግ፡ወደዱ፡በውስጡም፡ግራ፡አዝማች፡
ዓለሜን፡አፈ፡ንጉሥ፡ወርቄን፡ሾሙ። በዚህ፡ጊዜ፡ጳ
ጳስ፡አቡነ፡ሰላማ፡ሊቀ፡ጳጳስ፡አቡነ፡ቄርሎስ፡አብረው፡
እነዚህ፡ታቦቶች፡ሲገቡ፡በሊቀ፡ጳጳስ፡በጳጳስ፡ቡራኬ፡
ሲደረግ፡የዚያ፡ጊዜ፡ደስታ፡በመቼም፡አልተገኘ። መቅ
ደላም፡የንጉሥ፡የዕቃ፡ቤት፡ሆነ፡ዓዋጅም፡ሲነግሩ፡ዕ
ቃዬም፡መቅደላ፡ይግባ፡የወደደኝም፡ሁሉ፡መቅደላ፡
ይቀመጥ፡አሉ፡የታመነ፡ቦታም፡ስለ፡ሆነ፡ሰውም፡በወ



ንጀሉ፡ሲታሰር፡መቅደላ፡ይግባ፡ብለው፡ነበር⁘ ።
ከዚህ፡በኋላ፡ወደ፡ቤጌ፡ምድር፡ተመልሰው፡ግብር፡
እየተቀበሉ፡ሽፍታም፡እየሸሸ፡ይቀመጡ፡ዠመር፡ከዚ
ህም[1]፡ጊዜ፡ወንበዴ፡ከዱር፡ሌባ፡ከመንደር፡አልተገ
ኘም[2]፡ቅጣቱ፡እጅግ፡ጥኑ፡ስለ፡ሆነ። ፩ ቀንም፡ወደ፡
ንጉሡ፡ቲዝባ፡የሚባል፡ሀገር፡ሊጮህ፡ተሰብስቦ፡መጣ፡
ምነው፡ቢሉት፡ጃንሆይ፡እየአባትህ፡ብለው፡ለድኃዎ፡
ዓዋጅ፡ከነገሩለት፡እኛም፡ያባት[3]፡አለን፡ሌሊት፡ገስግ
ሰን፡በረት፡ከፍተን፡ላም፡ነድተን፡ሰው፡ሲተኛ፡ግድ
ግዳ፡ምሰን፡ያገኘነውን፡ወስደን፡እንኖራለን፡አሉ። ንጉ
ሡም፡በጥበብ፡እናንተ፡አሁን፡ጥቂቶች፡ናችሁና፡ሁላ
ችሁም፡አንድ፡ሁናችሁ፡ንገሩኝ፡ብለው፡ቀን፡ለክተው፡
ሰደዱዋቸው፡ደስ፡እያላቸው፡ተመለሱ። ከዚህ፡በኋላ፡
ቀን፡ሲደርስ፡አምባ፡ይፈርስ፡እንዲሉ፡ጎበዙ፡ሽማግ
ሌው፡ሳይቀር፡ተሰብስቦ፡መጣ፡እንደፊተኛው፡ቃል፡ን
ገሩኝ፡አሏቸው፡እየሳቁ፡ነገሩንም፡ተናግረው፡በጨረሱ፡
ጊዜ፡ንጉሡ፡እኔ፡የምሰጣችሁ፡ያባታችሁ[4]፡ይህ፡ነው፡
ብለው፡ከልብዎ፡የሞት፡ቃል፡ሲወጣ፡በዙሪያው[5]፡የ
ቆመ፡ወታደር፡ያነን፡የተሰበሰበ፡ባላገር፡እንደ፡ዘረፋ፡
በግ፡እየተሻማ፡በነፍጥ፡በጎራዴ፡በጦርም፡ተካፍሎ፡
ጨረሰው። ከዚህም፡ወዲህ፡ዋዛ፡የሚመስል፡ነገር፡በን
ጉሡ፡ፊት፡የሚናገር፡አልነበረም። ብላታ፡በቀቱም፡የ
ሚባሉ፡ጨወታ፡የሚያውቁ፡ነበሩ፡አፄ፡ቴዎድሮስም፡

---

[1] ከዚህ፡ [2] ጠፋ፡ [3] ያባታችን፡ [4] የአባታችሁ፡
[5] ዙሪው፡

ብላታ ፡ በቀቱ ፡ ጨወታ ፡ ታውቃለህ ፡ አሉኝ ፡ እስኪ ፡ አጫ
ውተኝ ፡ ቢሉ ፡ ጃንሆይ ፡ በዋዘው ፡ ጊዜ ፡ አውቅ ፡ ነበር ፡
ዛሬስ ፡ ረስቼዋለሁ ፡ አሉ ፡ ይህም ፡ የፍርሀት ፡ ጥበብ ፡ ይመ
ስላል ፨ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሸዋ ፡ የንጉሥ ፡ የሣ
ህለ ፡ ሥላሴ ፡ ልጅ ፡ አቤቶ ፡ ሰይፉ ፡ ተነሥተው ፡ ከሸዋ ፡
ምሥራቁን ፡ ሁሉ ፡ ይዘው ፡ አንኮበር ፡ ገቡ ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡
አቶ ፡ በዛብህ ፡ ደጋ ፡ ደጋውን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡
ላከ ፡ ምክራችን ፡ ዛሬ ፡ ይከተታል ፡ ሲል ። ንጉሡም ፡ ከበጌ ፡
ምድር ፡ ተነሥተው ፡ ሲገሠግሡ ፡ መጥተው ፡ በአንኮበር ፡ በ
ላይ ፡ ጐረቤላ ፡ ሲሰፍሩ ፡ አቶ ፡ በዛብህ ፡ የደጋውን ፡ ጦር ፡
ይዞ ፡ በከተማው ፡ አጠገብ ፡ በጨፉ ፡ እስከ ፡ ውሀው ፡ መጣ ፡
ይህን ፡ ጊዜ ፡ አቤቶ ፡ ሰይፉ ፡ ከቅጽሩ ፡ ውስጥ ፡ ሙቅ ፡ ም
ድር ፡ ከሚባለው ፡ ነፍጠኛዎን ፡ ይዘው ፡ ጦርነት ፡ ዠመሩ ፡
ወደ ፡ ንጉሡ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በሚካኤል ፡ አራዳ ፡ ዓቀበቱ ፡
ላይ ፡ በታችኛው ፡ ነፍጥ ፡ እጅግ ፡ ሰው ፡ አለቀ ፡ ድል ፡ እስ
ኪሆን ፡ ድረስ ። ነገር ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ላይ ፡ ፩ ሰው ፡ ከን
ጉሡ ፡ ተማርኮ ፡ ወደ ፡ አቤቶ ፡ ሰይፉ ፡ ገባ ፡ ቢጠይቁት ፡ ን
ጉሡ ፡ ጀንሆይ ፡ መጥተዋል ፡ አለ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ጠየቁት ፡
ቢሉ ፡ አቶ ፡ በዛብህ ፡ ለአቤቶ ፡ በይፉ ፡ የሆነውን ፡ አገር ፡
ይዘርፈው ፡ ያቃጥለው ፡ ነበርና ፡ በዚህ ፡ ልማድ ፡ አቤቶ ፡
ሰይፉ ፡ ሊዋጋኝ ፡ መጣ ፡ ብለዋል ፡ እንጂ ፡ አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡
መሆንዎን ፡ አላወቁም ፡ ነበርና ፡ ስለዚህ ፡ ጠየቁት ። የዚ
ያም ፡ ቀን ፡ ይህ ፡ የተማረከው ፡ የንጉሡ ፡ ወገን ፡ ወሬ ፡ ባይ
ነግር ፡ የመጣው ፡ ጦር ፡ ለዘር ፡ ባልተመለሰም ፡ ነበር ፡ ንጉ
ሡም ፡ የዚህን ፡ ጦርነት ፡ በአቤቶ ፡ ሰይፉ ፡ ቢያዩ ፡ እንደነ
ዚህ ፡ ያሉት ፡ በፊት ፡ ተገኝተው ፡ ቢሆን ፡ ሸዋን ፡ አላያትም ፡



ነበር ፡ የወታደርም ፡ ሚያ ፡ በአንኮበር ፡ ብቻ ፡ ይቈጠር ፡ አሉ ።
ነገር ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ አልቀረምና ፡ አቤቶ ፡
ሰይፉ ፡ የቴዎድሮስን፡ ወሬ ፡ ሲሰሙ ፡ እንግዴህስ ፡ ሰዌን ፡
አልጨርስም ፡ ብለው ፡ ከተማውን ፡ ለቀው ፡ ወደ ፡ ታች ፡
ወረዱ ። ይህን ፡ ጊዜ ፡ የንጉሡ ፡ ጦር ፡ በከተማው ፡ ገብቶ ፡
በየቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የገባውን ፡ ሰው ፡ እየገደለ ፡ ዕቃውን ፡
ሁሉ ፡ ዘረፈ ። ይህ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ምርኮኛ ፡ የያዝህ ፡
አምጣ ፡ ብለው ፡ ዓዋጅ ፡ ነገሩ ፡ እየተሰበሰበ ፡ በመጣ ፡
ጊዜ ፡ አቶ ፡ በዛብህ[1] ፡ ተነስቶ ፡ ይህ ፡ የከዳ ፡ ይህ ፡ የኛ ፡ ነው ፡
እያለ ፡ በ ፪ ወገን ፡ አቆመ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ባለ ፡ ወግ ፡ እየ
ተጠራ ፡ መጥቶ ፡ ያነን ፡ የከዳ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ቀኝ ፡ እጁን ፡
ግራ ፡ እግሩን ፡ እየቈረጠ ፡ ጨረሰ ። ይህን ፡ ጊዜ ፡ አስ
ለቃሽ ፡

አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ እጅግ ፡ ተዋረዱ ፡

የሸዋን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እጅ ፡ ነሥተውት ፡ ሄዱ ፡

አለች ። ይህን ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ በጌ ፡ ምድር ፡ ተመ
ለሱ ፡ ይህም ፡ የተቈረጠው ፡ ከሞተው ፡ በቀር ፡ ፳፪ ከንጉሡ ፡
ወገን ፡ በጦርነት ፡ በመንገድም ፡ በማናቸውም ፡ የሞተ ፡ ሺከ
፺፪ ሆን ፡ በአቤቶ ፡ ሰይፉ ፡ ጊዜ ፨ ። በዚህ ፡ ዘመን ፡
መቅደላ ፡ ገብተው ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ሰነበቱ ፡ ወደ ፡ በጌ ፡ ምድ
ርም ፡ ወርደው ፡ ተቀምጠው ፡ ሲኖሩ ፡ ወይዘሮ ፡ ተዋበች ፡
ሚስትዎ ፡ ታመሙ ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ከበጌ ፡ ምድር ፡ ተነስ
ተው ፡ ወደ ፡ ወረህ ፡ ይመኑ ፡ ወጥተው ፡ ደረቅ ፡ ወይራ ፡ ሂ
ደው ፡ ሲሰፍሩ ፡ እቴጌ ፡ ተዋበች ፡ አረፉ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በ

[1] በዛብኅ ፡

ሣፅን ፡ አድርገው ፡ በአልጋ ፡ ወደ ፡ ግሸን ፡ ለመቃብር ፡ ሲያ
ጉዙ ፡ ንጉሡ ፡ እንዲህ ፡ አለቀሱ ፡

እስቲ ፡ ጠይቁልኝ ፡ ርቃ ፡ ሳትሄድ ፡
እቴጌ ፡ ተዋበች ፡ ሚስትናት ፡ ገረድ ፡
እጅግ ፡ ስር ፡ አዋቂ ፡ ትላንትና ፡ ሞተች ፡
መድኃኒቱን ፡ ምሳ ፡ ታበላኝ ፡ ነበረች ፡

አሉ ። ራስ ፡ አሊም ፡ የይተጌ ፡ ተዋበች ፡ አባት ፡ ወደየጁ ፡
ቄላ ፡ ተሰደው ፡ ይኖሩ ፡ ነበርና ፡ ይህንን ፡ የልጅዎን ፡ ሞት ፡
ሰምተው ፡

ጠጅ ፡ አማረኝ ፡ ስላት ፡ ማሩን ፡ ታስጭናለች ፡
ራበኝም ፡ ስላት ፡ እህሉን ፡ ታስጭናለች ፡
በረደኝም ፡ ስላት ፡ ሸማ ፡ ትሰዳለች ፡
ሌባዬ ፡ ተይዛ ፡ ባልጋ ፡ ትሄዳለች ፡
የት ፡ አባቷን ፡ አውቃ ፡ ታሳዝነኛለች ፡

ብለው ፡ አለቀሱ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሲሞቱ ፡ መቃብርዎ ፡ ሐ
ይቅ ፡ ደሴት ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደጀ ፡ ሰላም ፡ ነው ። ከዚህ ፡
በኋላ ፡ ይቴጌ ፡ ተዋበች ፡ ግሸን ፡ ቀብረው ፡ በጌ ፡ ምድር ፡
ወርደው ፡ በኀዘን ፡ ተቀምጠው ፡ ሳሉ ፡ ልጅ ፡ ጋረድ ፡ የሚ
ባል ፡ ያጎትዎ ፡ ልጅ ፡ ሸፍታ ፡ ተነስቶ ፡ ሀገር ፡ ይዘርፍ ፡ ዠ
መር ፡ ጦርነቱም ፡ እጅግ ፡ የተፈራ ፡ ሆነ ፡ ንጉሡም ፡ ይህነን ፡
ሰምተው ፡ ሂደው ፡ ቢገጥሙት ፡ አልጋዎን ፡ ፈልጓልና ፡ ሲ
ዋጋ ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ንጉሡን ፡ አሳየኝ ፡ እያለ ፡ ገፍቶ ፡ ሲ
መጣ ፡ ከንጉሡ ፡ አጠገብ ፡ የእንግሊዝ ፡ ሰው ፡ ሊቀ ፡ መ
ኳስ ፡ ዮሐንስ ፡ ቁሞ ፡ ነበርና ፡ እንደ ፡ ቀረበ ፡ አይቶ ፡ ጠበ
ንጃ ፡ ቢተኩስ ፡ ልጅ ፡ ጋረድን ፡ ገደለ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የልጅ ፡
ጋረድ ፡ ወንድም ፡ ሊቀ ፡ መኳስ ፡ ዮሐንስን ። ንጉሡም ፡



የልጅ ፡ ጋረድን ፡ ወንድም ፡ ገደሉ ። ከዚህ ፡ ወዲህ ፡ ድል ፡
ለንጉሡ ፡ ሲሆን ፡ ከሞቶው ፡ በቀር ፡ የተማረከው ፡ ሺ ፡ ከ
፳፱ ሆን ። ይህነንም ፡ ሁሉ ፡ ደባርቅ ፡ ከገቢያው ፡ ላይ ፡ ሲ
ቀጡ ፡ አንገቱን ፡ ለብቻው ፡ አካሉን ፡ እየቈረጡ ፡ ጣሉት ፡
የዚህስ ፡ ቍጥር ፡ በምን ፡ ታወቀ ፡ ቢሉ ፡ ፍሪዳ ፡ በዝቶ ፡ ሲ
ታረድ ፡ ቍጥሩ ፡ በጭራው ፡ እንዲታወቅ ፡ አንገት ፡ አንገ
ቱን ፡ የተቈረጠውን ፡ ሁሉ ፡ ስብስብ ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ካብ ፡
ሲያስከቡት ፡ ተቈጠረ ። ንጉሡም ፡ አደራሽ ፡ በተገኙ ፡ ጊዜ ፡
አዝማሪ ፡ በግብር ፡ ላይ ፡ ቁሞ ፡

ጋረድ ፡ ሞተ ፡ እንኳ ፡ ተቀበረ ፡
ያንት ፡ ወንድም ፡ ነውና ፡ እንፈረው ፡ ነበረ ፡

ብሎ ፡ ገጠመ ፨ ። ከዚህም ፡ ቀድሞ ፡ ብሩ ፡ ኃይሉ ፡
የሚባል ፡ ሸፍታ ፡ ከጣና ፡ ባሕር ፡ ገብቶ ፡ ከደሴት ፡ ውስጥ ፡
ተቀመጠ ። የጣና ፡ ባሕርም ፡ አለታንኳ ፡ የሚገቡት ፡ አይዶ
ለምና ፡ በዙሪያው ፡ ያለ ፡ ታንኳ ፡ ሰብስበው ፡ ገብተው ፡ ሲ
ዋጉ ፡ በየጦሩ ፡ ጀንፎ ፡ ገመድ ፡ እያሰሩ ፡ ወርውሮ ፡ ከታ
ንኳ ፡ ሁኖ ፡ ሲወጋው ፡ ያነን ፡ ገመድ ፡ በሳበው ፡ ጊዜ ፡ ከነ
ታንኳው ፡ ያቀርበዋል ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ጕልበቱ ፡ ይ
ገድላል ፡ እንዴህ ፡ አድርገው ፡ ብሩ ፡ ኃይሉን ፡ ያዙ ። ይህም ፡
የባሕር ፡ ጦር ፡ በኢትዮጵያ ፡ አለ ፡ ቴዎድሮስ ፡ አልተደረ
ገም ፨ ። አገው ፡ ንጉሤም ፡ የሚባል ፡ ሸፍታ ፡ በ
ወጣ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ መቅደላ ፡ ነበሩ ፡ ጓዙን ፡ በመቅደላ ፡
እግር ፡ ሰላምጌ ፡ ትተው ፡ ገሥገሡ ፡ ከበረኃም ፡ ውስጥ ፡ እየ
ገባ ፡ እጅግ ፡ ቀን ፡ ተከተሉት ። ነገር ፡ ግን ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፡
በድንገት ፡ ደረሱበት ፡ ጥቂትም ፡ ተዋጋ ፡ ድል ፡ ሁኖ ፡ ሲ
ያዝ ፡ ከርሱ ፡ ገራ ፡ የነበረ ፡ ወታደር ፡ ድኃ ፡ ድኃውን ፡ ካገ

ርም ፡ ውጣ ፡ እያለ ፡ በግድ ፡ የወጣውን ፡ ምረውታል ። አ
ገው ፡ ንጉሜን ፡ ከወንድሙ ፡ ከመኳንንቱ ፡ ጋራ ፡ እጅ ፡ እግ
ሩን ፡ እየቈረጡ ፡ ጣሉት ፡ ከዚህም ፡ ላይ ፡ ከወደቁበት ፡ እ
ህል ፡ ውሀ ፡ የሚሰጥ ፡ አልነበረምና ፡ ውሀ ፡ ጥም ፡ ቢጠና
በት ፡ አገው ፡ ንጉሜ ፡ ይህነን ፡ የወርቅ ፡ ድሪዬ ፡ ሰጥቸ ፡ ፩ዋ
ንጫ ፡ ውሀ ፡ ባገኘሁ ፡ ብሎ ፡ ተመኘ ፡ ወንድሙም ፡ ሰም
ቶት ፡ ላትተርፍ ፡ ምን ፡ ያደክምሃል[1] ፡ ብሎት ፡ ወዲያው ፡
፪ቱም ፡ ሞቱ ። እንዲህ ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ እጅግ ፡
ደስታ ፡ አድርገው ፡ በምገዛው ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ያልዘፈነልኝ ፡
ጠላቴ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አዋጅ ፡ ነገሩ ። በዚህም ፡ ዓዋጅ ፡
ቃል፡እሰይ፡ንጉሡን፡ቀናዎ፡እያለ፡ያልዘፈነ፡የለም ፨ ።
ይህን ፡ አድርገው ፡ ሲመለሱ ፡ ከደጃች ፡ ውቤ ፡ ደብር ፡ ደረ
ስጌ ፡ አደሩ ፡ ወታደርም ፡ ድንገት ፡ ደርሶ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡
ነሽ ፡ የደጃች ፡ ውቤን ፡ ልጅ ፡ አይቶ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ሂዶ ፡
ጃንሆይ ፡ ለርስዎ ፡ ለንጉሥ ፡ የተገባች ፡ መልኳ ፡ እንደ ፡ ፀ
ሐይ ፡ የምታበራ ፡ ሴት ፡ አገኘሁ ፡ አለ ። ንጉሡም ፡ ሰው ፡
ጨምረው ፡ ሰደው ፡ አመጡ ፡ በመጡም ፡ ጊዚ ፡ መልከዎን ፡
ከግር ፡ እስከ ፡ ራስ ፡ ቈጥረው ፡ አይተው ፡ ይህችስ ፡ ጥሩ ፡
ወርቅ ፡ ናት ፡ አሉ ። ይህም ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ ሕግ ፡ አድርሰው ፡
በሥርዓተ ፡ መንግሥት ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ በጌ ፡ ምድር ፡ መጡ ።
ደብረ ፡ ታቦር ፡ ተቀምጠው ፡ ስሙ ፡ ዓለም ፡ አየሁ ፡ የሚ
ባል ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ተወለደ ። በዚህም ፡ ነፍጥና ፡ መድፍ ፡
ሲተኰስ ፡ ብዙ ፡ ደስታ ፡ ሁኖ ፡ ፳፪ እስር ፡ ተፈታ ፨ ።
ነገር ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ከሥር

---

[1] ይዳክምሐል ፡



ዓት ፡ ይናወጹ ፡ ዡመር ፡ ከድኃው ፡ በግብር ፡ ከጳጳሱ ፡ በም
ክር ፡ አልተሰማሙም ። አንድ ፡ ጊዜም ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡
ላይ ፡ ከሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ ጋራ ፡ አቡነ ፡ ሰላማን ፡ ተጣልተው ፡
የድንኳኑን ፡ ዙሪያ ፡ በሾህ ፡ አሳጥረው ፡ በነፍጥ ፡ ዘብ ፡ አስ
ጠበቋቸው ። ሊቀ ፡ ጳጳሱም ፡ እጅግ ፡ ነገር ፡ አይተው ፡ አድ
ንቀው ፡ ወደ ፡ ሀገረዎ ፡ ተመለሱ ። ደግሞም ፡ የንጉሡ ፡ ም
ግባር ፡ እየተለወጠ ፡ የሀገር ፡ መዘረፍ ፡ ጡዋት ፡ ማታ ፡ በየ
ቀኑ ፡ ልማድ ፡ ሆነ ፨ ። እንዲህም ፡ ሲሆን ፡ ካ
ህን ፡ ደብተራ ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ እጅግ ፡ የተጸላ ፡ ሆነ ፡ ሲሰ
ድቡትም ፤

ይህ ፡ አረግራጊ ፡
አቴና ፡ ወጊ ፡
ራሱን ፡ ታታቂ ፡
ወገቡን ፡ ሰባቂ ፡

ይሉት ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ከየምድሩ ፡ ነቅለውት ፡
ኖረ ፡ የርሻ ፡ ሁሉ ፡ መጋዘ ፡ ለንጉሡ ፡ ይገባ ፡ ነበር ፡ ምድር ፡
በእጄ ፡ ብለው ፡ ነበርና ፡ ለዜህም ፡ አማርኛ ፡ የሚያስረዳ ፡
ነገር ፡ አለቃ ፡ ፈንታ ፡ የማኅደረ ፡ ማርያም ፡ ለንጉሡ ፡ ባለ
ሟል ፡ ሁነው ፡ ፺ብር ፡ ሰጡዎና ፡ ንጉሡ ፡ ይህን ፡ ወስደህ ፡ አት
በላውም ፡ ከቤትህ ፡ ትቀብረዋለህ ፡ ቢሉዎ ፡ ጃንሆይ ፡ መሬት ፡
በእጄ ፡ ነው ፡ ብለዋል ፡ መቼም ፡ አያመልጥ ፡ አሉ ፡ ለጊዜው ፡
ፍቅር ፡ አለና ፡ አማርኛውን ፡ ቢሰሙ ፡ ንጉሡ ፡ ስቀው ፡
ዝም ፡ አሉ ። ደግሞም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡
ላይ ፡ ሲሰሩ ፡ አለቃ ፡ ፈንታ ፡ ብለው ፡ ይህ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ
ያን ፡ ስፋትና ፡ መጥበቡ ፡ እስኪ ፡ እየው ፡ ቢሉዎ ፡ በዚህ ፡
ዘመን ፡ ንጉሡ ፡ ቂስን ፡ ብቻ ፡ ፭ ሰሞነኛ ፡ እያሉ ፡ ጥቂት ፡

ጥቂት፡ ያከብሩ፡ ነበርና፡ አለቃ፡ ፈንታ፡ ሲመልሱ፡ በአማርኛ፡ ቃል፡ ለምደዋልና፡ ጃንሆይ፡ ለ ፳ ሰሞነኛ፡ መቼም፡ ይበቃል፡ አሉ፡ የዚህን፡ ሁሉ፡ ነገር፡ ውስጡን፡ ቂም፡ አድርገው፡ ኑረው፡ በመጨረሻ፡ በጥቂት፡ ነገር፡ አስረው፡ ወዲያው፡ አስገደሉዎ ፨ ። እንዲህም፡ እያደረጉ፡ ካህን፡ ደብተራ፡ እንደ፡ ልማዱ፡ ለራሱ፡ መጠምጠሚያ፡ እያደረገ፡ ወደ፡ ንጉሡ፡ በመጣ፡ ጊዜ፡ እንዲህ፡ ብለው፡ ጠየቋቸው፡ መጠምጠሚያ፡ እያወለቃችሁ፡ ወደ፡ ታቦት፡ መግባታችሁ፡ ስለ፡ ምን፡ ነው፡ አሉ፡ ካህናትም፡ ሲመልሱ፡ ታቦት፡ ማኅደረ፡ እግዚአብሔር፡ ነው፡ አክሊላቲሆሙ፡ ያወርዱ፡ እንዘ፡ ይሰግዱ[1]፡ ይላልና፡ ስለዜህ፡ ነው፡ አሉ። በዚህ፡ ጊዜ፡ ንጉሡ፡ እንዴህ፡ ከሆነስ፡ በኔም፡ እግዚአብሔር፡ አድሮ፡ ነው፡ ይህን፡ ሁሉ፡ ሰው፡ እናንተን፡ ጨምሮ፡ የሚያስገዛኝ፡ እንግዴም፡ በፊቴ፡ ላይ፡ ጥምጥም፡ አይገባችሁም፡ አሉ። ከዚህ፡ ወዲህ፡ በንጉሡ፡ አደባባይ፡ የካህን፡ ጥምጥም፡ ቀረ፡ ከመነኰሴ፡ ቆብ፡ በቀር። ነገር፡ ግን፡ እግዚአብሔር፡ ስራውን፡ ሁሉ፡ በምክንያት፡ ይገልጣልና፡ ነፍስ፡ ገዳይ፡ ተይዘ፡ ወደ፡ ንጉሡ፡ መጣ፡ በዚህ፡ ጊዜ፡ አምባ፡ ጫራ፡ ሰፍረው፡ የጐንደር፡ ካህን፡ ፩ ሳይቀር፡ ይምጣ፡ ብለው፡ አዘዙ፡ በመጣም፡ ጊዜ፡ ጳጳስ፡ በቀኝ፡ እጨጌው፡ በግራ፡ ንጉሡ፡ በማኸከል፡ ተቀመጡ። እንዴህም፡ በሆነ፡ ጊዜ፡ ካህናቱን፡ ቄሶች፡ የሚባሉትን፡ ለይተው፡ በምንጣፍ፡ ላይ፡ አስቀመጡ። ከዜህ፡ በኋላ፡ ፍትሐ፡ ነገሥት፡ አስመጥተው፡ እነዚያን፡ ቄሶች፡

[1] quatre mots gheez.



የዚህን፡ የነፍስ፡ ገዳይ፡ ነገር፡ ፍረዱ፡ ቢሉ፡ አንዱ፡ ቄስ፡ ተነስቶ፡ ጃንሆይ፡ መሸ፡ ለቍርባን፡ ጠባ፡ ለኪዳን፡ ብለን፡ እንኖራለን፡ እንጂ፡ ፍትሐ፡ ነገሥትስ፡ አልተመለከትንም፡ አለ። ይህንም፡ በተናገረ፡ ጊዜ፡ ንጉሡ፡ ሲመልሱ፡ ደብተራስ፡ እንደኛ፡ ወታደር፡ ነው፡ በስማችሁ፡ መምሬ፡ ትባላላችሁ፡ ምን፡ እየስተማራችሁ፡ ነው፡ ፍትሐ፡ ነገሥት፡ ለናንተ፡ ይገባል፡ ብለው፡ ፊትዎ፡ ተለወጠ። በዚህ፡ ጊዜ፡ ሊቃውንቱ፡ ደብተሮች፡ ከአደባባዩ፡ ቁመው፡ ነበርና፡ ከንቲባ፡ ኃይሉ፡ ተነስተው፡ ጃንሆይ፡ ከነዚያ፡ ከቆሙቱ፡ እንታረቅ፡ እንጂ፡ እነዚህማ፡ እንኳን፡ ፍትሐ፡ ነገሥት፡ ይተረጕሙ፡ ያነበቡትን፡ ወንጌል፡ አይተረጕሙም፡ አሉ። ንጉሡ፡ ይህን፡ ሲሰሙ፡ ሊቃውንቱ፡ ደብተሮች፡ ቀረቡ፡ አፄ፡ ቴዎድሮስም፡ በትሕትና፡ ቃል፡ አባቶቼ፡ እኔ፡ ከናንተ፡ አውቃለሁ፡ ብዬ፡ ልማዳችሁን፡ መከልከሌ፡ አይደለም፡ ከነገሥታቱም፡ አልበልጥም፡ ነገር፡ ግን፡ ሥርዓት፡ ታውቁ፡ በዬ፡ ነው። አሁንም፡ ጥምጥማችሁን፡ መልሻለሁ፡ ፍትሐ፡ ነገሥትም፡ የናንተ፡ ነው፡ አውጡ፡ በኋቸው፡ ጊዜ፡ ገንዝባቸው፡ ነውና፡ ንሴብሐ[1]፡ ብለው፡ ተመለሱ፡ መጠምጠሚያም፡ እንደ፡ ቀደመው፡ ሆነ ፨ ።

ከዚህ፡ በኋላ፡ ግብር፡ እየተጨመረ፡ ድኃ፡ እየተመረረ፡ ሲኖሩ፡ ከ ፳ ሰሞነኛ፡ በቀር፡ ሁሉም፡ ይገብር፡ ብለው፡ ዓዋጅ፡ ቢነግሩ፡ ፩ የዳሞት፡ ደብተራ፡ መጥቶ፡ ጃንሆይ፡ እንደ፡ ዓረብ፡ ንጉሥ፡ መሆንዎ፡ ነው፡ አለ። ንጉሡም፡ ምንም፡ ካህን፡ ደብተራን፡ በምግበሩ፡ ቢጠሉት፡ የደኅንነት፡

[1] mot gheez.

ነገር ፡ አይጠሉም ፡ ነበሩና ፡ ልብዎን ፡ አንቅተው ፡ የዓረብ ፡
ንጉሥ ፡ ያልኸኝ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ አሉት ። እርሱም ፡ ጃን
ሆይ ፡ የዓረብ ፡ ንጉሥ ፡ ያልሁዎ ፡ አባቱ ፡ የክርስቲያን ፡ እ
ናቱ ፡ የእስላም ፡ ነበሩ ፡ አባቱ ፡ ሲሞት ፡ በአባቱ ፡ ስፍራ ፡
ነገሠ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የናቱ ፡ ዘመዶች ፡ መጥተው ፡ እሌህን ፡
ካፊሮች ፡ አጥፋልን ፡ በዘመናችን ፡ ደስ ፡ ይበለን ፡ አሉት ።
እርሱም ፡ ዘመዶቹን ፡ እንዴት ፡ ላጥፉ ፡ አይሆንም ፡ ቢላ
ቸው ፡ ከትምህርትና ፡ ከቍርባን ፡ አንዱን ፡ ይያዙ ፡ አሉት ።
እርሱም ፡ ክርስቲያኖችን ፡ ምከሩ ፡ ቢላቸው ፡ ትምህርት ፡
ይቅር ፡ ቍርባን ፡ ይኑር ፡ አሉ ። ምነው ፡ እንዴህ ፡ ማለታ
ቸው ፡ ቢሉ ፡ ቍርባን ፡ ታጕለ ፡ ሲባል ፡ ለጊዜው ፡ ያሳዝና
ልና ፡ ትምህርት ፡ ቀሊል ፡ መስሏቸው ፡ ነው ፡ በዚህም ፡ ነገር ፡
ትምህርት ፡ ቀርቶ ፡ ሲኖር ፡ በየደብሩ ፡ የሚኖሩት ፡ ፫ ት ፡
፫ ት ፡ ሰሞነኞች ፡ ፩ ሲሞት ፡ ፪ ይቀራሉ ። ደግመኛም ፡ አ
ንድ ፡ አንድ ፡ ሲሉ ፡ በሞት ፡ ተጨረሱ ፡ እየተማረ ፡ እንዳይ
ገባ ፡ ትምህርት ፡ ተከልክሏል ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ሀገሩን ፡ እስ
ላም ፡ ወርሶት ፡ ቀረ ። እርስዎም ፡ ጃንሆይ ፡ አስተማሪ ፡ ይገ
ብር ፡ ሰሞነኛ ፡ ይዳን ፡ ማለትዎ ፡ ትምርት ፡ ሲቀር ፡ ቍርባን ፡
እንደ ፡ ቀረ ፡ እኛን ፡ አስተማሪዎችን ፡ ገብሩ ፡ ማለት ፡ ቍር
ባን ፡ ይቅር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይዘጋ ፡ ማለትዎ ፡ መሰለ ፡
ብሎ ፡ ይህን ፡ ታሪክ ፡ ቢነግርዎ ፡ ንጉሡ ፡ እንዲህ ፡ መለሱ
ለት ፡ እንዳንተ ፡ የሚያስተምር ፡ ሁሉ ፡ ይገብር ፡ አላልሁም ፡
ዘንጉን ፡ እየጐተተ ፡ መንደር ፡ ለመንደር ፡ የሚዞር ፡ አረግ
ራጊውን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አሁንም ፡ አንተን ፡ የመሰለ ፡ ሁሉ ፡
ከግብር ፡ ይዳን ፡ ብለው ፡ ዓዋጅ ፡ ነገሩለት ፨ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሜጫ ፡ ዘጌ ፡ ላይ ፡ ሰፍረው ፡ ከእንግሊዝ ፡ ንግ



ሥት ፡ ራሰም ፡ የሚባል ፡ ተልከ ፡ መጣ ። ስለምን ፡ ቢሉ ፡
ቀድመው ፡ የመጡ ፡ ከእንግሊዝ ፡ ከፈረንጅም ፡ ነበሩ ፡
ንጉሡ ፡ ተጸልተዋቸው ፡ ታስረዋል ፡ ይህነን[1] ፡ ሰምታ ፡ የእ
ንግሊዝ ፡ ንግሥት ፡ ብዙ ፡ ልውጥ ፡ ልውጥ ፡ ዕቃ ፡ ድንቅ ፡
የሚባል ፡ የግምጃ ፡ ድንኳን ፡ አሲዛ ፡ ላከችው ፡ ደብዳቤ ፡
ጨምራ ፡ ቃሏም ፡ እሊህ ፡ ሰዎች ፡ የሀበሻን ፡ ንጉሥ ፡ በድ
ለው ፡ እንደሆነ ፡ በሀገርህ ፡ ፍርድ ፡ ይቀጡ ፡ ደህና ፡ ቢሆኑ ፡
ፈትተህ ፡ ላክልኝ ፡ የሚል ፡ ነው ፡ እርሱም ፡ ዕቃውን ፡ ሁሉ ፡
ሰጥቶ ፡ እነዚያንም ፡ አስታርቆ ፡ ተመልሶ ፡ መተማ ፡ ሲደ
ርስ ፡ ንጉሡ ፡ መልሰው ፡ ከነዚያው ፡ ዘመዶቹ ፡ ጋራ ፡ መቅ
ደላ ፡ ገብቶ ፡ ታሰረ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ለዚህ ፡
ንጉሥ ፡ ወዳጅ ፡ ነኝ ፡ አስታርቃለሁ ፡ ብዬ ፡ መጣሁ ፡ አስታ
ርቄ ፡ ስመለስ ፡ እኔን ፡ እንዴት ፡ አሠረ ። አሁንም ፡ እርሱ ፡
አይፈታኝም ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እንጂ ። ይህነንም ፡ ሲ
ናገር ፡ በመኳንንቱ ፡ ፊት ፡ ነበርና ፡ አይዞህ ፡ ንጉሡ ፡ አን
ተን ፡ አልጠሉም ፡ እነዚያን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አሁንም ፡ ትፈ
ታለህ ፡ ቢሉት ፡ እናንተም ፡ ደግ ፡ ተናገራችሁ ፡ በእግዚአ
ብሔር ፡ ኃይል ፡ ስፈታ ፡ ታያላችሁ ፡ ብሎ ፡ ዝም ፡ አለ ።
ይህም ፡ አልቀረምና ፡ ታሪኩ ፡ ኋላ ፡ ይነበባል ፨ ።

እንዲህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ሂደው ፡
ተቀመጡ ፡ አገርም ፡ እየተጨነቀ ፡ ነበረ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡
ግምባሮ ፡ ካሳ ፡ የሚባል ፡ የአለፋ ፡ ባላገር ፡ ሸፍታ ፡ ሁኖ ፡
ቋራ ፡ ባላምባራስ ፡ ገልሞ ፡ የንጉሡን ፡ ሹም ፡ ሊወጋ ፡ ወ
ረደ ። ባላምባራስ ፡ ገልሞም ፡ ጠጁ ፡ እንደ ፡ ወረደ ፡ እን

---

[1] ይህን ፡

ጀራው፡እንደ፡ተጣለ፡ግብር፡አስገብቶ፡ጥሎ፡ወጣ።
ግምባሮ፡ካሳም፡ያነን፡የተከተለ፡ሰው፡ሁሉ፡ይዞ፡ገብቶ፡
ሲበላ፡ሲጠጣ፡ባለምባራስ፡ገልሞ፡ሰልፎ፡ቢመጣ፡ገ
ጠመ፡ይህን፡ጊዜ፡የግምባሮ፡ካሳ፡ሰው፡ከጦር፡የተረ
ፈው፡በገደል፡አልቆ፡የቀረው፡፲፪ ተማረከው። የዚህም፡
የምስራች፡ጐንደር፡ለንጉሡ፡በገባ፡ጊዜ፡እጅግ፡ደስታ፡
ተደረገ፡ንጉሡም፡ወደ፡ጀንዳ፡ወረዱ፡በዚህ፡ግምባሮ፡
ካሳን፡ከባለሚሎቹ፡ጋራ፡ሰኞ፡ገባያ፡ሰቀሉት። የዚህም፡
ነገር፡ትንቢት፡አለው፡እንዴት፡ቢሉ፡አፄ፡ኢያሱ፡የሚ
ባሉ፡ከቤተ፡መንግሥት፡የተወለዱ፡ነበሩ፡ንጉሡም፡እ
ጅግ፡ያከብሩዎ፡ይወዱዎ፡ነበር። ከዚህም፡ፍቅር፡የተነሣ፡
ፊትና፡ኋላ፡ሲሄዱ፡የግምባሮ፡ካሳ፡ነገር፡ምን፡ይመስ
ለዋል፡ንብ፡ሰፈረብኝ፡ርግብ፡አረፈችብኝ፡እያለ፡ያሶ
ራል፡ብለው፡ጠየቁዎ። አፄ፡ኢያሱም፡ሲመልሱ፡ጃን
ሆይ፡ይህ፡ምን፡ነገር፡አለው፡ርግብ፡አረፈብኝ፡ማለቱ፡
ርግብ፡ያሞራ፡ወገን፡ናት፡ሥጋውን፡አሞራ፡ይበላዋል።
ንብ፡ሰፈረብኝ፡ማለቱ፡ንብ፡የዝንብ፡ወገን፡ነው፡ሙቶ፡
ዝንብ፡ይከበዋል፡ብለው፡ቢተረጕሙት፡አፄ፡ቴዎድ
ሮስ፡ይህን፡ጊዜ፡በፈረስ፡እንደሆኑ፡ወንዱ፡የመይሳ፡
ልጅ፡ይህን፡ያደርጋል፡ብለው፡ድንፋታ፡አድርገው፡ነበ
ርና፡እግዚአብሔርም፡በውነት፡ፈርዶ፡ግምባሮ፡ካሳን፡
ከንጉሡ፡እጅ፡ቢጥለው፡እንዲህ፡ተሰቀለ። ያነን፡በም
ርኮ፡የተቈጠረ፡፲፪ ሰው፡ግን፡አለፋ፡ከሚባል፡ሐሙስ፡
ገቢያ፡አውጥታችሁ፡ደብድቡት፡ብለው፡ቢያዙ፡ወጥቶ፡
በገቢያው፡ቀን፡ተደብድቦ፡አለቀ። እግዚአብሔር፡እን
ዳዘዘበት፨ ። በዚህም፡ዘመን፡ግራ፡አዝማች፡



ዓለሜን፡ተድላ፡ኋሉ፡ለአገው፡ጐጃም፡ሹሞ፡ወታደር፡
በተሰሪ፡ነበረ፡ንጉሡም፡ገሥግሠው፡በድንገት፡ደረሱ።
በዚህ፡ጊዜ፡ጦርነት፡ሲሆን፡ከባላገር፡ከወታደርም፡ከሞ
ተው፡በቀር፡፰ሺ፡የተማረከው፡ሆነ። ይህነንም፡ሰብስ
በው፡ባለወግን፡ሁሉ፡ጠርተው፡ሲቈርጥ፡ጊዜው፡መ
ሸቶ፡ነበር፡የማያልቅ፡ቢሆን፡ንጉሡ፡ቀርበው፡እንደ፡
ከብት፡እየከፈሉ፡እየቈጠሩ፡አሳደሩት። ሲነጋ፡አምጣ፡
ብለው፡ሁሉም፡ተደብድቦ፡ሲያልቅ፡ንጉሡ፡ለማየት፡
ቢወርዱ፡አንዱ፡አንገቱ፡ታርዶ፡ተንጋሎ፡ወድቆ፡እነ
ሣለሁ፡እያለ፡ነፍሱ፡ሳትለይ፡ቢያዩት፡ሁሉንም፡እን
ዴህን፡አድርጋችኋል፡ብለው፡ተቈጡ። በዚህም፡እርሰዎ፡
ንጉሡ፡ዠምረው፡ያን፡ሁሉ፡እያዩ፡አስጨረሰው፡ሲ
ቆሙ፡ወደ፡ፈጣሪዎ፡ይህን፡ሁሉ፡ጠላቴን፡በእጄ፡ጥሎ፡
እንዲህ፡አስተኝቶ፡ያሳየኝ፡ብለው፡መሬቱን፡ስመው፡
ከድንኳንዎ፡ገብተው፡ተቀመጡ። ይህም፡የተደረገ፡እን
ጃባራ፡ነው። የዚህም፡አልቃሽ፡

አንጥረኛው፡ብዙ፡የንጉሡ፡ቤት፡
ባል፡አልቦ፡አደረጉት፡ይህን፡ሁሉ፡ሴት፤

አለች፨ ። በዚህን፡ዘመን፡ጐንደር፡ሎዛ፡ሰፍ
ረው፡ጥኑ፡ራብ፡ሁኖ፡የበሬ፡አንዠት፡በአሞሌ፡ይገዛ፡
ነበር፡ሰውም፡ተጐዳ። አቤቶ፡አቡዬም፡የሸዋን፡አልጋ፡
በመንግሥት፡ይጠብቁ፡የነበሩ፡በዚያ፡ጊዜ፡ሙተው፡
ሎዛ፡ተቀበሩ። ከዚህም፡ተቀምጠው፡ኑረው፡ወደ፡መ
ቅደላ፡መጡ፡በዙሪያው፡ያሉ፡ሀገሮች፡እየተዘረፉ፡የመ
ቅደላ፡ወታደር፡የጋላውን፡ጦር፡ይጠብቅ፡ነበር፨ ።
ነገር፡ግን፡የእግዚአብሔር፡ይቅርታው፡በጊዜው፡ሲደ

ርስ ፡ በ፯ሺ፡ ከ፫፻፶፰ ዘመን ፡ በማርቆስ ፡ በሰኔ ፡ በ፳፱ ቀን ፡ ምንይልክ ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ ሀገርዎ ፡ ሸዋ ፡ መጡ ። የዚህስ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ከሀገርዎ ፡ ከሸዋ ፡ ከመጡ ፡ ዠምሮ ፡ ለአፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ እንደ ፡ ልጅ ፡ ሁነው ፡ መኳንንት ፡ ሠራዊትም ፡ ሁሉ ፡ እጅ ፡ እየነሱ[1] ፡ ያከብሩዎ ፡ ይወዱዎ ፡ ነበር ። በዘመንዎም ፡ ሁሉ ፡ ከንጉሡ ፡ ልጅ ፡ ከመሸሻ ፡ ሳይለዩ ፡ በራስ ፡ ውቤ ፡ ጠባቂነት ፡ መቅደላ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተቀመጡ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ሴት ፡ ልጅዎን ፡ ሰጥተው ፡ አማች ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፡ የሸዋን ፡ ሰው ፡ እናትዎን ፡ ይዘው ፡ ወጡ ፡ የዚህም ፡ መንገድዎ ፡ ማታ ፡ ተነስተው ፡ ሌሊቱን ፡ ሁሉ ፡ ነበር ። ሲነጋ ፡ ኩታማ ፡ በሚባል ፡ ፈረስዎ ፡ ንጉሡ ፡ ተቀምጠው ፡ ወደ ፡ እስር ፡ መንደር ፡ መጡ ፡ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ተናደው ፡ ነበርና ፡ እስሩን ፡ ሁሉ ፡ አውጡ ፡ ሲሉ ፡ የወርቂት ፡ ልጅ ፡ ማናቸው ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ጠየቁ ። ሰዎችም ፡ የክርስትና ፡ ልጅዎ ፡ ነበርና ፡ ይምሩታል ፡ ብለው ፡ ፈጥነው ፡ አሳዩዎ ። እርሱም ፡ እኔ ፡ ልጅዎ ፡ ነኝ ፡ በነገ ፡ ዠምበር ፡ ግብርዎን ፡ ላግባ ፡ ዛሬ ፡ ያሳድሩኝ ፡ አለ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በንጉሡ ፡ ልብ ፡ ምሕረት ፡ አልነበረምና ፡ እርሱን ፡ በፊት ፡ በፊት ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩ ፡ ፳፱ የጋሎች ፡ መኳንንት ፡ እነፋሪስ ፡ ቃሲም ፡ እነ ፡ አሊ ፡ ወዳጄ ፡ ራቁታቸውን ፡ እያስጐተቱ ፡ ከመቅደላ ፡ ገደል ፡ አቀረቧቸው ። እጅ ፡ እግራቸውን ፡ በጎራዴ ፡ እያስቈረጡ ፡ ሁሉንም ፡ ገደል ፡ ሲያስጥሉ ፡ አንዱ ፡ ባለመንቀር ፡ ከገደሉ ፡ ሲቀርብ ፡ ሞተ ። ሰዎችም ፡ አይተው ፡ ጃንሆይ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ሙቷል ፡

---

[1] እየነሡ ፡



ቢሉ ፡ ከነእጨቱ ፡ ገፍተህ ፡ ጣለው ፡ ብለው ፡ ቢጥሉት ፡ ከገደሉ ፡ ላይ ፡ እንጨቱ ፡ ይዞት ፡ ተንጠለጠለ ። ከዚህም ፡ ለይ ፡ እንዳይቀር ፡ በደንጊያ ፡ አሶርደው ፡ ብለው ፡ ተሰባብሮ ፡ አረፈ ፨ ። ይህን ፡ አድርገው ፡ ሲመለሱ ፡ አቡነ ፡ ሰላማን ፡ እያሙ ፡ እንዲህ ፡ ሳጠፉ ፡ ሳይገዝቱኝ ፡ ቀሩ ፡ አሉ ። ስለ ፡ ምን ፡ ሳይገዝቱ ፡ ቀሩ ፡ ቢሉ ፡ ንጉሡ ፡ ባጠገብዎ ፡ ሲሄዱ ፡ ሊገዝቱ ፡ ወጡ ፡ ሰዎችም ፡ መጥተው ፡ ንጉሥ ፡ ተናደዋል ፡ አሁን ፡ ቢገዝቱ ፡ እኛንም ፡ ጨምረው ፡ ያስጠፉናል ፡ ቢሉዎ ፡ እናንተስ ፡ ስታልቁ ፡ እነዚያው ፡ በኃጢአታቸው ፡ ይሙቱ ፡ ብለው ፡ ሳይገዝቱ ፡ ቀሩ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በመቅደላ ፡ የነበሩ ፡ ካህናት ፡ እጅግ ፡ ወቀሳ ፡ ወርዶባቸው ፡ ሞት ፡ ይመኙ ፡ ነበር ፡ ከፍርሀት ፡ የተነሣ ፨ ።

። ። ። ።

እንግዴህ ፡ ወደ ፡ በጌምድር ፡ ነገር ፡ እንመለስ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ደግመኛ ፡ ሂደው ፡ ዘጌን ፡ ዘረፉ ። ይህም ፡ ዘጌ ፡ የከበረ ፡ ገዳም ፡ ነው ፡ በዘረፉትም ፡ ጊዜ ፡ የቤቱ ፡ ሲያልቅ ፡ የአትክልት ፡ ቦታ ፡ ነበርና ፡ አትክልቱን ፡ ሁሉ ፡ በመጥረቢያ ፡ አስቈርጠው ፡ ስሩንም ፡ በዶማ ፡ አስቈፍረው ፡ ጣሉት ። ከዚያ ፡ ተመልሰው ፡ የቤገምድርን ፡ እህሉን ፡ ዘርፈው ፡ ቀጥለው ፡ ላሙን ፡ በሬውን ፡ ነድተው ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ አወጥተው ፡ ለሠራዊትዎ ፡ እየከፈሉ ፡ ሰጥተው ፡ እያረድህ ፡ ጣል ፡ ብለው ፡ አዘዙ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ እያረደ ፡ ሲጥል ፡ ደክሞት ፡ አድሮ ፡ ፩ ከብት ፡ በሰፈር ፡ ቁሞ ፡ የታየ ፡ እንደሆነ ፡ አለቃው ፡ ይቀጣ ፡ ነበር ። የታረደውም ፡ ከብት ፡ ሁሉ ፡ አሞራና ፡ ጅብ ፡ ሳይበላው ፡ ቀረ ። ደብረ ፡ ታቦርንስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ከተማ ፡ አደረጉት ፡ ቢሉ ፡ ከባሕር ፡ ወዲህ ፡ በሕንጻ ፡

የማይገኝ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደ ፡ ደብተራ ፡ ኦሪት ፡ ሜደውን ፡ ደልድለው ፡ አሳድገው ፡ ጠፈሩን ፡ በብረት ፡ ማ ገር ፡ በዚያው ፡ እየቸነከሩ ፡ ሰሩ ። ስለ ፡ ምን ፡ ቢሉ ፡ መድ ኃኒ ፡ ዓለም ፡ ይህን ፡ ያስጨረሰኝ ፡ እንደሆን ፡ መንግሥቴን ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ ባረከልኝ ፡ አውቃለሁ ፡ ብለው ፡ ነው ። በርሱም ፡ ቸርነት ፡ ተዠምሮ ፡ ሲጨረስ ፡ የእ ስር ፡ ቤት ፡ አደረጉት ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የበጌምድር ፡ ሰው ፡ አንድነት ፡ ገጥሞ ፡ ጠላት ፡ ሆነ ። በሌሊትም ፡ እየመጣ ፡ በ ተራራ ፡ እየቆመ ፡ እየተሳደበ ፡ ይሄድ ፡ ዠመረ ፡ አንድ ፡ ጊ ዜም ፡ ወደ ፤ በለሳ ፡ ሲገሠግሱ[1] ፡ ባላገሩ ፡ ነፍጥ ፡ አናስተኵ ስም ፡ ብሎ ፡ በምድር ፡ ነጕድ ፡ መለሰ ። በዚህ ፡ ተናደው ፡ የሀገሩን ፡ ባሕር ፡ ማሽላ ፡ ዱባውን ፡ በሸዋ ፡ አማርኛ ፡ የባር ፡ ቅል ፡ ነው ፡ ይህነን ፡ ቢነቅሉ ፡ ባላገርም ፡ የገዛ ፡ ቤቱን ፡ አቃ ጠለ ፡ አፍርሶ ፡ እንዳይማግድ ፡ ሰፈርም ፡ ሲሆን ፡ በየቤቱ ፡ እንዳይገባ ፡ ተተንኰሎ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ ተመልሰው ፡ ወይ ናደጋን ፡ ደሪጣን ፡ ዘርፈው ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ገቡ ። ከዚህ ፡ ወዲህ ፡ የመዓት ፡ እንጂ ፡ የምሕረት ፡ ስራ ፡ አልተደረ ገም ፨

። በ ፯ ሺ ከ ፫፻፶፱ ዓመት ፡ በሉቃስ ፡ በ ፳ መጥቅ ፡ በ ፳፭ አበቅቴ ፡ የዓለም ፡ ሁሉ ፡ ጭንቅ ፡ ተዠመረ ፡ ከነገሡ ፡ በ ፲፬ ዓመት ፡ የአማራ ፡ የሳይንት ፡ ሰዎች ፡ መኳን ንት ፡ ሲከዱ ፡ ተይዘው ፡ በሐምሌ ፡ በ ፬ ቀን ፡ በነፍጥ ፡ ተደ ብድበው ፡ አለቁ ፡ እሊህም ፡ ፬፻ ሆኑ ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ለን ጉሡ ፡ ፩ ነገረ ፡ ሰሪ ፡ መጥቶ ፡ ዋድሎች ፡ ሊከዱዎ ፡ ነው ፡ አለ ። ቴዎድሮስም ፡ በጥበብ ፡ ለዋድሎች ፡ ደመወዝ ፡ እሰ

[1] ሲገሠገሡ ፡



ጣለሁና ፡ ይሰብሰቡ ፡ ብለው ፡ ዓዋጅ ፡ ነገሩ ፡ የወገን ፡ እረኛ ፡ ሳይቀር ፡ ተሰበሰበ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የየጁን ፡ ጦር ፡ በራስ ፡ አዲሉ ፡ አዘው ፡ ዙሪያውን ፡ አስከብበው ፡ በነፍጥ ፡ አለቁ ፡ ይመወዛቸውም ፡ ይህ ፡ ሆነ ፡ የነዚህም[1] ፡ ቍጥር ፡ ፯፻፶ ነው ። በዚህም ፡ ራስ ፡ አዲሉ ፡ የየጁን ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ሀገሩ ፡ ሌሊቱን ፡ ሄደ ፡ እኛንም ፡ ነገ ፡ እንዲህ ፡ ያደርጉናል ፡ ሲል ። በዚህም ፡ መሄድ[2] ፡ ከተማው ፡ ሁሉ ፡ የሚይዝ ፡ እየመሰለ ፡ ተጨምሮ ፡ እንዳይሄድ ፡ ከሰፈር ፡ የወጣህ ፡ እቀጣኸለሁ ፡ ብለውኻል[3] ፡ እያለ ፡ በሰፈሩ ፡ ዙሪያ ፡ እየዞረ ፡ የንጉሡ ፡ ወ ገን ፡ ተናገረ ፡ እንዲህም ፡ ባይናገር ፡ ከሰፈር ፡ ፩ ሰው ፡ አይ ቀርም ፡ ነበር ፡ የንጉሡን ፡ መጨከን ፡ እያየ ፡ ሁሉም ፡ ፈር ቷልና ። ራስ ፡ አዲሉም ፡ ሰውን ፡ ይዞ ፡ በክርስቶስ ፡ ኃይል ፡ ሲያመልጥ ፡ ፈረስ ፡ በቅሎው ፡ ከሰፈር ፡ የቀረው ፡ ፯፻ ሆነ ። ደግመኛም ፡ የሜጫ ፡ የአገው ፡ መኳንንት ፡ የክዳት ፡ ነገር ፡ ተገኝቶባቸው ፡ ፬፻ ታሰሩ ፡ እሊህንም ፡ ከሜዳ ፡ ላይ ፡ አው ጥተው ፡ ዙሪያውን ፡ በእሾህ ፡ እሳጥረው ፡ ደግሞ ፡ በዘበኛ ፡ አስጠብቀው ፡ ከሱሪ ፡ በቀር ፡ ልብሳቸውን ፡ እየስገፈፉ ፡ ጣኋቸው ፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ እህል ፡ ውሀ ፡ ተከልክለው ፡ የቀን ፡ ጣይ ፡ የሌሊት ፡ ውርጭ ፡ ሲያደክማቸው ፡ በ ፲ ቀን ፡ በ ፲፭ ትም ፡ እየተናገሩ ፡ አለቁ ። ሰውም ፡ ሁሉ ፡ ከእህል ፡ በተ ለየ ፡ በ ፯ ቀን ፡ ይሞታል ፡ ማለት ፡ በነዚህ ፡ ዘንድ ፡ ሐሰት ፡ ሆነ ። ደግሞም ፡ ሐዋርያት ፡ የረኃብን ፡ ኃይል ፡ አውቀው ፡ ከረኃብ ፡ ጦር ፡ ይሻላል ፡ ያሉት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ቃል ፡ ተነገረ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ከራቡ ፡ ውሀ ፡ ጥሙ ፡ ጠንቶ

[1] የነዚያም ፡ [2] መሔድ ፡ [3] እቀጣሀለሁ ፡ ብለውሐል ፡

ቸው ፡ ውሀ ፡ ውሀ ፡ ሲሉ ፡ አንዱ ፡ የሜጫ ፡ መኰንን ፡ ወሰን ፡ ቢሠውር[1] ፡ የሚባል ፡ ፩ዋንጫ ፡ ውሀ ፡ ይስጡኝ ፡ ጃንሆይ ፡ ፫፻ ብር ፡ ልስጥ ፡ አለ ፡ ንጉሡም ፡ ሰምተው ፡ አላዘኑለትም ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፡ ሞተ ። የዚህንም ፡ ነገር ፡ ሚስቱ ፡ ስታለቅስ ፡

ጌታው ፡ የጌታው ፡ ልጅ ፡ ወሰን ፡ ቢሠውር ፡
ውሀ ፡ ልግዛ ፡ ይላል ፡ በ ፫፻ ብር ።

አለች ፨ ። ከዚህ ፡ ወዲህ ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ ተጣልተው ፡ እንግዳ ፡ ቅጣት ፡ ዠመሩ ። ሰውም ፡ መጨከነዎን ፡ እያየ ፡ ከሰፈር ፡ የወጣ ፡ ወገን ፡ እረኛውን ፡ በመንገድ ፡ ሲሄድ ፡ የተገኘውን ፡ ሁሉ ፡ ይገድል ፡ ዠመረ ። ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ገሥግሰው ፡ ቃሮዳ ፡ የሚባል ፡ የወይን ፡ ሀገር ፡ ደረሱ ፡ ከዚህም ፡ ሺ ፡ ከ ፺፻ ሕፃናት ፡ ሳይቀሩ ፡ ያዙ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እንግዳ ፡ ቅጣት ፡ አምጥተው ፡ ይህን ፡ የተያዘ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ቤት ፡ እየቈጠሩ ፡ አስገብተው ፡ በእሳት ፡ አቃጠሉት ፡ ሲጨንቀውም ፡ ቤቱ ፡ እየቀደደ ፡ እንዳይወጣ ፡ በዙሪያው ፡ እየተሰለፈ ፡ ነፍጠኛ ፡ ጋሻኛ ፡ አለበት ። ይህም ፡ ቅጣት ፡ ለንጉሡ ፡ እጅግ ፡ ተወደደ ። ተመልሰውም ፡ ከአሙስ ፡ ወንዝ ፡ ከአሞራ ፡ ገደል ፡ ከጠጉር ፡ የተያዘውን ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ተናገርነው ፡ በእሳት ፡ አቃጠሉት ፡ እንዲህም ፡ ሲደረግ ፡ ቤቱ ፡ ሲቃጠል ፡ ለባለቤት ፡ ዋጋ ፡ ይሰጡ ፡ ነበር ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ ሲበዛ ፡ ቀርቷልና ፡ ከብዛቱ ፡ የተነሣ ፡ ይመስላል ። በዚህም ፡ ዘመን ፡ ወደ ፡ ማኅደረ ፡ ማርያም ፡ ወርደው ፡ ካህናቱ ፡ እንደ ፡ ሥርዓት ፡ ሊቀበሉ ፡ ወጡ ፡ ከለቻ ፡ የሚባል ፡ ሜዳ ፡ ከገቢያው ፡ አጠገብ ፡ አለ ፡ ከዚያ ፡ ቈመው ፡ በጸናጽል ፡ በከበሮ ፡ እያመሰገኑ ፡ ሲረ

---

[1] ቢሰውር ፡



ግጡ ፡ ነፍጠኛን ፡ ዙሪያውን ፡ ከበበው ፡ ብለው ፡ አስፈጁዋቸው ፡ የነዚህም ፡ ቍጥር ፡ ፬፻፺[1] ሆነ ። በከተማው ፡ ውስጥ ፡ የቀረ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳወጣው ፡ እየሸሸ ፡ አመለጠ ፨ ። ከዚህ ፡ ተመልሰው ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ወጡ ፡ ከዚህም ፡ ገሥግሰው ፡ ከርብ ፡ ዠምረው ፡ እስከ ፡ ፍርቃ ፡ በር ፡ ወራሬ ፡ ቢለቁበት ፡ ሲያርስም ፡ ሲቈፍርም ፡ በመንገድም ፡ ሲሄድ ፡ የተገኘው ፡ ፺ ሺ ፡ ከ ፺፻ ሆነ ፡ ይህነንም ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ተናገርነ ፡ በይፋግ ፡ ከተማ ፡ ቤት ፡ እያስገቡ ፡ አነደዱት ፡ ከመንገድ ፡ በላይ ፡ በታችም ፡ የነበረ ፡ ቤት ፡ ሁሉ ፡ በሰው ፡ መቃጠል ፡ አለቀ ። እንዲህም ፡ ባለቀ ፡ ጊዜ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ላይ ፡ እርጉዝ ፡ እመጫትም ፡ ወንዱም ፡ እየተያዙ ፡ መጥተው ፡ ሲቃጠሉ ፡ ቢመሽ ፡ ቤትም ፡ ቢያልቅ ፡ ከሜዳ ፡ ላይ ፡ እየጠበቁ ፡ በዝናም ፡ ራቁታቸውን ፡ አደሩ ። በማግሥቱ ፡ ለማቃጠል ፡ ከቤት ፡ ሲገቡ ፡ የ ፫ዓመት ፡ ልጅ ፡ እናቱን ፡ እጁዋን ፡ ይዞ ፡ እንደ ፡ ትላንት ፡ ዝናም ፡ እንዳይመታን ፡ ነይ ፡ ቶሎ ፡ እንግባ ፡ እያለ ፡ ሲያለቅስ ፡ እናቱም ፡ ስታለቅስ ፡ አይተው ፡ ጠየቁ ፤ የልጁንም ፡ ነገር ፡ በሰሙ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ምነው ፡ እንዲህ ፡ ታደርገኛለህ ፡ ወይ ፡ እኔን ፡ ቶሎ ፡ ግደል ፡ ፍጥረትህ ፡ ይረፍ ፡ ብለው ፡ አልቅሰው ፡ ሊቃጠሉ ፡ የቀረቡትን ፡ ሁሉ ፡ ምረውት ፡ በየሀገሩ ፡ ገባ ። አንዱም ፡ ከቤቱ ፡ ውስጥ ፡ የእህል ፡ ጐድጓድ ፡ ኑሮ ፡ ሳያውቀው ፡ ገብቶበት ፡ ሰው ፡ አልቆ ፡ እሳቱ ፡ ሲበርድ ፡ አውጡኝ ፡ እያለ ፡ ጮኸ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የክርስቶስን ፡ ነገር ፡ አድንቀው ፡ አወጡት ፨ ። ይህም ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ ተነስተው ፡

---

[1] ፬፻ ከ ፺ ፡

በጣና ፡ ውስጥ ፡ የምትኖር ፡ ምጽርሐ ፡ ትባላለች ፡ ይሴት ፡
ናት ፡ ቢወርዱ ፡ ሳይሆንልዎ ፡ ተመለሱ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ብዙ ፡
ጦር ፡ መድፍም ፡ ይዘው ፡ ወርደው ፡ እየተዋጉ ፡ ገቡ ፡ በ
ዚያ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ብርቱ ፡ በታንኳ ፡ ሲያመልጥ ፡
የቀረውን ፡ ሁሉ ፡ በየቤቱ ፡ እያስገቡ ፡ እንደ ፡ ይፋግ ፡ አነደ
ዱት ፡ ተመልሰው ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ገቡ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡
የበጌ ፡ ምድር ፡ አልቃሽ ፡

እግዜርና ፡ ንጉሥ ፡ ተጣልተው ፡ ቁመው ፡
ቅዱስ ፡ ሚካኤልን ፡ ደኛ ፡ አስቀምጠው ፡
እግዜር ፡ በግራ ፡ ነው ፡ ንጉሡ ፡ በቀኝ ፡
በል ፡ ፍጅና ፡ ስጠኝ ፡ ሲሉ ፡ ሰማሁኝ ፤

አለች ። የጐጃምም ፡ አልቃሽ ፡ ሜጫን ፡ በዘረፉት ፡ ጊዜ ፡

ልብሴንም ፡ ገፈፈው ፡ ለበሰው ፡ እርዘኛ ፡
በሬዬንም ፡ ነዳው ፡ አረደው ፡ ነፍጠኛ ፡
እህሌንም ፡ ዘረፈው ፡ በላው ፡ ቀለበኛ ፡
ንጉሥ ፡ የቀረዎ ፡ ጥቂት ፡ አማርኛ ፡
ምነው ፡ ሆድ ፡ አይዘርፉ ፡ አርፌ ፡ አንድተኛ ፤

አለችና ።

አገሬን ፡ ዘረፈው ፡ አያለው ፡ ደስ ፡ ደስ ፡
ሞኙ ፡ በጌምድሬ ፡ ፈንታው ፡ እስኪደርስ ፤

አለች ። ፈንታ ፡ ያለችውም ፡ የቤገምድር ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በ
ቴዎድሮስ ፡ አዳይነት ፡ የመከራ ፡ ጽዋ ፡ በራብ ፡ በእሳት ፡ ተ
ቀበለ ። በየዕለቱ ፡ በማናቸውም ፡ ነገር ፡ እየተያዘ ፡ የሚሞ
ተው ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ልማድ ፡ ሁኖ ፡ ቍጥር ፡ የለውም ። ይ
ህም ፡ የንጉሡ ፡ ሰፈር ፡ ዙሪያው ፡ በእሾህ ፡ ከሰው ፡ ቁመት ፡
በልጦ ፡ ታጥሮ ፡ ነበረ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ቢሉ ፡ ንጉሡ ፡ ከሀገር ፡



ሁሉ ፡ ተጣሉ ፡ በሌሊትም ፡ እንደ ፡ ጋላ ፡ እየወጋ ፡ ይሄድ ፡
ዠመረ ፡ የንጉሡም ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ከሰፈር ፡ እን
ዳይወጣ ፡ ጠላትም ፡ እንዳይገባ ፡ ሰለዚህ ፡ ጥበብ ፡ አጠ
ሩት ፨ ። በዚህም ፡ በራብ ፡ ሰው ፡ ያልቅ ፡ ዠ
መረ ፡ ከረኃቡ ፡ ጥናት ፡ የተነሣ ፡ እመጫት ፡ ልጅዋን ፡ ከዠ
ርባዋ ፡ እያወረደች ፡ ስትጥል ፡ የሚያነሳ[1] ፡ እየጠፋ ፡ ፈረስ ፡
በቅሎ ፡ ይሄድ ፡ ነበር ፡ በላዩ ። ስለ ፡ ምን ፡ እግዚአብሔር ፡
ይህን ፡ ራብ ፡ አመጣ ፡ ቢሉ ፡ አስቀድመው ፡ የበጌምድርን ፡
እህል ፡ ሁሉ ፡ ፩ ሳይቀር ፡ ዘርፈው ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ አግብ
ተው ፡ ከእህል ፡ በቀር ፡ ለፈረስ ፡ ለበቅሎ ፡ ለአህያም ፡ ሣር ፡
ገለባ ፡ አትስጥ ፡ ብለው ፡ ዓዋጅ ፡ ነገሩ ፡ የከብትም ፡ ቀለብ ፡
እንደ ፡ ሰው ፡ እህል ፡ ብቻ ፡ ሁኖ ፡ ፫ ወር ፡ ተቀመጡ ፡ እህ
ልም ፡ አለቀ ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ እንዳይዘርፉ ፡ አስቀድሞ ፡ እህሉ ፡
አልቋል ፡ ርቀው ፡ እንዳይሄዱ ፡ ጠላት ፡ በዝቷልና ፡ ስለዚህ ፡
ራብ ፡ በከተማው ፡ ጠና ፡ ፩ ቁና ፡ እህል ፡ በ ፩ ብር ፡ እየተሸ
መተ ፨ ። ደብረ ፡ ታቦርንም ፡ ሐዲስ ፡ ጐንደር ፡
በሉ ፡ ብለው ፡ ዓዋጅ ፡ ነገሩ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ቢሉ ፡ ጐንደርን ፡
ከበጌምድር ፡ አስቀድመው ፡ ዘረፉት ፡ ከአፄ ፡ ፋሲል ፡ ዠ
ምሮ ፡ የነገሥታት ፡ ከተማ ፡ ነበረ ፡ ፩ ዘመንም ፡ ሁዳዴን ፡ ከ
ዚያው ፡ ተቀመጠው ፡ እስላምን ፡ ሁሉ ፡ በሃይማኖትህ ፡ ተከ
ራከር ፡ ብለው ፡ አቡነ ፡ ሰላማን ፡ የክርስቲያን ፡ ጠበቃ ፡ አድ
ርገው ፡ እየተረታ ፡ ክርስትና ፡ ገባ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የቅ
ዳሜ ፡ ሥዑር ፡ ቄጠማ ፡ ሰጥተው ፡ ከህናቱ ፡ ሲመለሱ ፡ ወታ
ደር ፡ እየተከተለ ፡ መጥቶ ፡ ቀሀን ፡ ተሻግሮ ፡ ዓቀበቱ ፡ ላይ ፡

---

[1] የሚያነሣ ፡

ልብስ ፡ ይገፍ ፡ ዠመረ ። ከዚህ ፡ ወዲህ ፡ በየቤቱ ፡ እየገባ ፡ ያገኘውን ፡ ሁሉ ፡ እየዘረፈ ፡ ወሰደ ። ደግሞም ፡ በየደብሩ ፡ ያለ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ በላዩም ፡ የነበረ ፡ መስቀል ፡ እያወረደ ፡ የቍስቋም ፡ ተለይቶ ፡ ዕቃ ፡ ግምጃ ፡ ሁሉ ፡ የወርቅ ፡ ምልክት ፡ ነበረው ፡ የደብረ ፡ ብርሃን ፡ ፪ መረዋ ፡ ትንሽና ፡ ትልቅ ፡ ሲመቱት ፡ ከሩቅ ፡ የሚሰማ ፡ ከየደብሩ ፡ የተገኘው ፡ መጽሐፍ ፡ ፱፻፷፩[1] ይህነን ፡ ሁሉ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ አወጡት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጐንደርን ፡ አጥፍተው ፡ ማነን ፡ ከተማ ፡ ያደርጋሉ ፡ እንዳይባል ፡ ስለዚህ ፡ ጐንደር ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ይሁን ፡ አሉ ። ይህነንም ፡ የጐንደር ፡ ዕቃ ፡ ከደብረ ፡ ታቦር ፡ አስነስተው[2] ፡ መቅደላ ፡ አገቡት ፡ የደብረ ፡ ብርሃን ፡ ትንሹ ፡ መረዋ ፡ ፩ ቁና ፡ ይፈጃል ፡ ባንድ ፡ መቅደላ ፡ መጥቶ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁኖ ፡ ነበር ። ትልቁ ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ መጥቶ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ የማይቻል ፡ ሁኖ ፡ ቀርቷል ። በዚህም ፡ ዘመን ፡ በኅዳር ፡ ፮ ቀን ፡ ሌሊቱን ፡ የሰማይ ፡ ከዋክብት ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ሽብር ፡ ወዲህና ፡ ወዲህ ፡ ሲራወጡ ፡ አደሩ ። በ ፳፩ ቀን ፡ የጐንደር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በከተማው ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ አቃጠሉ ፡ ከከተማው ፡ የራቀው ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ተረፈ ፨

። በዚህም ፡ ዘመን ፡ አቡነ ፡ ሰላማን ፡ ንጉሡ ፡ ተጣልተው ፡ ክህነትም ፡ እንዳይሰጡ ፡ ከልክለው ፡ በመቅደላ ፡ ፫ ዓመት ፡ ተቀመጡ ። በጐንደር ፡ ጥፋትም ፡ እጅግ ፡ አዘኑ ። ሰውም ፡ ከሰው ፡ ተጣልቶ ፡ ከቴዎድሮስ ፡ መዓት ፡ ይጣልህ ፡ እያለ ፡ ሲረግም ፡ ሲመርቅም ፡ ከቴዎድ

---

[1] ፱፻ ከ ፳፩ ፡ [2] አስነሥተው ፡



ሮስ ፡ በረከት ፡ ይክፈልህ ፡ ይል ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የነፍስ ፡ አሳብ ፡ አልነበረም ። ነገር ፡ ግን ፡ አቡነ ፡ ሰላማ ፡ ንጉሥ ፡ ምን ፡ ይልክን ፡ እጅግ ፡ ይወዱ ፡ ነበርና ፡ ከንጉሥ ፡ ምንይልክ ፡ ጋራ ፡ እንዲኖሩ ፡ ደብዳቤ ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ላኩ ። ይህስ ፡ ደብዳቤ ፡ ጳጳሱ ፡ የቁም ፡ እስር ፡ ሁነው ፡ እንዴት ፡ ተጥፎ ፡ ወጣ ፡ ቢሉ ፡ ይህን ፡ ታሪክ ፡ የጣፈ ፡ ሀገሩ ፡ ሸዋ ፡ ምሁይ ፡ ቄላ ፡ ወረው ፡ ነው ፡ ስሙም ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ይባላል ። በፍቅርም ፡ ልጅ ፡ ሁኖ ፡ ከአቡነ ፡ ሰላማ ፡ ጋራ ፡ ሲኖር ፡ ደብዳቤ ፡ ጻፍልኝ ፡ አሉት ፡ እርሱም ፡ የሀገሬ ፡ ንጉሥ ፡ ቢመጣልኝ ፡ ሀገሬ ፡ እገባለሁ ፡ እበቃለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ደብዳቤ ፡ በመንገድ ፡ የተያዘ ፡ እንደሆነ ፡ ንጉሡ ፡ ጣፊውን ፡ አምጡ ፡ ይላሉ ፡ በተገኘሁ ፡ ጊዜ ፡ ዓይኔ ፡ ሲያይ ፡ ገደል ፡ ይጥሉኛል ፡ ሲል ፡ እጅግ ፡ ተጨነቀ ። ከዚህ[1] ፡ በኋላ ፡ ብሞትም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ቸርነቱ ፡ ያድርግልኝ ፡ ብሎ ፡ ጥፈት ፡ ዠመረ ። ደግሞም ፡ እጅግ ፡ ቢፈራ ፡ ለጳጳሱ ፡ የጥበብ ፡ ቀለም ፡ አበጅቶ ፡ ከመንገድ ፡ ቢያዝም ፡ በተጻፈው ፡ ወረቀት ፡ ቀለሙ ፡ አይታይም ፡ ኋላ ፡ በብልሐት ፡ ቀይ ፡ ሁኖ ፡ ይገለጣልና ፡ ከጌታዬ ፡ ከንጉሡ ፡ ሲደርስ ፡ አሁንም ፡ በዚህ ፡ ልጣፈው ፡ አለዎ ፡ ጳጳሱም ፡ ጥፈህ ፡ አሳየኝ ፡ አሉት ፡ እርሱም ፡ እንደ ፡ ጥበቡ ፡ ጥፎ ፡ ሰጠዎ ፡ አይተው ፡ ጥበብህ ፡ ደግ ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሃይማኖት ፡ እንዳይጐድል ፡ በጥቁር ፡ ቀላም ፡ ጣፈው ፡ እግዚአብሔር ፡ በሃይማኖት ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡ ጠብቆ ፡ ከልጄ ፡ ከምን ፡ ይልክ ፡ ሸዋ ፡ ይደርስልኛል ፡ አሉ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ተጥፎ ፡ ለጳጳሱ ፡ የሃይማኖት ፡ ልጅ ፡

---

[1] ከዚህም ፡

መምህር ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ ተቀብለው ፡ ሸዋ ፡ ለንጉሥ ፡ ምን ፡ ይልክ ፡ ሰጡ ፨ ። በዜህም ፡ ጊዜ ፡ አቡነ ፡ ሰላማ ፡ መቅደላ ፡ ሁነው ፡ በሰኔ ፡ ዠምሮ ፡ ሳል ፡ ታመው ፡ ነበር ፡ እንቅልፍ ፡ አጥተው ፡ ከምታት ፡ የተነሳ ፡ በንጉሡም ፡ ስራ ፡ እየተናደዱ ፡ በ ፯ ሺ ፡ ከ ፫፻፶፫ ዓመት ፡ በዘመነ ፡ ዮሐንስ ፡ በ ጥቅምት ፡ በ ፲፫ ቀን ፡ ዓርብ ፡ ፱ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ እንዳባቶ ችዎ ፡ አረፉ ። መግነዝና ፡ ፍታት ፡ በሠርክ ፡ ተዠምሮ ፡ እ ስከ ፡ ማግስቱ ፡ ሠርክ ፡ ያረፈ ፡ የለም ፤ ከዚህ ፡ ወዲህ ፡ በሳ ጥን ፡ አግብተው ፡ በብዙ ፡ ጥበብ ፡ ስራ ፡ ገጥመው ፡ ላዩን ፡ በቀይ ፡ ሐር ፡ ለብጠው ፡ ከሣጥኑ ፡ በላይ ፡ ወርቅ ፡ ዘቦ ፡ ግ ምጃ ፡ አልብሰው ፡ በምሥራቅ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አግብ ተው ፡ በአልጋ ፡ አኖሩዎ ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የተደረገ ፡ ሥር ዓት ፡ ለጽፈት ፡ እንዳይበዛ ፡ ቀርቷል ፨ ። ይህ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ በኅዳር ፡ በ ፳ ቀን ፡ ንጉሡ ፡ ሸዋ ፡ ምን ፡ ይልክ ፡ መጥተው ፡ በጅፋ ፡ በላይ ፡ ሰፈሩ ። ስለ ፡ ምን ፡ ቢሉ ፡ የጳጳሱ ፡ ቃል ፡ ኀዘንም ፡ ሁሉ ፡ በመምህር ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ እጅ ፡ በጠማር ፡ ሁኖ ፡ ከመቅደላ ፡ መጥቶልዎ ፡ ያዝኑልዎ ፡ ነበርና ፡ ለማውጣት ፡ ይመስላል ፡ በኛ ፡ ዕውቀት ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ከአምባ ፡ ማርያም ፡ ተነሥተው ፡ በ ፳፩ ቀን ፡ ተንታ ፡ ሲደርሱ ፡ የመድፉን ፡ የነፍጡን ፡ የፈረሱን ፡ የእግሩን ፡ ሰ ልፍ ፡ አድርገው ፡ ለመቅደላ ፡ ቢታዩ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ከኛ ፡ የነበረ ፡ ምን ፡ ይልክ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ፍጥረት ፡ በመንግሥት ፡ ይዞ ፡ ወጣ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚሳነው ፡ ነገር ፡ የለም ፡ እያለ ፡ ሲያደንቅ ፡ የሚወደዎ ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ መቅደላ ፡ ቢቀርብልን ፡ ወጥተን ፡ የምን ዋጋው ፡ እየመሰልነ ፡ ሸዋ ፡ በገባን ፡ እያለ ፡ ተመኘ ፡ ንጉሥ ፡



ምን ፡ ይልክን ፡ የማይወድ ፡ አልነበረምና ። በመቅዳላም ፡ ሲኖሩ ፡ በንቍጣጣሽ ፡ በመስቀል ፡ በፈረስ ፡ ጕግስ ፡ ጨወታ ፡ ንጉሥ ፡ ምን ፡ ይልክን ፡ የሚመስል ፡ አይታይም ፡ ነበር ። በዚህም ፡ መወደድዎ ፡ ሸዋ ፡ ከአባትዎ ፡ ሀገር ፡ ሲገቡ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ በጋዲሎ ፡ የሰራልዎ ፡ ነገር ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ በመ ቅደላ ፡ ሲነገር ፡ ዋለ ፡ ይህስ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ተናገርነ ፡ ከመቅደላ ፡ ንጉሥ ፡ ምን ፡ ይልክ ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ ጋዲሎ ፡ ሲደርሱ ፡ በዛብህ ፡ የሚባል ፡ እገዛለሁ ፡ የሚል ፡ ነበር ። ለአፄ ፡ ቴዎድሮስም ፡ ፈቃደኛ ፡ ሁኖ ፡ ፩ ጊዜ ፡ ግብር ፡ ይዞ ፡ እስከ ፡ ወሎ ፡ መጥቶ ፡ ጅፋ ፡ ላይ ፡ ሰጥቶ ፡ ከንጉሡ ፡ ባይተማመን ፡ ሌሊት ፡ ተነ ሥቶ ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ መጣ ። በዜህም ፡ ጊዜም ፡ ፩ የበጌምድር[1] ፡ ወታደር ፡ ለሸዋ ፡ ወታደር ፡ በፈሊጥ ፡ ሲነግረው ፡ ፈረስ ፡ የሚገዛ ፡ መስሎ ፡ ፈረስ ፡ ያለህ ፡ ብር ፡ ቢለው ፡ ፈሊጡን ፡ ሳያውቅ ፡ አልሸጥም ፡ አለ ። ይህን ፡ ጊዜ ፡ የአማርኛ ፡ ድኃ ፡ ብሎት ፡ ሄደ ። ከዚህም ፡ ወዲህ ፡ ለቴዎድሮስ ፡ አልገዛም ፡ ብሎ ፡ ከመንዝ ፡ አፍቀራ ፡ የሚባል ፡ ገብቶ ፡ ተቀመጠ ። ንጉ ሡም ፡ ከቤገምድር ፡ መጥተው ፡ ሊዋጉት ፡ ቢቀርቡ ፡ ለመ ድፍ ፡ ራቀ ፡ ጦርም ፡ እንዳይቀርብ ፡ አምባው ፡ በሩ ፡ ጥኑ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሳይሰብሩት ፡ ቀረ ። ከዚህ ፡ ወዲህ ፡ ወንዙን ፡ በዓ ደባይ ፡ ወርደው ፡ መራቤቴን ፡ ዘርፈው ፡ ሰውም ፡ ከመ ቸገር ፡ የተነሳ ፡ ባንድ ፡ ተከትሎ ፡ ሄደ ፡ ከሞት ፡ የተረ ፈው ፨ ። እንግዴህ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ምን ፡ ይ ልክ ፡ ታሪክ ፡ እንመለስ ፡ ጋዲሎ ፡ ሲደርሱ ፡ ንጉሥ ፡ የን

[1] በጌ ፡ ምድር ፡

ጉሥ ፡ ልጅ ፡ ምን ፡ ይልክ ፡ መጣልን ፡ እያለ ፡ ወሬ ፡ በየሀገሩ ፡ ሲገባ ፡ በዛብህ ፡ ከደብረ ፡ ብርሃን ፡ ተነስቶ ፡ ንጉሥ ፡ ምን ፡ ይልክን ፡ ሊዋጋ ፡ መጣ ፤ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ጦር ፡ ሲሆን ፡ እግዚአብሔር ፡ ከንጉሥ ፡ ምን ፡ ይልክ ፡ ጋራ ፡ ሁኖ ፡ ሁሉም ፡ ድል ፡ ሆነ ። በዛብህም ፡ ፳ ሁኖ ፡ ከዚያ ፡ የሸሸ ፡ አፍቀራ ፡ ገብቶ ፡ ተቀመጠ ። ከዚህ ፡ ወዲህ ፡ ምሥራቁን ፡ ተጕዘው ፡ ሾላ ፡ ሜዳ ፡ ሲደርሱ ፡ ወይዘሮ ፡ ባፈና ፡ ተገናኙ ። ከዚህም ፡ አልፈው ፡ ዓዋዲን ፡ ተሻግረው ፡ አራምባ ፡ ገቡ ። ይህም ፡ አራምባ ፡ የጥንት ፡ ያባቶችዎ ፡ ከተማ ፡ ነው ፡ ወግም ፡ ሥርዓትም ፡ ይነገርበታል ። ከዚህም ፡ ተነስተው ፡ ማኽል ፡ ወንዝ ፡ ደርሰው ፡ አንኮበር ፡ ከአባትዎ ፡ ከተማ ፤ ሲገቡ ፡ በካህናቱ ፡ በሕዝቡም ፡ የተደረገው ፡ ደስታ ፡ ለሁሉ ፡ ተረፈ ። ካህናቱም ፡ ሕዝቡም ፡ ከደስታቸው ፡ የተነሣ ፡ እናቶቻቸው ፡ ላሞች ፡ ሲመጡ ፡ የተፈቱ ፡ ጥጆች ፡ መሰሉ ። ይህም ፡ የተደረገ ፡ በነሐሴ ፡ በ፳፬ ቀን ፡ ነው ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ደብረ ፡ በርሃን ፡ ወጥተው ፡ ሲቀመጡ ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ተናገርን ፡ በዛብህ ፡ አፍቀራን ፡ አልለቅም ፡ ብሎ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበርና ፡ አማላጆች ፡ ይማሩልን ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ምን ይልክ ፡ መጡ ። ንጉሡም ፡ አይተው ፡ እንደ ፡ ወንጌል ፡ ቃል ፤ ኩኑ ፡ የዋሀነ ፡ ከመ ፡ ርግብ ፡ ወኩኑ ፡ ጠቢባነ ፡ ከመ ፡ አርዌ ፡ ምድር[1] ፡ ይላልና ፡ ምሬዋለሁ ፡ አሉ ። ከዜህ ፡ በኋላ ፡ መጥቶ ፡ ልቹ ፡ በግብር ፡ ቀን ፡ ከአዳራሽ ፡ ሲገባ ፡ የልቡናን ፡ ምሥጢር ፡ እግዚአብሔር ፡ ያውቃል ፡ ይመረምራልና ፡ በንጉሡ ፡ ቅንነት ፡ እግዚአብሔር ፡ ተጨምሮ ፡ ተይዞ ፡ ታሠረ ።

[1] neuf mots gheez.



ኋላ ፡ ግን ፡ ከአደባባይ ፡ ፍርድ ፡ ሲወጣ ፡ ሞቱን ፡ ተቀብሎ ፡ አረፈ ። ይህም ፡ ቅጣት ፡ በየሀገሩ ፡ ቢሰማ ፡ የንጉሥ ፡ ኃይል ፡ ተፈራ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድም ፡ ለንጉሥ ፡ ምን ፡ ይልክ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ እንዳይሆን ፡ በዳዊት ፡ ቃል ፡ ወአኅሥሮ ፡ ለዕቡይ[1] ፡ ብሎ ፡ ተናግርዋል[2] ፡ ትቢተኛን ፡ አዋርደው ፡ ሲል ፥ ። እንግዴህ ፡ ጥንተ ፡ ነገር ፡ እንመለስ ፡ በበጌምድር ፡ ቴዎድሮስ ፡ ከሞት ፡ የቀረ ፡ ሠራዊትዎን ፡ ይዘው ፡ ሲኖሩ ፡ በሰፈርዎ ፡ ሰው ፡ ቢሞት ፡ ዘመድ ፡ ለዘመዱ ፡ እንዳያለቅስ ፡ ልቅሶ ፡ ተከልክሎ ፡ ዕንባውን ፡ ያጠጣ ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ማኻከል ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ሞቱ ፡ መርዶ ፡ ለይተጌ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ወደ ፡ መቅደላ ፡ ሲልኩ ፡ ሁሉንም ፡ ለደጃች ፡ ውቤ ፡ አልቅሱልኝ ፡ ብለው ፡ አዘዙ ። የሰውም ፡ ሁሉ ፡ በየዘመዱ ፡ የቀረበት ፡ ልቅሶ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ወጣለት ። የቤገም ድርም ፡ አልቃሽ ፡

የኔታ ፡ ደጅ ፡ አዝማች ፡ ሁለግዜ ፡ ደግነት ፡
ዛሬ ፡ እንኳ ፡ ለድኃው ፡ እንባ ፡ አስተረፉለት ፡

አለች ፥ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ሲኖሩ ፡ በጥቅምት ፡ በ፩ ቀን ፡ ዓርብ ፡ ተነስተው ፡ ያንዱን ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ በ፲፰ ቀን ፡ በ፳ ቀን ፡ እየተጓዙ ፡ መጥተው ፡ ጎራዳ ፡ ጥድ ፡ ሰፈሩ ። ስለምን ፡ እንዲህ ፡ ተጓዙ ፡ ቢሉ ፡ ቦምባ ፡ የሚሉት ፡ መድፍ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታይቶ ፡ የማያውቅ ፡ ታለቅነቱም ፡ ሰው ፡ እየገባ ፡ የሚወጣበት ፡ ይህነን ፡ አሰርተው ፡ ይዘው ፡ ነው ። በዚህ ፡ ዘመን ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ ነበረበት ፡ በየሀገሩ ፡ በመቅደላም ፡ ሌሊት ፡ እየገባ ፡ የቡዳ ፡

[1] deux mots gheez. [2] ተነግሯል ፡

ጅብ፡ሲበላ፡ሰውን፡ሁሉ፡አስጨነቀ፡በዚህም፡ጭንቅ፡
ነፍጠኛ፡ሁሉ፡መክሮ፡በየደጁ፡ሲተኩስ፡ብዙ፡ጅብ፡
አለቀ። አለቀ፡ዘነብ፡የሚባልም፡ለአፄ፡ቴዎድሮስ፡የተ
ወደደ፡ጸሐፊ፡የሸዋ፡ሰው፡ነበረ፡ለብቻው፡፲፩ ጅብ፡
ከደጁ፡ላይ፡ገደለ። ነብርም፡እንደዚሁ፡እየገባ፡ቤት፡
እየቀደደ፡መዝጊያ፡እየከፈተ፡ሰው፡ሲጣላ፡በመቅደላ፡
የሚተኛ፡የሚያርፍ፡አልነበረም፡ከፍርሀት፡የተነሣ፤በዚ
ህም፡ጊዜ፡በካፊር፡በር፡የደምቢያ፡ሰፈር፡የሚሉት፡
አለ፡፩ ወታደር፡ከቤቱ፡ተኝቶ፡ድመት፡መጣና፡በላዩ፡
ተኛ፡እርሱም፡ሲከብደው፡ጊዜ፡ይህን፡ነገር፡ምንድር፡
ነው፡አለና፡ቢንቀሳቀስ፡ድመትም፡በጥፍሩ፡ቢቈነጥጥ፡
ያው፡ነብር፡መስሎት፡ጩኸቱን፡ለቀቀ፡ሰዎችም፡ተሰ
ብስበው፡መዝጊያውን፡በግድ፡ከፍተው፡በመብራት፡ቢ
ያዩት፡ድመት፡ሆነ። ደግሞ፡በ፩ ስፍራ፡በጎታ፡ላይ፡የነ
በረ፡አገልግል፡ድመት፡ሲነካው፡ከሰው፡ላይ፡ሲወድቅ፡
አይጥም፡በሰው፡ላይ፡ስትሄድ፡በዚህ፡ኍሉ፡ጩኸት፡
ነበረ። ቡዳ፡መሆኑም፡በጅቡ፡ዠሮ፡ባንገቱም፡ምልክት፡
ተገኘበት። ነብሩም፡በገደሉት፡ጊዜ፡አካሉን፡ከ፪ ስፍራ፡
ቀበሩ፡በማግስቱ፡የሁለቱም፡ተቈፍሮ፡ወጥቶ፡ተገኘ፡
ይህ፡የቡዳ፡ጥበብ፡ይበላልና፡በዚህ፡ታወቀ፨ ።
እንግዴህ፡ወደ፡ቴዎድሮስ፡ታሪክ፡እንመለስ፡ይህስ፡በ
ምባ፡ከምን፡ተሰራ፡ቦታው፡ሰሪዎቹስ፡የት፡ናቸው፡ቢሉ፡
ጐንደር፡በተዘረፈ፡ጊዜ፡ከንዋየ፡ቅድሳት፡ወገን፡ንቅ፡
ያለበትን፡ሰባራውን፡እያዩ፡ዋጋው፡እየተገመተ፡ብሩን፡
እየሰጡ፡፴፪፫ ተገኘ፡ከመቅዳላም፡የነበረ፡፩፩ ቁና፡የሚ
ፈጅ፡፶የናስ፡ዋንጫ፡ተጨመረ፡በቀረውም፡የሀገር፡ናስ፡



ነው። ቦታውም፡በደብረ፡ታቦር፡አጠገብ፡ጋፋት፡ይባ
ላል። ሰሪዎቹም፡ከእንግሊዝ፡ከፈረንጅ፡ከሌላም፡ሀገር፡
እነዋልትማየር፡ነበሩ። ይህነንም፡በመንኰራኵር፡አድር
ገው፡ሲሄድ፡በፊቱ፡፫ ቀላድ፡አለ፡፶፶ ሰው፡እየሆነ፡ይ
ስባል። ሲሳብም፡በቍልቍለት፡ወደ፡ፊት፡እንዳይወረ
ወር፡ዓቀበቱን፡ሲወጣ፡ወደ፡ኋላ፡እንዳይገለበጥ፡መ
ያዥ፡መዘውር፡አለው። ጨጨሆ፡ሲደርስ፡ቍልቍለ
ቱን፡እንደሜዳ፡አስተካክለው፡ደልድለው፡ከመንገዱም፡
ላይ፡ደንጊያ፡ሰጎጥ፡የተገኘ፡እንደሆነ፡ጣት፡የሚያስ
ገባ፡ያህል፡ደንጊያውን፡ሰርስረው፡ከ፫ ት፡ከ፬ ላይ፡የእ
ንግሊዝ፡ባሩድ፡በሸዋ፡አማርኛ፡ይባላል፡ዳሄራ፡ይኽ
ነን፡እየጨመሩ፡ሲተኰስ፡ያደንጊያ፡ያደቃል፡ሜዳ፡ሲ
ሆን፡ጉዞ፡ይዠመራል፡መንገዱን፡ሁሉ፡እንዲህ፡እያደ
ረጉ፡በዋድላ፡ወጥተው፡ቿጣ፡ከወንዙ፡ሲደርስ፡ወርኍ፡
ታህሣሥ[1]፡ነበር፡ዘመኑም፡ዮሐንስ፡ነውና፡ልደትን፡
በ፳፰ ቀን፡አከበሩ፡ጥምቀትንም፡ከዚያው፡ዋሉ። ከዚ
ያም፡ተጕዘው፡በመጋቢት፡በ፳፪ ቀን፡ከመቅዳላ፡እግር፡
ሰላምጌ፡ገቡ፡ቀኑም፡ረቡዕ፡ነው። በማግሥቱ፡የመቅ
ደላን፡ካህናት፡ናፍቆያቸዋለሁና፡ይምጡና፡ልያቸው፡
ብለው፡ለራስ፡ቢሠውር፡ላኩ። ካህናቱም፡በሥርዓት፡
ሁነው፡ለብሰው፡መስቀል፡ይዘው፡ወረዱ። ንጉሡም፡
ከገቢያው፡ላይ፡ሰፍረው፡ነበሩ። በዚህ፡ጊዜ፡ካህናቱ፡
እጅ፡ነስተው፡ቈመው፡ሳሉ፡ንጉሡ፡በቁጣ፡ቃል፡አቡ

---

[1] ተኅሣስ፡

ንና ፡ እጨጌ ፡ የሚባሉ ፡ ሰዎች ፡ ሀገሩን ፡ ሁሉ ፡ ሲያስፈጁት ፡
ታያላችሁን ፡ አሉ ። እጨጌም ፡ ከካህናቱ ፡ ጋራ ፡ ቁመው ፡
ይህን ፡ ሲሰሙ ፡ ጃንሆይ ፡ ምን ፡ አልሁ ፡ ምን ፡ አጠፋሁ ፡ ጥፋት ፡
እንዳለብኝ ፡ ከሥራዊትዎ ፡ ይንገሩብኝና ፡ ልቀጣ ፡ ብለው ፡
ደንጊያ ፡ በቆብዎ ፡ ላይ ፡ ተሸክመው ፡ ቢወድቁ ፡ ንጉሡ ፡
የምህረት ፡ ቃል ፡ አልመለሱም ። በዚህ ፡ መኻከል ፡ መቅ
ደላ ፡ የኖሩ ፡ አባ ፡ ገብረ ፡ ሚካኤል ፡ የትግሬ ፡ ሰው ፡ ከካህ
ናቱ ፡ ጋራ ፡ ነበሩና ፡ ጃንሆይ ፡ በእስክንድርያ ፡ ሃይማኖት ፡
ይጽኑልን ፡ አሉ ። ንጉሡም ፡ ከእስክንድርያ ፡ ሌላ ፡ የማ
ነን ፡ ይገኜአለሁ ፡ ቢሉ ፡ የፈረንጅን ፡ ሃይማኖት ፡ ይዘዋል ፡
ይሉናል ፡ አሉዎ ። ፈረንጆችን ፡ አስጠርተው ፡ ንጉሡ ፡ መ
ስክሩ ፡ አሏቸው ፡ እነዚያም ፡ አንድ ፡ አንዱ ፡ እየተነሱ ፡ ሲ
መሰክሩ ፡ እኛ ፡ ተምረን ፡ አስተማሪዎች ፡ አይዶለንም ፡ የሃ
ይማኖትም ፡ ነገር ፡ ጠይቀውን ፡ አያውቁም ፡ አሉ ። በዚህ ፡
ጊዜ ፡ የቆሙትን ፡ ካህናት ፡ ተቀምጣችሁ ፡ ፍረዱ ፡ ሲሉ ፡
አለቃ ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስን ፡ ንጉሡ ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ ጠየቁዎ ፡
እንዲህ ፡ ብለው ፡ ሳኦል ፡ አቤሜሌክን ፡ ከካህናቱ ፡ ያስገደ
ለው ፡ ስለ ፡ ምን ፡[1] አሉ ። አለቃ ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስም ፡ ሲመ
ልሱ ፡ ሳኦል ፡ ለዳዊት ፡ ጌታው ፡ ወዳጁ ፡ ነበር ፡ ዳዊትም ፡
ለሳኦል ፡ አሽከር ፡ ባለሟል ፡ ሁኖ ፡ ሲኖር ፡ ኢይወጽእ ፡ ምስ
ፍና ፡ ወምልክና ፡ እምአባሉ ፡ ለይሁዳ[2] ፡ እንዳለ ፡ ከይሁዳ ፡
ዘር ፡ እንጂ ፡ ከሌላ ፡ አይወጣም ፡ ተብሎ ፡ ይነገራልና ፡ ይነ
ግሥብኻል ፡ እያሉት ፡ ጠልቶት ፡ ይኖር ፡ ነበር ። ከብዙ ፡

---

[1] ስለምን ፡ ነው ፡ [2] gheez.



ቀንም ፡ ፩ ቀን ፡ ለጉዳዩ ፡ ወደርሱ ፡ ገብቶ ፡ ጦር ፡ አንስቶ ፡
ወረወረበት ። እርሱም ፡ በክርስቶስ ፡ ኃይል ፡ ድኖ ፡ የሳኦል ፡
ልጅ ፡ ሜልኮል ፡ ሚስቱ ፡ ነበረችና ፡ ሸሽቶ ፡ ከርሰዋ[1] ፡ ቢ
ገባ ፡ ከንጉሡ ፡ ታዘው ፡ የሚፈልጉት ፡ መጡ ፡ ቢገቡባት ፡
ዳዊትን ፡ የታመመ ፡ አስመስላ ፡ ባልጋው ፡ አስተኝታ ፡ ል
ብሱን ፡ በበግ ፡ ደም ፡ አሳይታ ፡ ዳዊትስ ፡ እንዲህ ፡ ኮነ ፡ አለ
ቻቸው ። እነዚያም ፡ መልክተኞች ፡ ነገሩዋ ፡ አውነት ፡ መ
ስሏቸው ፡ ተመልሰው ፡ ለሳኦል ፡ ቢነግሩት ፡ ከነአልጋው ፡
ተሸክማችሁ ፡ አምጡት ፡ ብሎ ፡ መለሳቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡
ዳግመኛ ፡ እንደ ፡ መጡባት ፡ አይታ ፡ በመስኮት ፡ አሶጥታ ፡
ሰደደችው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሲሄድ ፡ ከአቤሜሌክ ፡ ቤት ፡ ገ
ብቶ ፡ አደረ ። አቤሜሌክም ፡ ለሳኦል ፡ የዳዊትን ፡ ወዳጅ
ነት ፡ ያውቃልና ፡ መጣልኝ ፡ የጌታዬ ፡ ወዳጅ ፡ ብሎ ፡ አሳ
ድሮ ፡ ሸኝቶ ፡ ሰደደው ። ሳኦልም ፡ ይህነን ፡ ሰምቶ ፡ ጠላ
ቴን ፡ እንዴት ፡ ተቀብሎ ፡ ሰደደው ፡ ሲል ፡ ተናደደ ፡ አቤ
ሜሌክም ፡ አላወቀ ፡ በንዲህ ፡ ያለ ፡ ከካህናቱ ፡ ጋራ ፡ ፻፰
ነበሩ ፡ በሰይፍ ፡ አስገደለው ፡ አሉ ። ንጉሡም ፡ ይህን ፡ ታ
ሪክ ፡ ሰምተው ፡ እንዲህ ፡ ሲሆን ፡ በፍርድን ፡ ነው ፡ ወይስ ፡
ያለ ፡ ፍርድ ፡ ብለው ፡ ጠየቁዎ ። አለቃ ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስም ፡
ከመጽሐፍ ፡ ትምህርት ፡ ጋራ ፡ እጅግ ፡ ፈሊጥ ፡ አማርኛ ፡
ያወቁ ፡ ሊቅ ፡ ነዎና[2] ፡ ሲመልሱ ፡ በፍርድ ፡ ነው ፡ ያልሁ ፡
እንደሆነ ፡ እጨጌን ፡ እንደ ፡ አቤሜሌክ ፡ እኛን ፡ እንደ ፡ ካ
ህናቱ ፡ አድርገው ፡ አሁን[3] ፡ በሰይፍ ፡ ያስፈጁናል ፡ አለ ፡

---

[1] ከርሥዋ ፡ [2] ነውና ፡ [3] አሁንም ፡

ፍርድ ፡ ነው ፡ ያልሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ንጉሥ ፡ አለ ፡ ፍርድ ፡
እንዴት ፡ ሰውን ፡ ያስገድላል ፡ ሲሉ ፡ ነገር ፡ ሊመጣብኝ ፡
ነው ፡ ብለው ፡ ተመለከቱና ፡ በፍርድ ፡ መሆኑን ፡ አላው
ቅም ፡ አሉ ⁘ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ካህናቱ ፡ ሲፈ
ርዱ ፡ ንጉሥን ፡ ያማ ፡ ይቀጣ ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ አባ ፡ ገብረ ፡ ሚ
ካኤል ፡ የፈረንጅን ፡ ሃይማኖት ፡ ይዘዋል ፡ ብለው ፡ ተናግረ
ዋልና ፡ ከንጉሡ ፡ ግፈፈው ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ሲወጣ ፡ ዙሪያ
ውን ፡ ቁሞ ፡ የነበረው ፡ ወታደር ፡ የአንገት ፡ ማተብ ፡ ሳይ
ቀር ፡ ተገፈው ፡ ራስ ፡ ቢሠውርን ፡ የማቅደላ ፡ ጠባቂ ፡ ነበ
ሩና ፡ አስጠርተው ፡ ይህን ፡ መነኰሴ ፡ አስረህ ፡ አኑረው ፡
ራብ ፡ ይግደለው ፡ ሲሉ ፡ ተቀብለው ፡ አስረው ፡ መቅደላ ፡
ገቡ ፡ በማግሥቱ ፡ ዓርብ ፡ አምጡ ፡ ብለው ፡ መነኰሴውን ፡
ፈትተው ፡ ሰደዱ ⁘ ። ከዚህ ፡ ወዲህ ፡ በመቅ
ደላ ፡ የሚኖሩ ፡ ካህናቱ ፡ ሁሉ ፡ በየቦታቸው ፡ ገብተው ፡ ለየ
ራሳቸው ፡ ሲያዝኑ ፡ ፈጣሪያቸውን ፡ ከዚህ ፡ ንጉሥ ፡ መ
ዓት ፡ እንዴት ፡ ታወጣን ፡ ይሆን ፡ እያሉ ፡ ይጨነቁ ፡ ነበር ፡
ምነው ፡ ቢሉ ፡ በንጉሡ ፡ በቴዎድሮስ ፡ ዘንድ ፡ ለመዓት ፡
የሚሆነው ፡ ለምሕረት ፡ ለምሕረት ፡ የሚሆነው ፡ ለመ
ዓት ፡ ይሆን ፡ ነበርና ፡ በማይሆን ፡ በጥቂት ፡ ነገር ፡ ያጠፉ
ናል ፡ ሲሉ ፡ ተጨነቁ ። ይህንም ፡ የሚያስረዳ ፡ ነገር ፡ በጕዞ ፡
ሲሄዱ ፡ በጭንቅ ፡ ስፍራ ፡ ከመንገድ ፡ ላይ ፡ ወታደር ፡ ከባ
ልደረቦቹ ፡ ብቻውን ፡ ተለይቶ ፡ ፩ ፈረስ ፡ ፪ አህያ ፡ ሲነዳ ፡
ፈረስ ፡ ለብቻው ፡ ወደቀ ፡ አህያም ፡ ጭነቱን ፡ ጣለ ፡ ይህን ፡
ጊዜ ፡ ያወታደር ፡ ለማናቸው ፡ ይሁን ፡ ተቸግሮ ፡ ጨንቆት ፡
ፈጣሪውን ፡ ሲያማርር ፡ ንጉሡ ፡ በኋላው ፡ ደርሰው ፡ ቢሰ



ሙት ፡ ለምን ፡ ፈጣሪህን ፡ ታማረዋለህ ፡ ይህን ፡ ንጉሥ ፡ ግ
ደልልኝ ፡ እንዳርፍ ፡ ብለህ ፡ ለምነው ፡ እንጂ ፡ አሉት ። እር
ሱም ፡ ሲመልስ ፡ ጃንሆይ ፡ አልሰማኝ ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ እኔስ ፡
ሀለጊዜ ፡ ለመንሁት ፡ አለ ። ቴዎድሮስም ፡ አውነትህ ፡ ብ
ለው ፡ ዝም ፡ ብለውት ፡ ሄደ ⁘ ። ፪ ተኛም ፡
ጎረዳ ፡ ጥድ ፡ ሰፍረው ፡ ከጐጃም ፡ የተድላ ፡ ጓሉ ፡ ወታደር ፡
ፈረሱን ፡ ይዞ ፡ መጥቶ፤ ከአደባባይ ፡ ቁሞ ፡ አስጠየቁት ፡
እርሱም ፡ ተናገረ ። የተድላ ፡ ጓሉ ፡ ወታደር ፡ ከኔ ፡ ምን ፡
አመጣህ ፡ ቢሉት ፡ ጃንሆይ ፡ እርሰዎን ፡ ብወድ ፡ ቢልዎ ፡
በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የያዘውን ፡ ፈረስ ፡ ተቀበለው ፡ ብለው ፡ ቅ
ረብ ፡ ወደኔ ፡ አሉት ። እርሱም ፡ ይገድሉኛል ፡ መስሎት ፡
ፈርቶ ፡ እየተንቀጠቀጠ ፡ እጅ ፡ እየነሣ ፡ ቀረበ ። ይህን ፡ ጊዜ ፡
ደመወዝ ፡ የሚሰጡበት ፡ ቀን ፡ ኑሮ ፡ ከፊትዎ ፡ በቀረበ ፡
ጊዜ ፡ ና ፡ ተቀመጥ ፡ ልብስህን ፡ ዘርጋ ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ቸር ፡
ገበሬ ፡ እህሉን ፡ በፍኝ ፡ ዝቆ ፡ ለድኋ ፡ እንደሚሰጥ ፡ ያነን ፡
ብር ፡ በምንጣፍ ፡ ተቈልሎ ፡ የነበረ ፡ ዝቀው ፡ አስታቀፉት ።
እርሱም ፡ እነሣለሁ ፡ ሲል ፡ ከብዶታልና ፡ የሚወድቅ ፡ መ
ሰለ ፡ ከመክበዱ ፡ የተነሣ ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ አይተው ፡
አገሩን ፡ ጠይቀው ፡ የደምቢያ ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ምስለኔውን ፡
አስጠርተው ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ የኔ ፡ ነው ፡ እኔ ፡ አዘዋለሁ ፡ እ
ንጂ ፡ ሌላ ፡ አይድረስበት ፡ አሉ ። ያም ፡ ሰው ፡ ብቻውን ፡
ነበርና ፡ ከዚያ ፡ ከተሸከመው ፡ ብር ፡ አንድ ፡ አንዱን ፡ እንደ ፡
መክፈልት ፡ እያደለ ፡ ገረድም ፡ አሽከርም ፡ ሲል ፡ ፲፭ ያህል ፡
ሰው ፡ ሁኖ ፡ ሄደ ። እግዚአብሔር ፡ ያነዲ ፡ ወያብዕል[1] ፡ ያለ

---

[1] deux mots gheez.

ቸው ፡ ሐና ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ነውና ፡ ለመዓት ፡ የሚሆ
ነውን ፡ ለምሕረት ፡ ያደረጉት ፡ ይህ ፡ ነው ፨ ።
ለምሕረት ፡ የሚሆነውን ፡ ለመዓት ፡ ያደረጉት ፡ በመቅደላ ፡
የነበሩ ፡ እስሮች ፡ በገደል ፡ ሲያስጥሉ ፡ ፩ መነኵሴ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ የፈረደበት ፡ ሲሮጥ ፡ መጥቶ ፡ ይህን ፡ ጉድ ፡ አ
ይቼ ፡ እሄዳለሁ ፡ ሲል ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ ቆመ ። ቴዎድሮ
ስም ፡ ያን ፡ መነኵሴ ፡ አሲዘው ፡ እስሮቹ[1] ፡ በወደቁበት ፡ ገ
ደል ፡ አብሮ ፡ ተጨመረ ። ቅጣት ፡ አይቶ ፡ ቢሄድ ፡ ሞት ፡
የሚገባው ፡ አይመስልምና ፡ የምሕረቱን ፡ ለመዓት ፡ ማድ
ረግዎ ፡ ይህ ፡ ነው ፨ ። እንግዴህ ፡ ወደ ፡ ጥንተ ፡
ነገር ፡ እንመለስ ፡ በሚያዝያ ፡ በ ፩ ቀን ፡ ረቡ ፡ የመቅደላን ፡
እስር ፡ ሁሉ ፡ ፳፱ ሆን ፡ ምሬዋለሁና ፡ አምጡ ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡
ሰላምጌ ፡ ነበሩ ። ፈረንጅም ፡ መጥቶ ፡ ዋድላ ፡ ከሶ ፡ አምባ ፡
ሰፈረ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ እነዚህን ፡ እስሮች ፡ ከአምባሰል ፡ ከ
ማሶ ፡ አባ ፡ ንጋት ፡ የደላንታ ፡ ምስለኔ ፡ ልጅ ፡ በሚባል ፡
ሽፍታ ፡ ወጥተው ፡ የተያዙ ፡ ነበሩና ። በ ፪ ተኛው ፡ ቀን ፡
ጸሎተ ፡ ሐሙስ ፡ ነበር ፡ ራበን ፡ ሀገራችንን ፡ እንግባ ፡ እያሉ ፡
ወደፈጣሪ ፡ እግዚኦ ፡ ይሉ ፡ ዠመር ። ቴዎድሮስም ፡ ይህን ፡
እግዚኦታ ፡ ቢሰሙ ፡ ምናልባቱ ፡ እግዚኦ ፡ እያለ ፡ ያሳጣ
ኛል ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ተቈጣ ፡ አንበሳ ፡ ተነስተው ፡ ያነን ፡
እግዚኦ ፡ ያለውን ፡ እስር ፡ ሁሉ ፡ አምጣው ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡
ወታደርም ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ለምዶታልና ፡ እየተ
ሰለፈ ፡ መጣ ። እንዲህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በገደል ፡ ከገቢያው ፡

[1] እሥሮቹ ፡



አጠገብ ፡ ቊመው ፡ ሲያስጥሉ ፡ አመሹ ፡ እንዲህም ፡ ሲያስ
ጥሉ ፡ ከወደቀው ፡ ከተነባበረው ፡ ተለይተው ፡ ከሞት ፡ የተ
ረፉት ፡ በማግስቱ ፡ ዓርብ ፡ ተገኝተዋል ፡ የክርስቶስ ፡ የቸር
ነቱ ፡ ፍርድ ፡ ረቂቅ ፡ ነውና ፡ ገድሎ ፡ እንደ ፡ ማንሳቱ ፡ ነው ፡
ከገደል ፡ ወድቀው ፡ ደግሞ ፡ በላይ ፡ ሰው ፡ ወድቆባቸው ፡
ተርፈዋልና ፡ እነዚህም ፡ ፪ ናቸው ። ደግሞም ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡
፩ ሴት ፡ አገርዋ ፡ ጐጃም ፡ ምጣ ፡ ስሟ ፡ ኀብሪቱ ፡ በመልክም ፡
የተመሰገነች ፡ ነበረች ፡ የ ፲፩ ወር ፡ ልጅ ፡ አዝላ ፡ የሚያዝያ ፡
ልደታ ፡ ረቡ ፡ አውጥተው ፡ ልጅቱን ፡ በፊት ፡ እናቲቱን ፡
በኋላ ፡ አስገደሏቸው ፡ በጠበንጃ ። ይህችስ ፡ በምን ፡ ተገ
ኘች ፡ እንዲህ ፡ ያለስ ፡ ሞት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አገኛት ፡ ቢሉ ፡
ንጉሥ ፡ ምን ፡ ይልክ ፡ ከመቅደላ ፡ በክርስቶስ ፡ ፈቃድ ፡ ከ
ወጡ ፡ በኋላ ፡ በዓመቱ ፡ የአፈ ፡ ንጉሥ ፡ ወርቄ ፡ ልጅ ፡ መ
ሸሻ ፡ በጅሮንድ ፡ ክንፉ ፡ የሚባል ፡ ዕቃ ፡ ቤት ፡ ነበሩ ። በጳ
ጉሜ ፡ ከመቅደላ ፡ ከድተው ፡ ሲወጡ ፡ ይህች ፡ ሴት ፡ የዚህ ፡
የዕቃ ፡ ቤት ፡ ክንፉ ፡ ሚስት ፡ ነበረችና ፡ ከባሌ ፡ አልለይም ፡
ብላ ፡ በኋላ ፡ ስትሔድ ፡ ደከሚት ፡ ከጥላ ፡ አረፈች ፡ ልጅዋን ፡
ለማጥባት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ባላገር ፡ እንጨት ፡ ሲሰብር ፡ ቢያ
ገኛት ፡ ምንድር ፡ ነሽ ፡ ብሎ ፡ ይዞ ፡ ለመቅደላ ፡ ሹም ፡ አው
ጥቶ ፡ ሰጣት ። ከዚህ ፡ ወዲህ ፡ ተልከ ፡ በንጉሡ ፡ ቃል ፡ ታ
ስራ ፡ ፯ ወር ፡ ተቀምጣ ፡ ነበረች ፡ ከእስር ፡ ቤት ፡ ሁና ። በዚ
ህም ፡ ጊዜ ፡ እነመሸሻ ፡ ወርቄ ፡ ንጉሥ ፡ ምን ፡ ይልክን ፡
ይወዱ ፡ ነበርና ፡ ሸዋ ፡ ለመግባት ፡ ከድተው ፡ ወጥተው ፡
ከሙሐመድ ፡ ሐምዛ ፡ ቤት ፡ አደሩ ። የመቅደላም ፡ ጦር ፡
እነዚህን ፡ ለመከተል ፡ ታዞ ፡ ሲገሠግስ ፡ አደረና ፡ ሲነጋ ፡

ከሙሐመድ ፡ ሐምዛ ፡ ቤት ፡ ቢደርስ ፡ እነመሸሻ ፡ ወርቄ ፡
ተነስተው ፡ ውጊያ ፡ ተዠመረ ፡ ከወሎ ፡ ጦር ፡ ጋራ ፡ ሁነው ፡
ጦሩም ፡ በርትቶ ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ ከባሻ ፡ ደማሹ ፡ ጭ
ፍራ ፡ ገብሩ ፡ ወንዴ ፡ የሚባል ፡ ሙሐመድ ፡ ሐምዛን ፡ በነ
ፍጥ ፡ ባጣለው ፡ ጊዜ ፡ የወረህ ፡ ይመኑ ፡ ባላባት ፡ ገገር ፡ ነበ
ርና ፡ ዓይነተኛው ፡ ሲወድቅ ፡ ሁሉም ፡ ተበተነ ፤ ከዜህ ፡ በ
ኋላ ፡ እነባሻ ፡ ደመሹ ፡ ግዳይ ፡ ሲያስጥሉ ፡ ቈይተው ፡ እን
መለስ ፡ ሲሉ ፡ የወሎ ፡ ጦር ፡ እየረዳ ፡ በኋላ ፡ መጣባቸው ፡
ጥቂትም ፡ ተወግተው ፡ ሲመለሱ ፡ መንገዳቸው ፡ ቍልቍ
ለት ፡ ነበርና ፡ የወሎው ፡ ጦር ፡ ሲጫናቸው ፡ በመርግ ፡ ብዙ ፡
ሰው ፡ አለቀ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ አሊ ፡ ጉበና ፡ የሚባል ፡ የ ፺
አለቃ ፡ በመርግ ፡ ሞተ ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በጌምድር ፡
ነበሩ ፡ የዚህንም ፡ የምስራች ፡ ሲሰሙ ፡ ጾም ፡ ተንቆ ፡ በሁ
ዳዴም ፡ ሥጋ ፡ መብላት ፡ ተለምዶ ፡ ነበር ፡ ከዚህም ፡ የተ
ነሣ ፡ መቅደላ ፡ ለሚጠበቁ ፡ ሴቶች ፡ ፳፫ ነበሩ ፡ ፪፪ ፍሪዳ ፡
ለእቴጌ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ፫ ሰጥተው ፡ ወዳጆቼ ፡ የኔ ፡ የሆና
ችሁ ፡ ሥጋ ፡ ብሉልኝ ፡ ብለው ፡ በሁዳዴ ፡ ሰሞን ፡ ላኩ ።
እነዚያም ፡ ቁባቶች ፡ አንድ ፡ ሁነው ፡ ሲመክሩ ፡ ክርስቲያ
ኖች ፡ ሁነን ፡ በጾም ፡ ሥጋ ፡ ብንበላ ፡ ክርስትናም ፡ ቀረ ፡ ኰን
ኔም ፡ አለብን ፡ ብንተወውም ፡ ይህ ፡ የምድር ፡ ንጉሥ ፡ ፈቃ
ዴን ፡ አላደረጋችሁ ፡ ሲል ፡ በሳይፍ ፡ ልናልቅ ፡ በምድርም ፡
በሰማይም ፡ ፪ ሞት ፡ ያገኛል ፡ ብለው ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ጳጳሱ ፡
ላኩ ። አቡነ ፡ ሰላማም ፡ ሲመልሱ ፡ ልጆቼ ፡ ክርስቶስ ፡ ያድና
ችሁ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ እኔም ፡ አዝንላችኋለሁ ፡ ወደ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ሥጋውን ፡ አትብሉ ፡ ብትሞቱም ፡ ሰማዕት ፡ ናችሁ ፡



ብለው ፡ ላኩባቸው ፡ አልበሉም ። ንጉሡም ፡ ቢሰሙ ፡ አል
ተቈጡም ። ደግሞም ፡ እንደነዚህ ፡ ሰላምጌ ፡ ሰፍረው ፡ የመ
ቅደላ ፡ ወታደር ፡ ሁሉ ፡ እጅ ፡ ሊነሳ ፡ ወረደ ፡ ንጉሡም ፡ አ
ይተው ፡ መቅደሎች ፡ ተጐድታችኋልና ፡ ሥጋ ፡ ብሉልኝ ፡
አሏቸው ። እነዚያም ፡ ወታደሮች ፡ ነገሩ ፡ ቢደንቃቸው ፡
ዝም ፡ ብለው ፡ ሲመለሱ ፡ ፊት ፡ አውራሪ ፡ ገብርዬን[1] ፡ አስ
ጠርተው ፡ ሲወቅሱ ፡ የመቅደላ ፡ ሰው ፡ ምንኛ ፡ ጠልቶኛል ፡
ብለው ፡ ክፉ ፡ ቃል ፡ ቢናገሩ ፡ ፊት ፡ አውራሪ ፡ ገብርዬ ፡ ሲ
መልሱ ፡ ጃንሆይ ፡ የመቅደላ ፡ ሰው ፡ ሴት ፡ ወንዱ ፡ አሽከሩ ፡
ሳይቀር ፡ ሁሉም ፡ ጦራችን ፡ ነው ። አሁን ፡ የተጣላነው ፡ እ
ንደሆን ፡ ይህ ፡ የመጣ ፡ የኋላ ፡ ጦራችን ፡ እኛን ፡ ብቻ ፡ ያገ
ኛል ፡ ይህም ፡ እንዳይረዳን ፡ ይሆናል ፡ ቢሉዎ ፡ እንዳሰቡት ፡
ቀረ ፨ ። እንግዴህ ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ ነገር ፡ እን
መለስ ፡ በሚያዚያ ፡ በ ፫ ቀን ፡ ሰቅለተ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆነ ፡ ዓ
ርብ ፡ በሰዓት ፡ የእንግሊዝ ፡ ዓይነተኛው ፡ ጦር ፡ ደላንታ ፡
ባባ ፡ ላይ ፡ ፊት ፡ ወራሪው ፡ ሻግያ ፡ መንገድ ፡ ጠራጊ ፡ ይሉ
ታል ፡ ባሹሎን ፡ ተሻግሮ ፡ አሮጌ ፡ ሰፈረ ። ይህን ፡ ጊዜ ፡ ቴ
ዎድሮስ ፡ ጦሩን ፡ ውጣ ፡ ብለው ፡ ከመቅደላ ፡ ከሰፈርም ፡
የነበረ ፡ ፴፫ መድፍ ፡ በፋላ ፡ ዙሪያውን ፡ አሰልፈው ፡ ነፍ
ጠኛውን ፡ ጋሻኛውን ፡ ቢለቁት ፡ አሮጌ ፡ ገጠመ ። በዚህም ፡
የፈረንጅ ፡ ጦር ፡ የሸሸ ፡ መስሎ ፡ ወዲህና ፡ ወዲህ ፡ ሲል ፡
የንጉሡ ፡ ጦር ፡ መኻከሉን ፡ ገባለት ፡ ከዚህ ፡ ወዲህ ፡ ከመ
ዠመሪያ ፡ ፊት ፡ አውራሪ ፡ ገብርዬ ፡ ሲወድቁ ፡ ሁሉም ፡

[1] ገብሬን ፡

ድል ፡ ሁኖ ፡ ከሞተው ፡ ከቈሰለው ፡ በቀር ፡ የተረፈው ፡ ምር
ከውም ፡ ተመለሰ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ በፋላ ፡ መንገድ ፡
መነጽር ፡ ይዘው ፡ ነበርና ፡ ድል ፡ መሆንዎን ፡ አይተው ፡ ይ
ልቁንም ፡ የፊት ፡ አወራሪ ፡ ገብርዬን ፡ ሞት ፡ ቢሰሙ ፡ ደንግ
ጠው ፡ ከሰፈርዎ ፡ ሰላምጌ ፡ ገብተው ፡ አዝነው ፡ ተቀመጡ ።
ሠራዊትዎም ፡ ሁሉ ፡ ለየራሱ ፡ መውጫውን ፡ አሰበ ። በማ
ግሥቱም ፡ ቅዳሜ ፡ ሥዑር ፡ ሲሆን ፡ ከህናቱ ፡ ተሰብስበው ፡
ቈጠማ ፡ ይዘን ፡ ገብረ ፡ ሰላመ ፡ እንዳንል ፡ ንጉሡ ፡ እንዴህ ፡
ሁነው ፡ በደስታ ፡ አይቀበሉን ፡ እንዳንቀር ፡ ፈራን ፡ ብለው ፡
ለራስ ፡ ቢሠውር ፡ ላኩ ፡ ከዚህ ፡ ወዲህስ ፡ እዘኑ ፡ አልቅሱ ፡
እንጂ ፡ ሁሉስ ፡ ምን ፡ ይሆናችኋል ፡ ብለዋቸው ፡ ቀሩ ። ከ
ዜህ ፡ በኋላ ፡ ከእንግሊዝ ፡ የመጣው ፡ አይነተኛው ፡ ሥል
ጣን ፡ ይባላል ፡ ከሀገሬ ፡ የመጡ ፡ ያሰርኳቸውን ፡ ፈትተህ ፡
ገንዘባቸውንም ፡ ጨምረህ ፡ ፩ ሳይቀር ፡ ስደድልኝ ፡ ብሎ ፡
ላከ ። ንጉሡም ፡ ይህን ፡ ቢሰሙ ፡ ፳፪ ፍሪዳ ፡ ፳፪ በግ ፡ ሰብ
ስበው ፡ ራሰምን ፡ እስከ ፡ ወገኖቹ ፡ ፈትተው ፡ ሰደዱለት ።
ሥልጣንም ፡ ያንን ፡ የመጣ ፡ ፍሪዳና ፡ በግ ፡ አልተቀበለም ፡
ከድኃ ፡ የተቀማ ፡ ገንዘብ ፡ ነውና ፡ በለውት ፡ ማንም ፡ እየ
ወሰደው ፡ እየሞተም ፡ ቀረ ። በ፳ተኛውም ፡ ቀን ፡ እሑድ ፡
ትንሣኤ ፡ ሲሆን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሲጨነቅ ፡ ውሎ ፡ ሌሊቱን ፡
ጨረቃ ፡ በደም ፡ አምሳል ፡ ተከበ ፡ ቢታይ ፡ ለንጉሡ ፡ ኀል
ፈት ፡ ምልክት ፡ ሆነ ። ወዲያውም ፡ ንጉሡ ፡ ይህን ፡ ምል
ክት ፡ ቢያዩ ፡ ተነስተው ፡ መንገድ ፡ ዠመሩ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡
ባሻ ፡ አሰኔ ፡ ወደ ፡ ማን ፡ ሀገር ፡ እንሄዳለን ፡ ጃንሆይ ፡ ሁሉም ፡
ጠልቶናል ፡ አሁንስ ፡ እንመለስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያዘዘው ፡ አይቀ



ርም ፡ ብለው ፡ ተመልሰው ፡ ከሰፈር ፡ ገብተው ፡ ወደኔ ፡ የም
ትሆን ፡ መቅደላ ፡ ግባልኝ ፡ አሉ ። ይህን ፡ ጊዜ ፡ ወታደር ፡
እየተነሳ ፡ እስካሁን ፡ የተጨነቅነው ፡ አንሶን ፡ እንግዴህ ፡ መ
ቅደላ ፡ ምናችን ፡ ነው ፡ እያለ ፡ በፊትዎ ፡ እየተናገረ ፡ ሲሄድ ፡
በሰላምጌ ፡ ሜዳ ፡ የሰፈረ ፡ ሁሉ ፡ ድንኳኑን ፡ እየነቀለ ፡ የከበ
ደውን ፡ ጥሎ ፡ የቀለለውን ፡ አንስቶ ፡ ተጠቅሎ ፡ ሲነሳ ፡ ን
ጉሡ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መዓት ፡ የሠራዊትዎን ፡ ክዳት ፡
ቢያዩ ፡ ከመናደድ ፡ የተነሳ ፡ በጕዘው ፡ ኋላ ፡ ደርሰው ፡ ባንዱ ፡
ላይ ፡ ጠበንጃ ፡ ተኰሰው ፡ ቢስቱት ፡ እርሱም ፡ አዞሮ ፡ ተ
ኰሰ ። ነገር ፡ ግን ፡ አልመታዎም ፡ የክርስቶስ ፡ ትእዛዝ ፡
ገና ፡ ስለ ፡ ሆነ ። የዚህንም ፡ ታሪክ ፡ የዳዊት ፡ ነገር ፡ ያስረዳ
ናል ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ቢሉ ፡ ዳዊትን ፡ አቤሴሎም ፡ ልጁ ፡ ከመ
ንግሥቱ ፡ ባሰጣው ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ፈጣሪው ፡ እያዘነ ፡ ሲሄድ ፡
ሳሚ ፡ ወልደ ፡ ጌራ ፡ የሚባል ፡ ከመንገድ ፡ ላይ ፡ ተነስቶ ፡
ሲሰድበው ፡ ሲያዋርደው ፡ አቢሳ ፡ ቢሰማ ፡ ጌታዬን ፡ ንጉ
ሡን ፡ እንዴት ፡ ብሎ ፡ ይህ ፡ ይሳድባል ፡ ሲል ፡ ሊገድለው ፡
ወደርሱ ፡ ቢቀርብ ፡ ዳዊት ፡ ልበ ፡ ሰፊ ፡ ነገር ፡ አሳላፊ ፡ ነውና ፡
ተው ፡ እግዚአብሔር ፡ ዳዊትን ፡ ስደብ ፡ ብሎ ፡ አዞታልና ፡
ብሎ ፡ አቢሳን ፡ መለሰ ። ምነው ፡ እንዲህ ፡ ማለቱ ፡ ቢሉ ፡
እግዚአብሔር ፡ ፍጥረቱን ፡ በተጣላበት ፡ ወራት ፡ ሁሉም ፡
ጠላት ፡ ይሆናልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ቴዎድሮስም ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ እንደ ፡ ተለይዎ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ከዳዎ ፡ አይተው ፡
ተመልሰው ፡ ከመቅደላ ፡ በር ፡ በታች ፡ ተቀመጡ ። እግዚ
አብሔር ፡ ተለየ ፡ ማለትም ፡ በረድኤት ፡ በስራ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡
በምልዓት ፡ አይዶለም ፡ እርሱ ፡ የማይኖርበትስ ፡ ፍጥረት ፡

የለም ፨ ። እንዲህም ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ የእንግ
ሊዝ ፡ ጦር ፡ ወደ ፡ ሰላምጌ ፡ እየተጓዘ ፡ መጥቶ ፡ በሰልፍ ፡ ሥ
ራት ፡ ሜዳውን ፡ ሁሉ ፡ ያዘው ። ይህን ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ ቦምባ ፡
ያልነው ፡ ስራ ፡ ከገቢያው ፡ ላይ ፡ አድርሰው ፡ ትተውት ፡
ነበርና ፡ እንግሊዞች ፡ አይተው ፡ እጅግ ፡ ናቁት ፡ ስለ ፡ ምን ፡
ቢሉ ፡ ይኸው ፡ ከተሰራ ፡ ዠምሮ ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ በርሱ ፡
ደክሞ ፡ ነበር ፡ በተጨረሰም ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ሰሪዎቹን ፡ እነ
ዋልትማየርን ፡ ተኩሱትና ፡ ድምፁን ፡ ልስማው ፡ የአረሩ
ንም ፡ መንገድ ፡ ልየው ፡ ቢሉ ፡ እነዚያም ፡ በተንኰል ፡ ጥ
በብ ፡ ሲያታልሉ ፡ አሁን ፡ ብንተኵሰው ፡ በከተማ ፡ ሀገር ፡
መኻከል ፡ የድምፁ ፡ ኃይል ፡ የቀረበች ፡ እርጉዝ ፡ ያሶር
ዳል ፡ የደከመ ፡ በሽተኛ ፡ ይገድላል ፡ እያሉ ፡ እውነት ፡ አስ
መስለው ፡ ሳይተኰስ ፡ ቀርቶ ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ተናገርነ ፡ ከደ
ብረ ፡ ታቦር ፡ ተነስቶ ፡ በ፺ ወር ፡ በብዙ ፡ ድካም ፡ ሰውም ፡
እየሞተበት ፡ እስከ ፡ መቅደላ ፡ ደረሰ ። በዚያም ፡ ጊዜ ፡ ከገቢ
ያው ፡ ላይ ፡ ለወግ ፡ ለታሪክ ፡ ሁኖ ፡ ቀረ ። ከዚህ ፡ ወዲህ ፡
የቴዎድሮስ ፡ ሠራዊት ፡ ተነስተው ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ ወ
ገን ፡ ቢገቡ ፡ የጦር ፡ መሳሪያን ፡ ሁሉ ፡ እየተቀበሉ ፡ ጋሻ ፡
ጋሻውን ፡ በእሳት ፡ አቃጠሉት ፡ አንድ ፡ ሳይቀር ። ከዚህ ፡
በኋላ ፡ የእንግሊዝ ፡ ወገን ፡ መድፉን ፡ እየከፈለ ፡ በሰላምጌ ፡
ተራራ ፡ መቅደላን ፡ አስተያይቶ ፡ ተቀመጠ ፡ ብዙውንም ፡
መድፍ ፡ በገቢያው ፡ ላይ ። የቀረውን ፡ በፋላ ፡ አራዳ ፡ በ
ሾላ ፡ ከውሀው ፡ አጠገብ ፡ አድርጎ ፡ ሜዳውን ፡ ይዞ ፡ ሳለ ፡
ንጉሡም ፡ ከታችኛው ፡ በር ፡ ተቀምጠው ፡ ሠራዊትዎ ፡
ተጨርሶ ፡ ሄዶ ፡ የመቅደላው ፡ ከበር ፡ ታገደ ። ይህን ፡ ጊዜ ፡



ንጉሡ ፡ የሚይዘው ፡ እንደጠፋ ፡ እንደ ፡ ሰከረ ፡ ሰው ፡ ሁ
ነው ፡ ከፈረስ ፡ ወጥተው ፡ ከበር ፡ ተነሱ ። እንዲህም ፡ ከሆነ ፡
ጊዜ ፡ የሚከተልዎን ፡ እየተቆጡ ፡ ሲሄዱ ፡ ከእንግሊዝ ፡ ወ
ገን ፡ ፪ እየገደሉ ፡ ተመለሱ ። ስለ ፡ ምን ፡ ከዚህ ፡ ላይ ፡ ሳይ
ሞቱ ፡ ቀሩ ፡ ጠበንጃስ ፡ ሳይተኰስብዎ ፡ ቀረ ፡ ቢሉ ፡ የሚ
ሞቱበት ፡ ሰዓት ፡ ገና ፡ ስለ ፡ ሆነ ። ደግሞም ፡ የእንግሊዞች ፡
ሥርዓት ፡ እግዚአብሔር ፡ መርጦ ፡ ያነገሠውን ፡ እንደ ፡ ንግ
ሥት ፡ ቃል ፡ አንገድልም ፡ ማለት ፡ ይመስላልና ፡ ስለዜህ ፡
በደህና ፡ ተመልሰው ፡ ከመዠመሪያው ፡ በር ፡ ገብተው ፡ ተ
ቀመጡ ። ይህን ፡ ጊዜ ፡ በሰላምጌ ፡ የተሰለፈ ፡ መድፍ ፡ ሲቀ
ድም ፡ የነፍጥ ፡ ተኵስ ፡ ሲከተል ፡ ፩ አፈኛ ፡ ወታደር ፡ እን
ዲህ ፡ አለ ። እኒህ ፡ ንጉሥ ፡ ከዚህ ፡ መቅደላ ፡ መግባታቸው ፡
እኛን ፡ ይዘው ፡ ሊሞቱ ፡ ነው ፡ ከዚህ ፡ ኵሉ ፡ ይዘን ፡ ብን
ሰጥ ፡ ምን ፡ አለ ፡ ሲል ፡ አንዱ ፡ ሲመልስ ፡ አንት ፡ ዋሾ ፡ ስ
ትዋሽ ፡ የለመድህ ፡ እሳት ፡ ጨብጦ ፡ የሚቆም ፡ ማነው ፡ አ
ለው ። ሰው ፡ ከመባልዎ ፡ በቀር ፡ የቴዎድሮስ ፡ ሁለንተና ፡
እሳት ፡ ነውና ። አንዱም ፡ ሲመልስ ፡ ምንኛ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡
ተናገርህ ፡ ስንኳን ፡ ለሞት ፡ ለጠላት ፡ አሳልፈን ፡ እንሰጥ ፡
ከቤታችንም ፡ ሁነን ፡ ንጉሥን ፡ ብንከዳ ፡ ይፈረድብናል ።
ደግሞም ፡ ይህ ፡ የመጣ ፡ የእንግሊዝ ፡ ሹም ፡ ሥልጣን ፡ እኒህ ፡
የሀበሻ ፡ ሰዎች ፡ ንጉሣቸውን ፡ ከዱ ፡ ሲል ፡ ይታዘበናል ፡ ታ
ዝቦም ፡ አይቀር ፡ አስፈርዶ ፡ ያስፈጀናል ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥቱ ፡
እኛም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ላናደርገው ፡ ላይሆንልን ፡ አለው ።
በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ለነዚያ ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ቀረ ፡ በመ
ዠመሪያ ፡ ንጉሥን ፡ ይዘን ፡ እንስጥ ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ ቅደ

ምልን ፡ መያዙን ፡ በኋላ ፡ እኛ ፡ እንረዳለን ፡ ማለት ፡ ነበረ ። እንዲህም ፡ ባሉት ፡ የዲያብሎስ ፡ አምሳል ፡ ይሆን ፡ ነበር ፡ የዚህስ ፡ ነገር ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ሲፈጥር ፡ አስቀድሞ ፡ መላእክትን ፡ በጨለማ ፡ ፈጥሮ ፡ አስቀመጣቸው ። በዚህ ፡ መኻከል ፡ እርሱ ፡ በባሕርዩ ፡ ቢሠወራቸው ፡ ማን ፡ ፈጠረን ፡ ወይስ ፡ እርስ ፡ በርሳችን ፡ ተፈጣጠርን ፡ እያሉ ፡ ሲነጋገሩ ፡ ሰምቶ ፡ ይኸው ፡ ዲያብሎስ ፡ ዙፋኑ ፡ ማዕርጉ ፡ ከሁሉ ፡ በላይ ፡ ነበርና ፡ ትዕቢት ፡ ይዞት ፡ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ፈጣሪውን ፡ አጥቶ ፡ ተቸግርዋል ፡ እኔ ፡ ፈጠርኋችሁ ፡ ብዬ ፡ ልመስገን ፡ ብሎ ፡ አሰበ ። አስቦም ፡ አልቀረ ፡ እስመ ፡ እምተረፈ ፡ ልብ ፡ ይነብብ ፡ አፍ ፡ እንዲል ። እኔ ፡ ፈጠርኋችሁ ፡ እመኑልኝ ፡ ስገዱልኝ ፡ አላቸው ። መላእክትም ፡ የአካላቸው ፡ ብርሃን ፡ እንደ ፡ ጨረቃ ፡ ሁኖላቸው ፡ ሰይፉ ፡ እንደ ፡ ሰይፋቸው ፡ ክንፉ ፡ እንደ ፡ ክንፋቸው ፡ ሁኖ ፡ አዩትና ፡ አንተማ ፡ እንደኛ ፡ አይደለህም ፡ በምን ፡ በልጠኸን ፡ ፈጠርኸን ፡ ቢሉት ፡ ከላንተ ፡ በላይ ፡ ስታዩኝ ፡ በምን ፡ በልጠኸን ፡ ትሉኛላችሁ ፡ የፈጠርኋችሁስ ፡ እኔ ፡ ነኝና ፡ ስገዱልኝ ፡ አላቸው ። መላእክትም ፡ አዋቆች ፡ ናቸውና ፡ እንተ ፡ እኛን ፡ ብትፈጥር ፡ እኛ ፡ በኤረር ፡ ያሉን ፡ ባልፈጠርንም ፡ ነበር ፡ እረ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ፈጠርኸን ፡ ቢሉት ፡ እላንት ፡ ምቀኞች ፡ ተመቅኝታችሁኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የፈጠርኋችሁማ ፡ እኔ ፡ አይደለሁም ፡ ይልቅስ ፡ እመኑልኝ ፡ ስገዱልኝ ፡ ቢላቸው ፡ በላ ፡ ከሆነልህማ ፡ ሠዓሊ ፡ በሥዕሉ ፡ ፈጣሪ ፡ በፍጡሩ ፡ ይታወቃልና ፡ እንግዳ ፡ ፍጥረት ፡ ፈጥረህ ፡ አሳየንና ፡ እንስገድልህ ፡ አሉት ። ዲያብሎስ ፡ ግን ፡ አፍ ፡ እኩል ፡ ጉል



በት ፡ ስንኩል ፡ እንዲሉ ፡ ፈጠርኋችሁ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መፍጠር ፡ ተሳነው ፡ ሐሰቱ ፡ ክህደቱ ፡ ታወቀ ፡ ሐሰት ፡ ክህደት ፡ የተባለ ፡ ሁሉ ፡ ከዲያብሎስ ፡ ተገኘ ። ያም ፡ ወታደር ፡ እንያዝ ፡ ብሎ ፡ በአፉ ፡ ተናገረ ፡ እንጂ ፡ ቴዎድሮስን ፡ በእጁ ፡ ይዞ ፡ አልታየምና ፡ ስለ ፡ ዚህ ፡ ዲያብሎስን ፡ መሰለ ፨

። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከበሩ ፡ ላይ ፡ ጥኑ ፡ ውጊያ ፡ ተዠመረ ፡ ከእንግሊዝም ፡ ወገን ፡ ፩ መድፍ ፡ ሲተኰስ ፡ በሩ ፡ ተሰበረ ፡ ከዚህም ፡ ላይ ፡ ከወዲያም ፡ ከወዲህም ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ሞተ ። ከዚህም ፡ ጊዜ ፡ የክረምት ፡ ነጐድጓድ ፡ መሰለ ፡ የመድፉና ፡ የነፍጡ ፡ ድምጥ ። እንዲህም ፡ ሲሆን ፡ የእንግሊዝ ፡ የመድፉ ፡ አረር ፡ ልኩ ፡ በክንድ ፡ አውራጣት ፡ ድረስ ፡ ነው ፡ በውስጡም ፡ ባሩድና ፡ አረር ፡ አለው ። ባረፈም ፡ ጊዜ ፡ በገዛ ፡ ኃይሉ ፡ ተተኰሶ ፡ የመጣውን ፡ ያህል ፡ ይሄዳል ። ሲሄድም ፡ ሳያርፍ ፡ የሚተኰስ ፡ ነበረ ። አለ ፡ ድምጥም ፡ መጥቶ ፡ ሲያርፍ ፡ የሚተኰስ ፡ ነበረ ፡ ፫ ወገን ፡ ነው ። ከዚህም ፡ አስቀድሞ ፡ ደላንታ ፡ ሲደርስ ፡ ቢተኩሱት ፡ በሸሎን ፡ ተሻግሮ ፡ በዳውንት ፡ መሻገሪያ ፡ መንገድ ፡ አረፈ ፡ ፋላ ፡ ሰላምጌም ፡ ሁኖ ፡ የተተኰሰው ፡ መቅደላን ፡ እየዘለለ ፡ ይሄድ ፡ ነበረ ። ከውስጡም ፡ የቀረ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ እየወደቀ ፡ የተነሣው ፡ ብዙ ፡ ነው ። በዚህም ፡ መኻከል ፡ የእንግሊዝ ፡ ወገን ፡ በሩን ፡ ሰብሮ ፡ ሲገባ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ከላይኛው ፡ በር ፡ አልፈው ፡ ተቀመጡ ። በቋንቋው ፡ እየተናገረ ፡ ነገሩም ፡ ማፉሽ[1] ፡ የለም ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ቴዎድሮስን ፡ ንጉሡን ፡ እየፈ

[1] mot arabe : ما فيه شى dénaturé.

ለገ ፡ ሲቀርብ ፡ ቢያዩት ፡ ይህስ ፡ ይዞ ፡ አስሮ ፡ ሲወስደኝ ፡
ሞቱ ፡ ይሻለኛል ፡ ብለው ፡ በራስዎ ፡ ፈርደው ፡ እንደ ፡ ዓመ
ፀኛ ፡ ጠበንጃ ፡ አሶጡበት ። እንዲህም ፡ በእጅዎ ፡ ሲሞቱ ፡
የዚህም ፡ ወሬ ፡ እንደ ፡ ስምዎ ፡ በየሀገሩ ፡ ደረሰ ። ለዚህም ፡
ሞትዎ ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ የተደረገ ፡ አልቃሽ ፡ ስታለቅስ ፡

ዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ይዞ ፡ የገዛው ፡ ንጉሥ ፡
እንዲህን ፡ ስሱ ፡ ጠበንጀ ፡ የሚጐርስ ።
በዚያ ፡ በመቅደላ ፡ ጩኸት ፡ በረከተ ፡
የሴቱን ፡ አላውቅም ፡ ወንድ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሞተ ፡
አያችሁት ፡ ብያ ፡ ያንበሳውን ፡ ሞት ፡
በሰው ፡ እጅ ፡ መሞትን ፡ ነውር ፡ አድርጎት ፡

አለች ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሁሉም ፡ በሥልጣን ፡ እጅ ፡ ሆነ ፡
የመቅደላም ፡ ወታደር ፡ ሁሉ ፡ የጦር ፡ መሰሪያውን ፡
ገደል ፡ እየጣለ ፡ እጅ ፡ ነስቶ ፡ ሲቆም ፡ በምጥ ፡ እንደ ፡
ተያዘች ፡ ሴት ፡ መሰለ ። ያለወቀ ፡ መሳሪያውን ፡ ያልጣለ ፡
የሚዋጋ ፡ መስሎ ፡ እጅግ ፡ ሰው ፡ አለቀ ። ጋሻ ፡ ጦር ፡ ነፍ
ጥም ፡ የያዘውን ፡ የእንግሊዝ ፡ ወገን ፡ እየተቀዳደመ ፡ በነ
ፍጥ ፡ ፈጀው ፡ ስለምን ፡ ቢሉ ፡ እንኳን ፡ በጦር ፡ ጊዜ ፡ የጦር ፡
መሳሪያ ፡ ድል ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ ከሰፈሩም ፡ ከገቢያውም ፡ ለ
የጉዳዩ ፡ ሲሄድ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሰው ፡ ጦር ፡ ትንሽም ፡ የወ
ገብ ፡ ብረት ፡ ይዞ ፡ የሚገባ ፡ አልነበረምና ፡ ስለዚህ ፡ የጦር ፡
መሳሪያ ፡ ሲያይ ፡ ሰውን ፡ ይገድል ፡ ነበረ ፡ ደግሞም ፡ የሀ
በሻ ፡ ሰው ፡ ከዳተኛ ፡ ይባላልና ፡ አስቀድሞ ፡ እንዳይገድለ
ው ፡ ይመስላል ። እንዲህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ከሞት ፡ የተረፈ ፡
ከየስፍራው ፡ እየወጣ ፡ በመቅደላ ፡ ሲሰበሰብ ፡ ሥልጣን ፡



የእንግሊዞችም ፡ ሹም ፡ ንጉሡን ፡ ከወደቁበት ፡ አስነሣ ፡
ለማስቀበር ፡ ቀኑም ፡ ማክሰኞ ፡ ማታ ፡ ጊዜ ፡ ነበረ ። የሞቱ
በት ፡ ግን ፡ ሰኞ ፡ ነው ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ዕለቱን ፡ ሳይቀበሩ ፡ ቀሩ ፡
ቢሉ ፡ ከንጉሡ ፡ ከቴዎድሮስ ፡ ጋራ ፡ የነበሩ ፡ የእንግሊዝ ፡ ወ
ገኖች ፡ የሌሎችም ፡ የንጉሡን ፡ ከእግር ፡ እስከ ፡ ራስዎ ፡ መ
ልክዎን ፡ አስመስለው ፡ ሥለው ፡ ከእንግሊዝ ፡ ንግሥት ፡
ገብቶ ፡ ይኖራል ፡ የሀበሻ ፡ ንጉሥ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ለማለት ።
በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ሥልጣን ፡ የቴዎድሮስ ፡ ሥዕል ፡ አምጥቶ ፡
ቢያዩ ፡ ሥዕሉ ፡ ከመልክዎ ፡ ፩ ሆነለት ። ይህን ፡ ጊዜ ፡ በው
ነት ፡ የሀበሻ ፡ ንጉሥ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሞትዎን ፡ አመነ ።
ይህ ፡ ባይሆን ፡ ቴዎድሮስ ፡ መሆንዎን ፡ ሞትዎንም ፡ አያም
ንም ፡ ነበርና ፡ ስለዚህ ፡ ዕለቱን ፡ ሳይቀበሩ ፡ ቀሩ ። በተቀበ
ሩም ፡ ጊዜ ፡ መቃብር ፡ ሲደርስ ፡ እንደ ፡ በልግ ፡ ጊዜ ፡ በረዶ ፡
ቢዘንብ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በውሀ ፡ ጥም ፡ እጅግ ፡ ተጨንቆ ፡ ነበ
ርና ፡ በረዶውን ፡ እያፈሰ ፡ ሲቅም ፡ ውሀ ፡ ጥሙ ፡ ታገሠለት ።
ከየምንጩ ፡ የሚገኘውን ፡ ከየጕድጓዱም ፡ በ ፩ ብር ፡ ፩ ዋ
ንጫ ፡ ውሀ ፡ የእንግሊዝ ፡ ወገን ፡ እየገዛ ፡ ይጠጣ ፡ ነበረ ፡ አለ
ዋጋ ፡ ቀምተው ፡ የሚወስዱት ፡ ነገር ፡ ስለሌለ ። በዚህም ፡
ጊዜ ፡ የምርኮውን ፡ ዙሪያ ፡ በመድፍና ፡ በነፍጥ ፡ አጥሮ ፡ ፫ አ
ላማ ፡ ነጭና ፡ ጥቁር ፡ ቀይ ፡ ተከለ ፡ ይህም ፡ ጥቁርና ፡ ቀዩ ፡ የኀ
ዘን ፡ የመከራ ፡ ነጩ ፡ የዕርቅ ፡ የደስታ ፡ ምልክት ፡ ተባለ ። በዚ
ህም ፡ ቀይና ፡ ጥቁሩ ፡ ሲነሳ ፡ ነጩ ፡ አላማ ፡ ሲቀር ፡ የሀበሻ ፡
ሰው ፡ ምሬኻለሁ ፡ በየሀገርህ ፡ ግባ ፡ ብሎ ፡ ዓዋጅ ፡ ሲነግር ፡
ቋንቋው ፡ በአማርኛ ፡ ሲወጣ ፡ እልልታ ፡ ደስታ ፡ ተደረገ ።
በማግስቱ ፡ ረቡ ፡ ሲረፍድ ፡ ፩ ሳይቀር ፡ የመቅደላ ፡ ሰው ፡

ወጥቶ፡ ሰላምጌ፡ ሰፈረ። የእንግሊዞች፡ ወገን፡ ከአምባው፡ ውስጥ፡ ገብቶ፡ እስከ፡ ዓርብ፡ ድንኳኑን፡ ተክሎ፡ ተቀምጦ፡ ነበረ። የንጉሡም፡ ልጅ፡ ዓለም፡ አየሁ፡ ከእናቱ፡ ጋራ፡ ከ እንግሊዞች፡ አልተለየም። እንዲህም፡ በተደረገ፡ ጊዜ፡ ሚ ያዝያ፡ ከገባ፡ ፫ ቀን፡ ፋሲካ፡ ነበረ። የመቅደላ፡ ደኅናውም፡ እስሩም፡ እየተፈታ፡ አሮጌ፡ ሰፈረ። የጸሎተ፡ ሐሙስ፡ ዕለት፡ ፩፻ እስሮች፡ በገደል፡ ሲያልቁ፡ እነዚህ፡ እንደምን፡ ተረፉ፡ ቢሉ፡ ሁሉም፡ ለሞት፡ ቀርበው፡ ነበሩ፡ ነገር፡ ግን፡ በክርስ ቶስ፡ ፈቃድ፡ ከአቶ፡ ይገዙ፡ ልጅ፡ ከሸዋው፡ ሰው፡ በቀር፡ የቀረውን፡ ሁሉ፡ ምረውታል። የዚህም፡ ሞት፡ ከሴትዎ፡ ነገር፡ የተነሣ፡ መሰኋል። ከዚህ፡ በኋላም፡ አሮጌ፡ የተደ ረገው፡ እነራስ፡ ዳርጌ፡ እነዋግሹም፡ ተፈሪ፡ ከእስራት፡ ወጥ ተው፡ ነበሩና፡ ከሥልጣን፡ ቢገናኙ፡ አባቶቻቸውን፡ ጠይቆ፡ በየሀገራችሁ፡ ግቡ፡ አለ። ይህን፡ ጊዜ፡ ወይዘሮ፡ መስታዎት፡ ብትመጣ፡ በሥልጣን፡ ቃል፡ ራስ፡ ዳርጌ፡ የሸዋን፡ ሰው፡ ሁሉ፡ ይዘው፡ ከባትዎ፡ ሀገር፡ ሸዋ፡ ገብተው፡ ተቀመጡ። ይህም፡ ታሪክ፡ የተጣፈ፡ ቴዎድሮስ፡ ከሞቱ፡ ከ፲፫ ዓመት ዓለም፡ ከተፈጠረ፡ ፯ሺ፡ ከ፫፻፸፫ ዓመት፡ ነው።